
# የእንስሳት አብዮት



«ሁሉም እንስሳት እኩል ናቸው።
ነገር ግን ጥቂት እንስሳት ከሌሎች ይበልጥ እኩል ናቸው። »

ደራሲ - ጆርጅ ኦርዌል
ተርጓሚ - መስፍን ማሞ ተሰማ

# የእንስሳት አብዮት


## ደራሲ - ጆርጅ ኦርዌል
## ተርጓሚ - መስፍን ማሞ ተሰማ



**የሽፋን ምስልና የውስጥ ገጽ ቅንብር**
**ተከስተ እሸቴ**

የመጀመሪያ ዕትም ሚያዚያ 2003 ዓም

© መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው

Printed by
Sigma Signs & Graphics
(02) 9621 4424
0425 232 590
Sydney - Australia

**«ከመጻህፍት አንዳንዶች የሚቀመሱ፤ አንዳንዶች የሚዋጡ ፤ ሌሎች ደግሞ የሚመነዠኩም ናቸው። »**

ፍራንሲስ ቤከን

**ይህ የትርጉም ሥራ**

## መታሰቢያነቱ

**በተስፋይቱ ምድር ኢትዮጵያ ከአለፉት አያሌ ዓመታት ጀምሮ ለፍትህ፣ ለአንድነት፣ ለባንዲራ ክብር፣ ለሀገር ሉዓላዊነት፣ ለሕግ የበላይነት፣ ለሰው ልጆች ሰብዓዊ መብት መከበር፤ ለዜጎች ሁሉ እኩልነት፤ በጥቅሉ ለዲሞክራሲያዊ ስርዓትና ለመልካም አስተዳደር እውን መሆን የሕይወት መስዋዕትነትን ለገበሩት፤ በየወህኒ ቤቶችም በግፍ ለማቀቁት ኢትዮጵያውያን ሁሉ ይሁን ! !**

**መ . ማ . ተ .**

# ምሥጋና

የእንስሳት አብዮትን ረቂቅ በማንበብ ሙያዊ አስተያየቶቻቸውን ያለ አንዳች ገደብ ላካፈሉኝ ስደተኛ ጋዜጠኞች፤

በኢትዮጵያ የቀድሞ የብስራት ጋዜጣና አሁን የቋጠሮ ድረ ገጽ አዘጋጅ ሳምሶን አስፋው፤

የታገዱ የኢትዮጵ ጋዜጣና መጽሄት ዘጋቢና በሲድኒ ትታተም የነበረችው የድንቅነሽ መጽሄት አዘጋጅ አብይ አፈወርቅ፤

የዚህን ትርጉም ስራ የሽፋን ምስል ስራ በመንደፍና የውስጥ ገፆቹን ቅርጽ በማዘጋጀት ጊዜውንና እውቀቱን ለተባበረኝ የሲድኒዋ ድንቅነሽ መጽሄት ዲዛይንና ሜክአፕ አቀናባሪ፤ በአውስትራሊያ የኒው ሳውዝ ዌልስ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማኅበር ድረ ገጽ አዘጋጅ ተከስተ እሸቴ፤

እነሆ ልባዊና ወንድማዊ ምስጋናዬ በያላችሁበት ይድረሳችሁ ! !

# በትርጉም ሥራው ዙሪያ

መስፍን ማሞ «እነሆ ‘የእንሰሳት አብዮት’ ... » ብሎናል። ከዝነኛው እንግሊዛዊ ደራሲ ከጆርጅ ኦርዌል “Animal Farm” ወደ አማርኛ ቋንቋ የመለሰው አዲስ መታያው ነው። ይህ ስራ በብዙ ያለማችን ቋንቋዎች እየተተረጎመ ትርክቱና የፈጠራው ይትብሃል ሁሌም ተደራሲን እያስደመመ የሚኖር ምጸት ስንቁ ስራ ነው። ተርጓሚ መስፍን ማሞ እንደወትሮው ሁሉ ዓይነ ግቡ ብዕርተኛ መሆኑን በዚህ የትርጉም ሥራውም ላይ አሳይቷል። ይህንን ዘመን ጠገብ ሥራ ውብ በሆነ አማርኛ ታድጎናል። ፈረንጅኛ ስም የያዙት ገጸ ባህርያት ብቅ እያሉ ባያነቁን ኑሮ ልክ አዲስ ያማርኛ ወጥ ሥራ እየተደረሰን ያለን ያህል ይሰማናል። ይህ ደሞ ከመገኛ ቋንቋው የጠለፈበት አማርኛው የሸገነ መሆኑን የምናስተውለው ያለእረፍት ከገጽ ገጽ ስንፈተለክ እራሳችንን ማግኘታችን ነው። ተርጓሚው፤

(1) ተዛማጅ/ውርስ ------Adaptation;
(2) ባህላዊ ትርጉም ------Cultural translation;
(3) ጽንፈ ባህል ትርጉም ----Cultural-bound translation;
(4) እሙን ትርጉም ------ Faithfull translation;
(5) ልቅ፥ ነጻ ትርጉም ------Free translation;
(6) ጥብቅ፥ ጥሬ ትርጉም ----Literal translation; ከሚባሉት የትርጉም ዓይነቶች መካከል በአራተኛው ተራ ቁጥር የተመለከተውን «እሙን ትርጉም ---- Faithfull translation »ንን መርጦ እንደተጠቀመበት ማስተዋል ይቻላል። ይህም ለሥራው ልቀት የበኩሉን በጎ ሚና ተጫውቷል። በሌላ ወጥና ትርጉም ሥራዎቹ ዳግም እንድናገኘው የሩቅ አውስትራሊያዋን የጥበብ አድባር ተማለጂን እንላታለን።

ጋዜጠኛና ደራሲ
አበራ ለማ
በኖርዌይ ደራስያን ማኅበር
የዓለም አቀፍ ኮሚቴ ቦርድ አባል፤ ኦስሎ

********* | *********

ሙሃመድ ቡአዚዝ ራሱን በማቃጠል በቱኒዚያ የቀሰቀሰው አብዮት እነሆ ሰደድ እሳት ሆኖ በ17 የዓረብ ሀገራት ተቀጣጥሎ፤ የታችኛውንም የአፍሪካ ክፍል መጎብኘት ጀመረ።

በዚህም ወቅት ከ65 ዓመታት በፊት ለንባብ የበቃው የጆርጅ ኦርዌል 'Animal Farm' መጽሀፍ በመስፍን ማሞ 'የእንስሳት አብዮት' በሚል ወደ አማርኛ ተመልሶ ደረሰኝና አነበብኩት።

ብዙዎች በንግግራቸውና በፅሁፎቻቸው የሚጠቅሱት ይህ ዝነኛ መፅሀፍ ዘመን የማይሽረው መሆኑን ዛሬ በአብዮት በሚናጠው የአፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ ክፍል ተወላጆች የሆንን ይበልጥ ይከሰትልናል።

ፀሀፊው ኤሪክ አርተር (ጆርጅ ኦርዌል) ይህችን ዓለም የተሰናበተው ከዛሬ 60 ዓመት በፊት ቢሆንም፤ የዛሬውን የሚነግረን እንጂ የትናንቱን የሚያስታውሰን አይመስልም። የሁልጊዜም ተወዳጅ እና ተነባቢ መፅሀፍ ቢሆንም፤ ከምን ጊዜውም በላይ ይበልጥ ወቅታዊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። መስፍን ደግሞ ወደ አማርኛ ሲመልሰው ለተነባቢነቱ ብዙ እንደተጨነቀበት ያስታውቃል፤ ተሳክቶለታልም።

ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና
የኢትኦጵ ጋዜጣና መፅሄት አዛታሚ
የፔን ዩ ኤስ ኤ 2010 ተሸላሚ

********* | *********

መስፍን ማሞ ተሰማ በቋጠሮ ድህረ ገጽ ላይ "መልዕክተ አራዳ" በተሰኘው ቋሚ ዓምድ ሥር ባቀረባቸው በርካታ መጣጥፎቹ የብዕሩን አቅም አስመስክሯል። በአጫጭርና ምናብ ፈጠር ሥራዎቹ የሚታወቀው መስፍን ፦ ዛሬ ደግሞ **“አኒማል ፋርም”** የተሰኘውን **የጆርጅ ኦርዌል** ድንቅና **"ዘመን ተሻጋሪ"** መጽሃፍ **" የእንስሳት አብዮት"** በሚል ተስማሚ ርዕስ ወደ አማርኛ መልሶ፤ እንሆ በረከት ብሎናል። እኛም በረከት ለብዕርህ እንለው ዘንድ ይገባል ።

በሥነ-ጽሁፍ ክህሎቱ በመታገዝ መስፍን የትርጉም ሥራውን ኢትዮጵያዊው ተደራሲ ሊረዳውና ሊያጣጥመው በሚችል መልክ አቅርቦታል ። የወግ ጥረቃ ችሎታው ታሪኩ ወንዝ አፈራሽ እስኪመስለን ድረስ አገረኛ ቃና ሰጥቶታል። መጽሃፉን እያነበብኩ ሳይታወቀኝ በታሪኩ ውስጥ ያሉ እንስሳትን ገጸ ባህሪ ሊተኩ የሚችሉ ሰዎች ከዘመኑ ...መካከል ሲያፈላልግ እራሴን አግኝቼዋለሁ። ...የሚገርመው ደግሞ ተተኪዎቹ መገኘታቸው ነው። " መተካካት ... ! "

ከ65 ዓመታት በፊት የተፈጠሩ ባለ 4 እግር እንስሳትን ገጸ ባህሪ የሚተኩ ሕያው ሰዎች ዛሬ መገኘታቸው የጆርጅ ኦርዌልን ሥራ “ዘመን ተሻጋሪ” አሰኝቶታል። ተርጓሚው መስፍንም ዘመን ተሻጋሪውን ሥራ ወንዝ አሻግሮ አገራዊ መዓዛ ሰጥቶታልና ምስጋና ይገባዋል።

ጋዜጠኛ
ሳምሶን አስፋው
የቋጠሮ ድህረ ገጽ አዘጋጅ

# መቅድም

## ጆርጅ ኦርዌል - ምጥን ታሪክ

ኤሪክ አርትር ብሌር ወይም በብእር ስሙ ጆርጅ ኦርዌል እንግሊዛዊ ሲሆን በ1903 (እአአ) ህንድ ውስጥ ተወለደ። አባቱ በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥሮ ይሰራ ነበር። ቤተሰቦቹ በ1907 ወደ እንግሊዝ ተጓዙ። በ1917 ኦርዌል ኢተን (Eton) ኮሌጅ ገባ። በዚያም ለተለያዩ የኮሌጁ መፅሄቶች ፅሁፍ ያቀርብ ነበር። ከ1922 እስከ 1927 የህንድ ኢምፔሪያል ፖሊስ አባል በመሆን በበርማ አገለገለ። ይህ ግዳጅ በሰጠው ልምድ ተመርኩዞ በ1934 *"Burmese Days"* የተሰኘውን የመጀመሪያውን ልቦለድ ፃፈ። በዚህ መኻል ኦርዌል ለአያሌ አመታት በድህነት ማቋል። ወደ እንግሊዝ ከመመለሱ በፊት ለሁለት አመታት በፓሪስ ኖሯል። በግል አስተማሪነት፣ በት/ቤት መምህርነት፣ በመፃህፍት መደብር ውስጥ በረዳትነት፣ እና ለተለያዩ ጋዜጦች መጣጥፎችን እና አስተያየቶችን በማበርከት ሰርቷል። *"Down and Out in Paris and London"* የሚለው መፅሀፉ በ1933 ታተመ።

በ1936 በላንክሻየር እና ዮርክሻየር ክልሎች ውስጥ ስለሰፈነው መጠነ ሰፊ ስራ አጥነት እንዲያጠና ቪክቶር ጎላንዝ በተባለ ባለ ስልጣን ተላከ። *"The Road to Wigan Pier"* (1937) የሚለው መፅሀፉ በዛ ስላየው ጉስቁልና የሚገልፅ ስሜት ቆንጣጭ መፅሀፍ ነው። በ1936 መጨረሻ ኦርዌል ከሪፓብሊካኖች ጎን ለመዋጋት ወደ ስፔን ዘመተ። በጦርነቱም ቆሰለ። *"Homage to Catalonia"* የሚለው ድርሰቱ የእርስ በርስ ጦርነቱን የሚያሳይ ነው። በ1938 ክፉኛ በመታመሙ ፈውስ አልባ ህሙማን ከሚታከሙበት ጣቢያ ገባ። ከዚህ በኋላ ሙሉ ለሙሉ ከበሽታው አልዳነም ነበር። ለስድስት ወራት ሞሮኮ ተሻግሮ ኖረ። እዛም "Coming Up for Air" የተባለውን ድርሰቱን ፃፈ። በሁለተኛው የአለም ጦርነት በሆም ጋርድነት ሲያገለግል ለቢቢሲ የዜና አውታርም ይዘግብ ነበር።

ከ1941 እስከ 1943 በምስራቅ ግንባር ተሳትፏል። "ትሪቢዩን" ለተባለው ጋዜጣ በዋና አርታኢነት ከማገልገሉም በተጨማሪ የፖለቲካ እና የስነፅሁፍ አስተያየቶችንም በቋሚነት ያቀርብ ነበር። ለ"ኦብዘርቨር" እና ለ"ማንቸስተር ኒውስ"ም የተለያዩ ፅሁፎችን አበርክቷል። ልዩ የሆነው የፖለቲካ ምፀት ድርሰቱ *የ እንስሳት አብዮት (Animal Farm)* በ1945 ታተመ።

ኦርዌል *የእንስሳት አብዮትን* ፅፎ ከጨረሰ በኋላ ግን ለማሳተም ፍዳውን አይቷል። አራት የታወቁ የእንግሊዝ ማተሚያ ቤቶች መፅሀፉን ለማተም ፈቃደኞች ሳይሆኑ ቀርተዋል። ለዚህም ዐብይ ምክንያቱ የእንግሊዝ ማስታወቂያ መስሪያ ቤት የመፅሀፉን መታተም ይቃወም ስለነበር ከአሳታሚ ድርጅቶቹ ጋር ባደረገው ውል መሰረት ነበር።

ቀደምት የሆኑትን የኦርዌልን ስራዎች በማሳተም ረገድ ወኪሉ የነበረው Gollancz *የእንስሳት አብዮትን* ለማተም ከተረከበ በኋላ ከማስታወቂያ መስሪያ ቤት ጋር ተነጋግሮ መፅሀፉን እንደማያትም ለኦርዌል አሳውቆታል።

ታዋቂው ገጣሚ T.S. Elliot ዳይሬክተር የነበረበት Faber and Faber የተሰኘው አሳታሚ ድርጅትም *የእንስሳት አብዮትን* አጣጥሎ ከህትመት አግዶታል።

*የእንግሊዝ ማስታወቂያ መስሪያ ቤት የኦርዌል የእንስሳት አብዮት /አኒማል ፋርም/* እንዳይታተም ተፅእኖ ያደርግ የነበረበት ዋናው ምክንያት መፅሀፉ የሶቪየት ህብረትን መንግስታዊ አስተዳደር ይዘትና አምባገነን መሪዎቹን (ስታሊንን እና ተከታየዮቹን) በእሳሞች ተምሳሌነት (ሲምቦሊዝም) በማጋለጥ የቀረበ በመሆኑ የመጽሀፉ መታተም እንግሊዝና አሜሪካ በወቅቱ ከሩሲያ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አደጋ ላይ ይጥለዋል በሚል ፍርሃቻ ነበር። ጆርጅ ኦርዌል የእንግሊዝ መንግስት ያደረገበትን ጫና በመቃወም የተለያዩ አቤቱታዎችን አቅርቧል።

ይሁንና በ1945 Secker and Warburg የተባለው አሳታሚ ድርጅት *የእንስሳት አብዮትን /አኒማል ፋርም/* የመጀመሪያ እትም በማውጣት ከህዝብ እጅ እንዲገባ አድርጓል።

በ1996 የ'ታይም' መፅሄት *የእንስሳት አብዮትን* የምእራቡ አልም ታላላቅ መፅሀፍት ከሚባሉት ምድብ ውስጥ አስቀምጦታል። እንዲሁም የሃያኛው ክፍለ ዘመን አንድ መቶ ምርጥ የስነ ፅሁፍ ስራዎች ከተባሉት መካከል በ31ኛ እርከን ላይ የሚገኘው *የእንስሳት አብዮት /አኒማል ፋርም/* ነው።

በ1995 በ"ፔንጉዩን" እና በ'W H Smith' የመፃህፍት አሳታሚዎች *የእንስሳት አብዮት* የምእተ አመቱ ታላቅ ተነባቢ መፅሀፍ የሚል ሽልማትን አገኘ። *"Animal Farm"* እና *"Nineteen Eight-Four"* (በ1949 ነበር የታተመው) የተባሉት መፃህፍት ጆርጅ ኦርዌልን በአለም ዝነኛ አደረጉት።

ጆርጅ ኦርዌል በ1950 ሎንዶን ውስጥ አረፈ። ህይወቱ ከማለፉ ጥቂት ቀናት አስቀድሞ ዴዝሞንድ ማክካርቲ የተባለ ወዳጁ በላከለት መልእክት "በእንግልዝ ስነ ፅሁፍ ውስጥ ወደር የሌለው አስተዋፅኦ አበርክተሃል። ... ከአንተ ትውልድ ለዘላለም ከሚታወሱት ጥቂቶቹ አንዱ ነህ።" ብሎ ነበር።

# መግቢያ

***የእንስሳት አብዮት*** ለኦርዌል 'አኒማል ፋርም' መፅሀፍ የአማርኛው ትርጉም መጠሪያ የተሰጠ **ርዕስ** ነው።

ርዕሱን የመረጥኩበት አብይ ምክንያት የመፅሀፉን **ይዘት** ፍንትው አድርጎ በማሳየትና ለ'አኒማል ፋርም' '*የእንስሳ እርሻ*' ከሚለው የቃል በቃል ፍቺ ይልቅ **'የ እንስሳት አብዮት'** የሚለው ውርስ ትርጉም ለኢትዮጵያዊ አንባቢ ይበልጥ ስሜት ይሰጣል በማለት ያመንኩበት በመሆኑ ነው።

*የእንስሳት አብዮት* ጆርጅ ኦርዌል በሩሲያ አብዮት ውስጥ የታዘበውንና አብዮቱ በህዝብ ላይ ያስከተለውን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ህይወት ድቀት ምፀታዊ /ሳቲሪካል/ በሆነ አቀራረብ ያጋለጠበት ስራ ነው።

*የእንስሳት አብዮት* ፅንሰ ሀሳብ /ጭብጥ/ በሰው ልጆች አስከፊ የጭቆና አገዛዝ የተማረሩ እንስሳት ከረሀብ፣ ከድህነት፣ ከብዝበዛ፣ ከኢ-እንስሳዊ አስተዳደር ነፃ ለመውጣት እና ራሳቸውን በራሳቸው ለመምራት በገገርዎቻቸው ላይ ማመፃቸውንና ስር ነቀል ለውጥ ማድረጋቸውን ብቻ ሳይሆን አመፁ /አብዮቱ/ በህይወታቸው ላይ ያስከተለውን 'ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ' ለውጥ ጭምር ተምሳሌያዊ /ሲምቦሊክ/ በሆነ ገፀ ባህሪያትና የታሪክ ክስተቶች አዋቅሮ የሚያትት ነው።

*የእንስሳት አብዮት* ጥልቀትና ምጥቀት ያለው አመራማሪና ህሊናን ሞጋች መፅሀፍ በመሆኑ በርካታ የስነ ህብረተሰብ፣ የስነ ፖለቲካና የስነ ፅሁፍ ምሁራን አያሌ ጥናታዊ ፅሁፎችን ያቀረቡበትና በማቅረብም ላይ ያሉበት ታላቅ መፅሀፍ ሆኖ ይገኛል። በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ከቋንቋና ስነ ፅሁፍ ምሁራን መካከል *በእንስሳት አብዮት* ላይ በሚያቀርቡት የምርምር ፅሁፍ /ቴሲስ/ አማካይነት የፒኤች ዲ (ዶክትሬት ኦፍ ፊሎዞፊ) ድግሪያቸውን ያገኙበታል።

እርግጥ ነው እንዲህ ያለን ጥልቅ መፅሀፍ ይዘቱንና ውበቱን ጠብቆ ከተፃፈበት ቋንቋ ውጪ መተርጎምና ለህዝብ ለማቅረብ ብርቱ ጥንቃቄን ማድረግና ሳይታክቱ ደጋግሞ የእርምት ስራ መስራትን ይጠይቃል።

በዚህ የትርጉም ስራ በተቻለ መጠን የኦርዌልን የአፃፃፍ ስልት ከነይዘቱ ለመጠበቅ ጥረት ተደርጓል። አልፎ፣ አልፎ ግን ረጃጅም አንቀፆች መልእክታቸውን ሳያዛንፉ የአንባቢን አይን በማያፈዙ መንገድ በአዳዲስ አንቀፆች ተከፋፍለዋል። ይህ አከፋፈል በትርጉሙ ይዘት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ምንም የለም፣ የአንባቢን እይታ ከመማረክና የመልእክቱን ግንዛቤ ከማመቻቸት በቀር።

ኦርዌል መፅሀፉን 'የእንስሳ እርሻ' (አኒማል ፋርም) ብሎ የሰየመው እንስሳቱ ከአመፃቸው በኋላ ለእርሻው ጣቢያ በሰጡት ስም ሲሆን በውስጥ ገፆች ውስጥ ይህ

የኦርዌል ስያሜና አጠቃቀም የቃል በቃል ትርጉሙን ሳይለወጥ እንደተጠበቀ ይገኛል።

ከዚህ በተጨማሪ ኦርዌል *መፅሀፉን* በአስር ምእራፋት ሲከፋፍል ለየምእራፉ መለያ *ያደረገው* ቁጥሮችን ነው። (ምእራፍ አንድ፣ ሁለት፣ ወዘተ)። ይሁንና በዚህ ትርጉም ውስጥ እያንዳንዱ ምእራፍ **ከሚያጠነጥንበት ጭብጥ** በመነሳት ለየምእራፉ ተገቢ ናቸው ብዬ ያመንኩባቸውን አርእስቶች ሰጥቻለሁ። ይህም ለመልእክቱ ማጠናከሪያን ለየምዕራፉ ደግሞ ተጨማሪ ቃናን ይፈጥራል በሚል።

*በእንስሳት አብዬት* 'መንግስት' ውስጥ ከሚገኙት ገፀ ባህሪያት መካከል ከገሃዱ አለም አንፃር ያላቸውን ተምሳሌነት /ሲምቦሊዝም/ ለዚህ የትርጉም ስራ አንባቢያን ግንዛቤ መንደርደሪያ ለማድረግ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ጨለፍ አድርገን እንመልከት።

**አዛውንቱ ሜዠር**፣ ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለእኩልነትና ለመልካም አስተዳደር ከ አድማስ የዘለቀ ራዕይ ነበረው። በአቶ ጆንስ እርሻ ጣቢያ ለአብዮቱ /**እመፁ**/ መቀስቀስ ለእንስሳቱ የስነ ልቡና እና የርዕዮተ ዓለም ትጥቅ የሰጣቸው አዛውንቱ ሜዠር ነበር።

አያሌ *የእንስሳት አብዮትን* የተነተኑ የስነ ህብረተሰብ፣ ስነ ፖለቲካ እና ስነ ፅሁፍ ምሁራን አዛውንቱ ሜዠር በገሀዱ ዓለም ውስጥ የነበረውን የኮሚኒስት ማኒፌስቶ እና የዳስ ካፒታል ፀሀፊን ኢኮኖሚስቱንና ፈላስፋውን /ፊሎዘፈሩን/ ኮሚኒስት ካርል ማርክስን ይወክላል ወይም 'ሲምቦላይዝ' ያደርጋል ይላሉ። ሌሎች ደግሞ አዛውንቱ ሜዠር ማርክስን እና ሌኒንን በማጣመር የቀረበ ተምሳሌ ነው ብለውም ፅፈዋል።

ካርል ማርክስ በህይወት እያለ የዓለም ላብአደሮች ሁሉ እንዲያምፁና በካፒታሊስት ጨቋኞች ላይ እንዲነሱ ሲያስተምር ቢኖርም አብዮት ፈንድቶ ሰራተኛው ህዝብ ስልጣን ይዞ ሳያይ ህይወቱ አልፏል። አዛውንቱ ሜዠርም እንስሳቱ ***ለአመፅ*** እንዲነሳሱ ቢያስተምራቸውም ***አመፅ*** መነሳቱን ሳያይ ነበር የሞተው።

**ስኖውቦል**፣ በአቶ ጆንስና ባልደረቦቹ ላይ የተደረገውን ***አመፅ*** ከመሩት መካከል አንዱና ዋናው ሲሆን የአዛውንቱ ሜዠርን ትምህርት አስፋፍቶ የእንስሳዊነትን /አኒማሊዝም/ መርሆ የቀመረ ብሩህ አእምሮ እና ጠንካራ የስራ ባህሪ የነበረው አብዮተኛ ነበር።

በርካታ *የእንስሳት አብዮት* ተንታኝ ምሁራን ስኖውቦልን ከሩሲያው የቦልሼቪክ ፓርቲ አባል ከሊዮን ትሮትስኪ ጋር ያዛምዱታል። ትሮትስኪ ከሌኒን ጋር የቦልሼኮችን አብዮት በሩሲያ ያቀጣጠለ አብዮተኛ ምሁር ነበር።

ትሮትስኪ ከሌኒን ሞት በኋላ ስልጣን 'በኩዴታ' የወሰደውን የስታሊንን አስተዳደር በመንቀፉ ከኮሚኒስት ፓርቲው ተባርሮ ከሀገሩ ከሩሲያ በመሰደድ ሲኖር ስታሊን በላካቸው ገዳዮች ሜክሲኮ ውስጥ ህይወቱ አልፏል።

**ናፖሊዮን**፣ ራሱን ለፕሬዚዳንትነት ብቸኛው እጩ አድርጎ ያቀረበ *የእንስሳ እርሻ* ፍፁም አምባገነን መሪ ነበር። **ከአመፁ** ድል በኋላ ናፖሊዮን በመሰረተው አስተዳደር /መንግስት/ እንስሳቱ ከዚህ በፊት በዘመነ ጆንስ እንኳን አይተውት በማያውቁት ሁኔታ በምዝበራና በጭካኔ የተሞላ የግፍ አገዛዝ ውስጥ እንዲማቅቁ አድርጓቸዋል።

*በእንስሳት አብዮት* መፅሀፍ ውስጥ ናፖሊዮን የሩሲያን አምባገነን መሪ ጆሴፍ ስታሊንን ያንፀባርቃል በማለት የተነተኑ የስነ ህብረተሰብ፣ ስነ ፖለቲካና ስነ ፅሁፍ ጠቢባን ጥቂት አይደሉም።

**ስኩለር**፤ ኦርዌል በእንስሳት አብዮት ውስጥ ከቀረፃቸው እጅግ ውስብስ፤ አመራማሪና አስገራሚ ገፀ ባህሪያት መካከል አንዱ ሆኖ ይገኛል። **ከአመፁ** መሪዎች አንዱ የሆነው ስኩለር 'ድንጋይ ዳቦ ነው' ብሎ የማሳመን ችሎታ ነበረው። ብሩህ አ እምሮ ያለው ፈጣን ተናጋሪና እጅግ ሎሌ ሲሆን የሌሎችን ሀሳብ (ለመልካም ግብ ሳይሆን ለማደናገሪያ ወይም እውነትን ለማድበስበሻ) የማስለወጥ ሀይሉ ከአነጋገር ስልቱ ጋር ተዳምሮ ወደር የማይገኝለት 'አጭበርባሪ' ፖለቲከኛ አድርጎታል።

በርካታ ፀሀፍት ስኩለርን ከሶቪየት ህብረቱ የስታሊን ፕሮፓጋንዲስት ሞሎቶቭ፤ አንዳንዶቹም ከኮሚኒስት ፓርቲው አፈ-ልሳን 'ፕራቭዳ' እና እንዲሁም ከናዚ ፓርቲ የፕሮፓጋናዳ ክፍል ሃላፊ ዶ/ር ጆሴፍ ጎብልስ ጋር አነፃፅረው አቅርበውታል።

*የእንስሳት አብዮት* በሌሎች በርካታ ገፀ ባህሪያትም የተሞላ መፅሀፍ ሲሆን ለምሳሌ እጅግ አመራማሪና እንቆቅልሽ ከሆኑት መካከል ሽማግሌው ቤንጃሚን፤ ሰባኪው ሙሴ፤ ክሎቨር፤ ቦክሰር፤ የምስጢር ፖሊሶቹ፤ አቶ ፒልኪንግተን ወዘተርፈ በገሀዱ ዓለም የምናውቀው ህይወት ነፀብራቆች ሆነው ይገኛሉ።

ስለ *እንስሳት አብዮት* መፅሀፍ ይዘትና ገፀ ባህሪያት ይህንን ያህል ካስተዋወቅሁ በኋላ **የእንስሳት አብዮት ወቅታዊ ፋይዳ ምን ይሆን?** በሚለው ዙሪያ አንዳንድ ነጥቦችን መሰንዘር አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

መፅሀፉ በታተመበት ዘመንና ወቅት አያሌ ትንታኔዎችን የሰጡት ጠበብት መፅሀፉን የመረመሩት በወቅቱ ከነበረው የሶሺያሊስት ስነ መንግስታዊ እና ስነ ፖለቲካዊ አወቃቀር ርዕዮትና አስተዳደር ላይ ተንተርሰው ነበር።

እነሆ ቀዝቃዛው ጦርነት (Cold war) ካበቃ እና ዘመነ - ኮምዩኒዝምም በምናውቀው መልኩ ካከተመ አመታት ተቆጥረዋል። ይሁንና ምናልባትም ከዘመነ - ኮምዩኒዝም በላቀ ደረጃ፤ በዴሞክራሲ እና በህዝብ ድምፅ የበላይነት ስም በሚመፃደቁ አምባገነኖች አገዛዝ ስር በመማቀቅ ላይ የሚገኙት ሀገራት ቁጥር ግን እያሻቀበ በመሄድ ላይ ይገኛል።

ለዚህም ነው በዚህ ዘመንና ትውልድ ያሉት የስነ ፖለቲካ፤ ስነ ህብረተሰብና ስነ ፅሁፍ ጠበብት **የእንስሳት አብዮት** ጭብጥና አንደምታ (ኢምፕሊኬሽን) ወይም ተምሳሌነት /ሲምቦሊዝም/ ዛሬም ቢሆን በአፍሪካ፤ በመካከለኛው ምስራቅ፤ በሩቅ ምስራቅ፤ በምስራቅ አውሮፓና በደቡብ አሜሪካ ሀገራት ውስጥ *በዴሞክራሲ እና በነፃ ምርጫ ስም የሚመፃደቁትን ዘረኛና አምባገነን መንግስታትን የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የማህበራዊ አስተዳደር ብልሹነትን፤ የተቀነባበረ መንግስታዊ የሀገርና የህዝብ ሀብት ንብረት ዝርፊያንና ሙስናን፤ በህዝቦች ላይ እየተፈፀመ ያለውን ኢሰብአዊ ግፍና በደልን ወዘተርፈ እንደ መስታወት ቁልጭ አድርጎ በማሳየት ሀይሉ ዘመን ያልገደበው፤ ድንበር ያልከለለው ዓለም አቀፋዊ መፅሀፍ መሆኑን በአፅንዖት የሚገልፁት።*

እነሆ **የእንስሳት አብዮት** ትርጉም ለኢትዮጵያዊያን አንባቢያን በዚህ ዘመንና በዚህ ወቅት የቀረበበትም ዐብይ ምክንያት ይኸው ነው - ድንበር ያልከለለው፤ ዘመን ያልገደበው፤ እውነታን አንፀባራቂ መሆኑ!!

*መፅሀፉን በጥሞና አንብቦና መርምሮ መልእክቱን በመረዳት ወቅታዊ ፋይዳውን ከምንገኝበት እውነታ ጋር ማገናዘብ ግን የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አንባቢ የቤት ስራ ይሆናል።*

በመጨረሻም፤

ይዋል ይደር እንጂ፣ በህዝብ ደም እና እንባ የሚሳለቁ አምባገነኖች ሁሉ **በህዝብ አመፅ** (ቱኒዚያንና ግብፅን በአስረጅነት ይጠቅሷል) ተገርስሰው ህዝባዊ ፍርድ የሚቀበሉበት ጊዜ ፀሀይ በምስራቅ እንደ መውጣቷ ያለ አይቀሬ የተፈጥሮ ህግ ነው!!

እነሆ '*የእንስሳት አብዮት*' . . .

መልካም ንባብ!

መስፍን ማሞ ተሰማ
ሚያዚያ 2003 ዓ/ም (ኤፕሪል 2011)
ሲድኒ - አውስትራሊያ

# የእንስሳት አብዮት

## ምእራፍ አንድ

### የአዛውንቱ ሜዠር ህልም

አቶ ጆንስ የማኖር እርሻ (Manor Farm) ባለቤት ሲመሽ የዶሮዎቹን ቤት ቢዘጋጋም ጥንብዝ ብሎ ሰክሮ ስለነበር ግን መሹለኪያዎቻቸውንም መዝጋቱን ዘነጋ። በእጁ ያንጠለጠለው ፋኖስ ግራና ቀኝ እየደነሰ በሚረጨው ብርሃን እየተመራ ሜዳውን አቋርጦ ከቤቱ ጓሮ በር ሲደርስ ቧት ጫማውን አውልቆ ገባ። ኩሽና ከሚገኘው የቢራ ማጠራቀሚያ የመጨረሻውን ብርጭቆ ቢራ ቀድቶ እየጠጣ ወ/ሮ ጆንስ ወደምታንኮራፋበት መኝታው ሄደ።

የመኝታ ቤቱ መብራት እንደጠፋም በእርሻው ውስጥ ባሉት ህንፃዎች ሁሉ ሹክሹክታና ጉምጉምታ ሆነ። አዛውንቱ ሜዠር፤ ያልተኮላሸው ነጩ አሳማ፤ ባለፈው ምሽት እንግዳ የሆነ ህልም ማየቱንና ህልሙንም በእርሻው ጣቢያ ለሚኖሩ እንስሳት ሁሉ ማካፈል እንደሚፈልግ ቀኑን ሙሉ በመካከላቸው ሲወራ ውሎ ነበር። በስምምነታቸውም መሰረት አቶ ጆንስ ጥልቅ እንቅልፍ ሲወስደው በትልቁ መጋዘን ይሰባሰባሉ። አዛውንቱ ሜዠር (ሁሌም የሚጠራው እንዲህ ቢሆንም በይፋ የወጣለት ስም ግን የዊሊንግደኑ ቆንጆ የሚል ነበር) በእርሻው ጣቢያ በሚኖሩት እንስሳት ሁሉ የተከበረ በመሆኑ የአንድ ሰአት እንቅልፍ አጥተው የሚናገረውን ለመስማት ሁሉም እንስሳት ዝግጁዎች ነበሩ።

ከትልቁ መጋዘን በአንደኛው ጥግ ከመሬት ትንሽ ከፍ ባለ መድረክ ቢጤ በተጎዘጎዘው የደረቅ ሳር ፍራሽ ላይ ከምሶሶው አንጓ በተንጠለጠለው የሚበራ ፋኖስ ስር ሜዠር ይጠብቃቸዋል። እድሜው አስራ ሁለት አመት ነበር። ምንም እንኳን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰውነቱ ቢወፍርምና ክራንቻ ጥርሶቹ ተከርክመው ባያውቁም ሜዠር የአዋቂነትንና የአስተዋይነትን ገፅታ የተላበሰ አሳማ ነበር። ወዲያው ሌሎች እንስሳት እየመጡ እንደጎራቸው የተመቻቸ ስፍራ መያዝ ጀመሩ። አስቀድመው የደረሱት ሶስቱ ውሾች ነበሩ። ብሉቤል፤ ጄሲ እና ፒንቸር። ቀጥሎ አሳሞቹ መጡ። ከተጎዘጎዘው ሳር ከመድረኩ ፊት ለፊትም ተቀመጡ። ዶሮዎቹ በየመስኮቶቹ ደፎች ላይ ቁጢጥ አሉ። ርግቦች ክፈፎች ላይ ሰፈሩ። በጎቹና ላሞቹ ከአሳሞቹ ጀርባ ጋደም ብለው ማመንዠክ ያዙ። ባለ ሁለት ጎማ ጋሪ ጎታቾቹ ፈረሶች ቦክሰር እና ክሎቨር ተከታትለው ደረሱ። ፀጉራማ ግዙፍ ኮቴዎቻቸው በተነጠፈው ድርቆሽ ሳር ላይ ያሉትን ደቃቃ እንስሳት እንዳይረግጡ በጥንቃቄ እየተራመዱ።

ክሎቨር በመካከለኛ እድሜ ላይ የምትገኝ፤ አራተኛውን ልጇን ከወለደች በኋላ የቀድሞ አካላዊ ቅርፅዋን ከቶም መመለስ ያልቻለች ደንዳና ሰውነት ያላት የጋማ ከብት ናት። ቦክሰር

ግዙፍ እንስሳ ነበር። አስራ ስምንት ክንድ ቁመት ያለውና ጥንካሬውም የሁለት ፈረሶችን የሚያክል። አፍንጫውን ሰንጥቆት የሚያልፈው ነጭ መስመር የሞኝ ፊት ሰጥቶታል። እንደውም ቦክሰር በብልህነት አይታማም። ይልቁንም የሚታወቀው ወላዋይ ባልሆነው ባህሪውና በጠንካራ ሰራተኝነቱ ሁለንተናዊ ከበሬታን ያገኘ በመሆኑ እንጂ። ከፈረሶቹ ቀጥሎ የመጡት ነጯ ፍየል ሙሬል እና ቤንጃሚን አህያው ነበሩ።

ቤንጃሚን በእርሻው ጣቢያ ካሉት እንስሳት ሁሉ ሽማግሌውና ስሜቱ የማይታወቅ ነበር። እጅግ አልፎ አልፎ ብቻ ነበር የሚናገረው። ከተናገረም፤ ለምፀት። ለምሳሌ፤ እግዚአብሄር ጭራ የሰጠኝ ዝንቦችን እንዳባርርበት ነበር፤ ግን በቅርቡ ጭራም አይኖረኝ ዝንቦችም አይወሩኝ - ይላል። በእርሻው ጣቢያ ከሚገኙት እንስሳት መካከል ስቆ የማያውቅ ብቸኛው ፍጡር። ስለምን ስቀህ አታውቅም? ተብሎ ሲጠየቅ፤ የሚያስቅ ነገር ከቶም አጋጥሞኝ አላውቅም - ይላል።
ይሁንና በግልፅ ባያምንም ለቦክሰር ፍፁም ታማኝ ነበር። ከትንሹ የፍራፍሬ እርሻ ማዶ ከሚገኘው መለስተኛ የግጦሽ መስክ ዘወትር እሁድ ከቦክሰር ጋር ጎን ለጎን ሆነው ሳይነጋገሩ በዝምታ ሲግጡ ይውላሉ።

ሁለቱ ፈረሶች ጎኖቻቸውን እንዳሳረፉ እናታቸው የጠፋችባቸው ጫጩት ዳክየዎች ምናምን እየለቃቀሙና በሌሎች እንዳይረጋገጡ ግራና ቀኝ እየቃኙ፤ ማረፊያ የሚሆን ምቹ ቦታም እየማተሩ በአጀብ ሆነው ወደ መጋዘኑ ገቡ። ክሎቨር በፊት እግሮቿ እንደ ቀለበት በከለለችላቸው ክብ ውስጥ ገብተው ከተደላደሉ በኋላ እንቅልፋቸውን ይለጥጡ ጀመር። የአቶ ጆንስን መጓጓዣ ጋሪ የምትጎትተው ቂላቂልና ቆንጆዋ ነጭ በቅሎ፤ ሞሊ፤ ስኳሯን በቁንጥ እያላመጠች መጣች። ከፊት ለፊት ቦታ ያዘች። ነጩን ጭራዋን እየነሰነሰች፤ እላዩ ላይ የታሰረው ቀይ ሪቫን እንዲታይላት ትሽኮረመማለች። በመጨረሻ የመጣችው ድመት ነበረች። ዙሪያ ገባዋን ተመለከተች፤ የሞቀ ስፍራ ለማግኘት። ቀጥሎም በቦክሰርና በክሎቨር መሃል ተወሸቀች። ተደላድላ ተኝታ ማንኳረሯን ተያያዘችው። ከሜዠር ንግግር አንዲትም ቃል እንኳን አልሰማችም።

እነሆ ሁሉም እንስሳት በስብሰባው ቦታ ተገኝተዋል፤ ከጓሮው በር የወፍ ማደሪያ ስፍራ ላይ ከሚተኛው ከለማዳው ጥቁሩ አሞራ ሙሴ በስተቀር። እንስሳቱ ሁሉ ቦታ ቦታቸውን ይዘው በጉግት በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን የተረዳው ሜዠር ጉሮሮውን ጠራርጎ ንግግሩን ጀመረ።

“ጓዶች፤ ትላንትና ማታ ስላየሁት እንግዳ የሆነ ህልም መቼም ሁላችሁም ሰምታችኋል። ህልሙን ዘግየት ብዬ እመለስበታለሁ። መጀመሪያ የምነግራችሁ ሌላ ጉዳይ አለኝ። እንደምገምተው ከሆነ፤ ጓዶች፤ በመካከላችሁ የምቆይበት ጊዜ እየተመናመነ ነው። ከመሞቴ በፊት በተመክሮ ያገኘሁትን እውቀት ለእናንተ የማስተላለፍ ተልእኮ ግዴታ አለብኝ። ረዥም እድሜ ኖሬያለሁ። በማደሪያዬ ውስጥ ሆኜ የማሰላስልበት ብዙ ጊዜ ነበረኝ። እንደማምንበትም ከሆነ እንደማንኛውም በዚህች ምድር ላይ በህይወት እንደሚገኝ እንስሳ ሁሉ ስለ ህይወት ምንነት ማለፊያ ግንዛቤ አለኝ። ልነግራችሁ የምፈልገውም ስለዚሁ ጉዳይ ነው።

“እናም ጓዶች፤ ይህ የእኛ ህይወት ትርጉሙ ምንድን ነው? ሀቁን እንጋፈጠው። ህይወታችን ጎስቋላ፤ አድካሚና እድሜያችንም አጭር ነው። ተወልደናል። ግን የሚመግቡን ነፍስና ስጋችንን ለማቆየት የሚችል ያህል ብቻ ነው። አቅሙ እስካለን፤ የመጨረሻው ወዛችን እንጥፍጣፊ ድረስ እንድንሰራ እንገደዳለን። ጉልበታችን ሲዳከምና የመስራት አቅም ስናጣ አሰቃቂ በሆነ ጭካኔ እንታረዳለን። በ እንግሊዝ ሀገር የሚኖር የትኛውም እንስሳ ከአንድ አመት እድሜው በኋላ ደስታና መዝናናት ምን እንደሆን አያውቅም። የትኛውም እንስሳ

እንግሊዝ ውስጥ ነፃነት የለውም። የእንስሳ ህይወት የባርነትና የጉስቁልና ነው። ይህ ነው ገሀዱ እውነት።

"ታዲያ ይህ የተፈጥሮ ሂደት ደንብ ህግ ሆኖ ነውን? ይህች የምንኖርባት መሬት ፍጡራኗን መመገብና መሰረታዊ ህይወት መለገስ የማትችል ድሃ በመሆኗስ ይሆን? አይደለም ጓዶች። በፍጹ‌ራሽ አይደለም! የእንግሊዝ አፈር ለምለም ነው። አየሯም ግሩም። አሁን በላይዋ ላይ ከሰፈርነው እንስሳትም ቁጥር በላይ በበቂ መመገብ እና በገፍ የማምረት ብቃት ያላት ሀገር ናት። ይህ እኛ የምንኖርበት እርሻ እንኳን ደርዘን ፈረሶችን፣ ሃያ ላሞችን፣ በመቶ የሚቆጠሩ በጎችን፣ ሁሉንም አንደላቆ እና አኩርቶ ማኖር የሚችል ነው። ይህ ግን በዚህ እርሻ ላይ ለምንኖር የማይታሰብ ህልም ሆኗል። ታዲያ ለምን ይሆን በዚህ አስከፊ ህይወት ውስጥ እየማቀቅን የምንገኘው? ምክንያቱም የላባችን አንጡራ ምርት በሙሉ በሰው ልጆች ስለሚሰረቅ ነው። ጓዶች፣ የጉስቁልናችን ሁሉ ምስጢር መልሱ ይህ ነው። በአንድ ቃል፡ ሰው። ሰው ብቸኛው ጠላታችን ነው። ረሀብና ምዝበራን ከስሩ መንግሎ ለመጣል - ሰውን ማስወገድ።

"ሳያመርት የሚያጋብስ ብቸኛው ፍጡር ሰው ነው። ወተት አይታለብም። እንቁላል አይጥልም። ሞፈርና ቀንበር ለመጎተት ደካማ ነው። ጥንቸል አባርሮ ለመያዝ አቅም የለውም። ግን የእንስሳት ሁሉ ጌታ ነው። ወደ ስራ ያሰማራቸዋል። እስትንፋሳቸውን የሚያሰነብት ብቻ ይመግባቸውና የላባቸውን ምርት በሙሉ ሰብስቦ ይወስዳል። የኛ ጉልበት መሬት ያርሳል። አዛባችን ማዳበሪያ ይሆናል። ነገር ግን በላያችን ካለው ቆዳችን ውጪ ምንም ንብረት የለንም።

"እናንት ከፊት ለፊቴ የማያችሁ ላሞች፣ ባሳለፍነው አመትስንት ሺህ ሊትር ወተት ነበር የታለባችሁት? ለጥጃዎቻችሁ ጉልበትና ሰውነት ሊሆናቸው የሚገባው ወተት የት ደረሰ? እያንዳንዱ ጠብታ በሙሉ በጠላቶቻችን ጉሮሮዎች ተንቆርቁሯል። እናንት ዶሮዎች፣ ባሳለፍነው አመት ምን ያህል እንቁላሎች ጣላችሁ? ከእነዚህስ መካከል ስንቶቹ ናቸው የተፈለፈሉት? የተረፉት በሙሉ ለጆንስና ለሰዎቹ ገንዘብ ለማስገኘት ገበያ ወርደው ተቸብችበዋል።

"አንቺስ ክሎቨር፣ በስተርጅና ሊጦሩሽና ሊደግፉሽ ይገባቸው የነበሩት የወለድሻቸው አራቱ ግልገሎች የት አሉ? እያንዳንዳቸው በአንድ አመት እድሜያቸው ተሸጠዋል። መቼም ቢሆን መቼ ከአንዳቸውም ጋር በአይነ ስጋ አትገናኙም። በእርሻ ለመድከምሽና ለአራቱ ግልገሎችሽ ወሮታሽ ምን ሆነ? ነፍስሽን ማሰንበቻ ቀለብና ግርግም?

"ይህ የምንኖረው ጎስቋላ ህይወት የሰጠንን የእድሜ ዘመን እንኳን አጠናቀን እንድንኖረው አልተፈቀደልንም። በበኩሌ አላጉረመርምም። ከታደሉት ጥቂቶቹ መካከል አንዱ ነኝና። ከአራት መቶ በላይ ልጆች ሲኖሩኝ እነሆ እድሜዬም አስራ ሁለት አመት ሆኗል። የአሳማ ተፈጥሮአዊ ህይወት እንዲህ ነውና። ግና የትኛውም እንስሳ በመጨረሻ የጭካኔን ቢላ ማምለጥ አይቻለውም።

"እናንት ከፊት ለፊቴ የተቀመጣችሁ ወጣት አሳሞች፣ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እዚሁ እርሻ ጣቢያ የነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ የጣእር እሪታ የምታሰሙበት ወቅት ይመጣል። ከእንዲህ ያለው መአት ለመታደግ፣ አሳሞች፣ ዶሮዎች፣ በጎች፣ ሁላችንም አንድ መሆን ይኖርብናል። ፈረሶችና ውሾችም እንኳን እጣ ፈንታችሁ ከእኛ የተለየ አይሆንም።

"አንተ ቦክሰር፣ እነዚህ ታላላቅ ጡንቻዎችህ ሃይላቸውን አጥተው የሚሸሹ እለት ጆንስ ሳይውል ሳያድር ለፈረስ አራጆች ይሸጥሃል። እነሱም አንገትህን ቀንጥሰውት ስጋህን ቀቅለው ለቀበሮ ማደኛ ያውሉታል። ውሾችን በተመለከተ ግን ሲያረጁ እና ጥርሳቸው ሲረግፍ ጆንስ አንገታቸው ላይ ጡብ አስሮ ባቅራቢያ ካሉት ኩሬዎች ውስጥ ወስዶ ይደፍቃቸዋል።

"እንግዲህ ጓዶች፣ ይህ በእኛ ህይወት ላይ የተፈጠረው ሰቆቃ ሁሉ መሰረታዊ ምንጩ የሰው ልጆች ለመሆናቸው እንደ ብርሃን ግልጥ አይደለምን? ሰው ብቻ ከተወገደ የድካማችን ፍሬ ሁሉ የራሳችን ይሆናል። በአጭር ጊዜም ሀብታም እና ነፃ ልንሆን እንችላለን። እና እንግዲህ ምን ማድረግ ይኖርብናል? አዎ፣ አቅማችንን ሁሉ አቀናጅተን የሰውን ዘር ለማስወገድ ቀን ተሌት መስራት! ጓዶች፣ ለእናንተ መልእክቴ ይህ ነው፣ **አመፅ**! **አመፁ** መቼ እንደሚነሳ ግን አላውቅም። ምናልባት በሳምንት ወይም በመቶ አመት ጊዜ ውስጥ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይህንን ከስሬ የሚገኘውን ድርቆሽ ሳር እንደማየው ሁሉ፣ በእርግጠኝነት መናገር የምችለው፣ ይፍጠን ወይም ይዘግይ እንጂ ፍትህ እውን ይሆናል። ጓዶች፣ በአነስተኛው የህይወት ዘመናችሁ ሁሉ ውስጥ ግባችሁ ይህ ይሁን። ከሁሉም በላይ ደግሞ ይህንን መልእክት ከእናንተ በኋላ ለሚመጡት ሁሉ አስተላልፉ፡ የነገዎቹ ትውልዶች ትግሉን ተረክበው በድል እስከሚጠናቀቅ ድረስ ይታገሉ ዘንድ።

"አስታውሱ፣ ጓዶች፣ የአላማ ፅናታችሁ መቼም ይሁን መቼ መላላት የለበትም። ምንም አይነት አለመግባባት ከአላመችሁ ሊያስታችሁ አይገባም። ሰውና እንስሳት የጋራ የሆነ ጥቅም አላቸው፣ የአንዱ ብልፅግናም የሌላው ብልፅግና ነው በማለት የሚሰብኩዋችሁን ከቶም አትስሙዋቸው። ሁሉም ሀሰት ነው። ሰው ከራሱ ጥቅም ሌላ የሌሎችን ፍጥረታት ጥቅም አይጠብቅምና። በእኛ በእንስሳት መካከል በትግላችን ውስጥ ፍፁማዊ የሆነ ጓዳዊነት ይስፈን። ሰዎች ሁሉ ጠላቶቻችን ናቸው። እንስሳት ሁሉ ጓዶቻችን።"

እዚህ ላይ ታላቅ ሁካታ ተፈጠረ። ሜዠር በሚናገርበት ወቅት አራት የደለቡ አ ይጦች ከጉድጓዶቻቸው ወጥተው በኋላ አግሮቻቸው ቁጢጥ ብለው ንግግሩን ያዳምጡ ነበር። አይጦቹን የተመለከቱት ውሾች ተፈትልከው ሲወረወሩባቸው አ ይጦቹ በተፈጥሮ ቅልጥፍናቸውና ፍጥነታቸው ወደ ጉድጓዶቻቸው በመወንጨፍ ህይወታቸውን ማትረፍ ቻሉ። ይህን ጊዜ ሜዠር ፀጥታ ይሰፍን ዘንዳ የፊት እግሩን አነሳ።

"ጓዶች" አለ ሜዠር " እልባት ልንሰጠው የሚገባ ጉዳይ አለ። እንደ አይጥና ጥንቸል የመሳሰሉ የዱር እንስሳት ወዳጆቻችን ናቸው ወይስ ጠላቶቻችን? በጉዳዩ ድምፅ እንስጥበት። ለጉባኤው የማቀርበው ጥያቄ ይህ ነው፣ አይጦች ጓዶቻችን ናቸውን?"

እነሆ ድምፅ ተሰጠ። ጠቅላላ ጉባኤው በአብላጫው አይጦችም ጓዶች ናቸው በማለት ወሰነ። ሆኖም አራት ድምፅ የተምታታ ተገኘ። እነሱም የሶስቱ ውሾችና የድመት ነበሩ። በተደረገው ማጣራትም ውሾቹና ድመቲቱ በተቃውሞም በድጋፍም (በሁለት አቅጣጫ) ድምፅ መስጠታቸው ተደረሰበት። ከዚህ በኋላ ሜዠር ንግግሩን ቀጠለ።

"እንግዲህ ብዙም የምናገረው ነገር የለም። ሁሌም ቀዳማዩን ግዳጃችሁን እንድታስታውሱ ነው በድጋሚ የማሳስባችሁ። ለሰው ልጅ እና ለድርጊቱ ጠላትነታችሁ የፀና ይሁን። *በሁለት እግር የሚሄድ ሁሉ ጠላት ነው። በአራት እግር የሚሄድ ወይም ክንፍ ያለው ሁሉ ወዳጅ።* ከሰው ጋር በምናደርገው ፍልሚያ ውስጥ ከቶም ቢሆን የሰው ምግባሩን እንዳትወርሱ። ሰውን ድል ብታደርጉት እንኳን ምግባራቱን አትውረሱ። *ማንኛውም እንስሳ በቤት ውስጥ መኖር፣ ወይም አልጋ ላይ መተኛት፣ ወይም ልብስ መልበስ፣ ወይም አልኮል መጠጣት፣ ወይም ሲጋራ ማጤስ፣ ወይም ገንዘብ መያዝ፣ ወይም መነገድ፣ የለበትም። ማንኛውም የሰው ልጅ*

*ልማዶች በሙሉ ርኩስ ናቸው።* ከምንም ነገር በላይ፣ ***ማንኛውም እንስሳ በሌላ እንስሳ ላይ ጭቆናን ማንሰራፋት የለበትም።*** ደካማ ይሁን ብርቱ፣ ሊቅ ይሁን ተራ፣ ሁላችንም ወንድማማቾች ነን። **ማንኛውም እንስሳ በፍፁም ሌላ እንስሳን መግደል የለበትም። ሁሉም እንስሳት እኩል ናቸው።**

"በመጨረሻም ጓዶች፣ ትላንት ማታ ስላየሁት ህልም ልንገራችሁ። ያየሁት ህልም ጭብጡ፣ የሰው ልጅ ከጠፋ በኋላ ስለምትኖረው አለም ነበር። ታዲያ ይኸውላችሁ፣ ይህ ህልም ለረዥም ጊዜ የረሳሁትን ሌላ ነገር አስታወሰኝ። ከብዙ አመታት በፊት፣ ገና ህፃን አሳማ ሳለሁ፣ እናቴና ሌሎች አሳሚቶች ቅላፄውን እና ከስንኞቹ ውስጥ ደግሞ የመጀመሪያዎቹን ሶስት ቃላት ብቻ የሚያውቁትን የድሮ ዘመን መዝሙር ይዘምሩ እንደነበር አስታወስኩ። ያንን ዜማ በልጅነት ዘመን ልቦናዬ ባውቀውም ቅሉ ከጊዜ በኋላ ግን ከህሊናዬ ወጥቶ ነበር።

"እነሆ ትላንትና ማታ ባየሁት ህልም ውስጥ ተመልሶ መጣ። በዚህ ብቻ አልቆመም። የመዝሙሩን ቃላትም አስታወስኳቸው። አዎን፣ እርግጠኛ ነኝ - የድሮ ዘመን እንስሳት ይዘምሩዋቸው የነበሩ ቃላት፣ ግና ከበርካታ ተከታታይ ትውልዶች ህሊና የጠፉ። ያንን መዝሙር አሁን እዘምርላችኋለሁ፣ ጓዶች። ድምፄ ጎርናና

እድሜዬም የገፋ ቢሆንም እንኳን መዝሙሩን ካስተማርኳችሁ እናንተ ከእኔ በተሻለ ለራሳችሁ ትዘምሩታላችሁ። *"የእንግሊዝ አራዊት"* ይባላል።

አዛውንቱ ሜዠር ጉሮሮውን ጠራርጎ ይዘምር ጀመር። እውነትም እንደተናገረው ድምፁ ጎርናና ቢሆንም ማለፊያ አድርጎ ዘመረው። ዜማው ቀስቃሽነት ነበረው። ቃላቱም እንዲህ ይላሉ፣-

የእንግሊዝ አራዊት፣ የአየርላንድ አራዊት
የየሀገሩ ሁሉ አራዊት
ተሳተፉ የደስታዬን ምንጩን
ስለ መጪው ብሩህ ዘመን።

ይዘገያል ወይ ይፈጥናል፣ ያ ቀን ግን ይመጣል
ጨቋኙ ሰው ይገረሰሳል።
የእንግሊዝ ምርታማ እርሻዎች እንዳሉ
ለአራዊት ብቻ ይሆናሉ።

ይወልቃሉ ከአፍንጫዎቻችን ቀለበቶቹ
ከጫንቃዎቻችንም ላይ መጫኛዎቹ
ልጓምና እና መሰርሰሪያ ለዘላለሙ ይዝጋሉ
ግርፋትም ያበቃል፣ ጅራፎችም ፀጥ ይላሉ።

አዱኛችንም ይሆናል በሽበሽ
ገብስና ስንዴ፣ አጃና ሳር ድርቆሽ
አደይ አበባና ባቄላ የእህል ዘር በሙሉ
ያኔ የኛ ይሆናሉ።
በእንግሊዝ እርሻዎች ፀሀይ ይወጣል

ውሃውም ሁሉ ይፀዳል
የጣፋጭ አየር ሽታ ይነፍሳል
ነፃ በምንወጣበት በዚያች ቀን።
ስለዛ ቀን ሁላችን እንድከም
ፍሬውን ሳናይ እንኳ ብናልፍም።
ላሞችና ፈረሶች፣ ዳክዬና ዶሮዎች
ስለነፃነት ስትሉ፣ ሁላችሁም ጣሩ።

የእንግሊዝ አራዊት፣ የአየርላንድ አራዊት
የሁሉም ሀገራት አራዊት
አድምጡ፣ አሰራጩት ህልሜን
ስለመጪው ብሩህ ዘመን።

ይህ መዝሙር ሲዘመር እንስሳቱን ሁሉ በሀሴት አጦዛቸው። ሜዠር የመጨረሻውን ስንኝ ከመዘመሩ በፊትም ሁሉም እንስሳት ራሳቸውን ችለው ይዘምሩት ገቡ። የመጨረሻ ደደቦች የሚባሉት እንኳን ሳይቀሩ የመዝሙሩን ዜማ እና ጥቂት ቃላትንም ይዘው ነበር። ብልሆቹማ፣ ለምሳሌ አሳሞቹና ውሾቹ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ የመዝሙሩን ሙሉ ስንኞችና ዜማ ሸመደዱ። ከተወሰኑ ልምምዶች በኋላም የእርሻው ጣቢያ በሙሉ 'የእንግሊዝ አራዊት' በሚለው የተቀናጀ ዝማሬ ተናጋ። ላሞች አምቧለሉት። ወሾች አላዘኑተ። በጎች አንጎራጎሩት። ፈረሶች አሽካኩት። ዳክዬዎች ኳክ አሉት። እጅግ ደስተኞች በመሆናቸውም ያለ ማቋረጥ አምስት ጊዜ አከታትለው ዘመሩት። ምናልባትም ሌሊቱን ሙሉ ሲዘምሩ ሊያድሩ ይችሉ ነበር፣ እንዲያቋርጡ ባይገደዱ ኖሮ።

አለመታደል ሆኖ የመዝሙሩ ሁካታ አቶ ጆንስን ቀሰቀሰው። ተስፈንጥሮም ተነሳ፣ በእርሻው ጣቢያ ቀበሮ ለመግባቱ እርግጠኛ ሆኖ። ከመኝታ ቤቱ ባንደኛው ጥግ ሁሌም የሚያቆመውን ጠመንጃውን አፈፍ አድርጎ ስድስት ጥይት ጨለማው ውስጥ ተኮሰ። ቀለሃዎቹ ከመጋዘኑ ግርግዳ ውስጥ ተሰነቀሩ። የእንስሳቱም ስብሰባ በችኮላ ተበተነ። ሁሉም ወደየመኝታቸው ስፍራ ተፈተለኩ። ወፎቹ ወደየጎጆዎቻቸው ተወነጨፉ። እንስሳቱም በየምድባቸው ተጋደሙ። ከመቅፅበትም ድፍን የእርሻ ጣቢያው በእንቅልፍ እርጭታ ተዋጠ።

# ምእራፍ ሁለት

## አመፅ ፈነዳ

ከሶስት ምሽት በኋላ አዘውንቱ ሜዠር በተኛበት ህይወቱ አለፈች። ሬሳውም ከፍራፍሬው እርሻ ግርጌ ተቀበረ።

ይህ የሆነው በመጋቢት ወር መጀመሪያ ላይ ነበር። በቀጣዮቹ ሶስት ወራት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ምስጢራዊ እንቅስቃሴ ሲካሄድ ሰነበተ። በእርሻ ጣቢያው ውስጥ ካሉት እንስሳት ለብልሆቹ የሜዠር ንግግር ስለ ህይወታቸው ፍፁም ልዩ የሆነ አመለካከትን ሰጥቶዋቸው ነበር። በሜዠር የተተነበየው **አመፅ** መቼ እንደሚፈነዳ አያውቁም። በእነሱ የህይወት ዘመን ውስጥ ይከሰታል የሚል እምነትም አልነበራቸውም። የእነሱ ተግባር ዝግጁ ሆኖ መጠባበቅ መሆኑን ግን በሚገባ ተገንዝበዋል።

እንስሳቱን የማስተማሩ እና የማደራጀቱ ሃላፊነት የወደቀው አሳሞቹ ላይ ነበር፣ ምክንያቱም እነሱ ከእንስሳቱ ሁሉ ብልሆች ናቸው የሚል የወል ግንዛቤ ተሰጥቶታልና። ከእኒህ አሳሞች መካከል ሁለት ያልተኮላሹ ወጣቶች ከፍተኛ ታዋቂነት ነበራቸው። ስኖውቦል እና ናፖሊዮን ይባላሉ። አቶ ጆንስ ለእርባታ ሽያጭ የሚቀልባቸው። ናፖሊዮን፣ ግዙፍ እና አስፈሪ ገፅታ ያለው የበርክሻየር ክፍለ ሃገር አሳማ ነበር። የእርሻ ጣቢያው ብቸኛ በርክሻየራዊ። ናፖሊዮን ተናጋሪ አይደለም። የሚፈልገውን ነገር በማስፈፀም ጉልበቱ ግን የተከበረ። ስኖውቦል ከናፖሊዮን ይልቅ ፍልቅልቅ አሳማ ሲሆን ባነጋገሩ ፈጣንና በፈጠራ ችሎታው የተሻለ ይሁን እንጂ የናፖሊዮንን ያህል ባህሪያዊ ጥንካሬ አልነበረውም።
ሌሎቹ ተባእት አሳሞች በሙሉ ወፋፍራምና ለምግብነት የሚዘጋጁ ነበሩ። ከነዚህም መካከል ይበልጥ ታዋቂው ስኩለር የተባለው፣ ክብ ጉንጭ፣ እርግብግብ አይን፣ ፈጣን እንቅስቃሴና ጆሮ ወጊ ድምፅ ያለው ትንሽ ወፍራም አሳማ ነበር። የሚደነቅም ተናጋሪ። በአስቸጋሪ ነጥቦች ላይ ሲከራከር ከጎን ወደ ጎን እየነጠረ፣ ጭራውን ሽው ሽው ሲያደርግ የማሳመን ሃይል ነበረው። እንስሳቱ ስለ ስኩለር ሲናገሩ “ምላሱ ጤፍ ይቆላል“ ይላሉ።

እነዚህ ሶስቱ (ስኖውቦል፣ ናፖሊዮን እና ስኩለር) የአዛውንቱ ሜዠርን ትምህርት አስፋፍተው ይዘትና ቅርፅ በመስጠት “እንስሳዊነት” የሚል ስም ሰጥተውታል። በየሳምንቱ በተደጋጋሚ ምሽቶች፣ አቶ ጆንስ ከተኛ በኋላ፣ በእርሻው መጋዘን ምስጢራዊ ስብሰባዎች እየጠሩ ስለ እንስሳዊነት አላማ ለሌሎቹ ይሰብካሉ። በመጀመሪያ ሰሞን ብዙዎቹ የሚገኙት በይሁን ባይነትና በፍላጎት አልባነት ነበር። እንደውም አንዳንዶቹ እንስሳት ‘ጌታው’ (ማስተር) እያሉ ስለሚጠሩት አቶ ጆንስ ታማኝነታቸውን እየገለፁ ይናገሩ ነበር። ወይም “የሚመግበን አቶ ጆንስ ነው፣ እሱ ከሌለ በረሃብ እናልቃለን” ይላሉ።

አንዳንዶቹ ደግሞ "ከሞትን በኋላ ስለሚፈጠረው ነገር ለምን እኛን ሊያስጨንቀን ይገባል?" ወይም "ይህ **አመፅ** መፈንዳቱ አይቀሬ ከሆነ እኛ አመፁን ለማምጣት መስራት አለመስራታችን ምን ለውጥ ያመጣል?" እያሉ ይጠይቃሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ከእንስሳዊነት መርህ የወጡ መሆናቸውን ለማስረዳት አሳሞቹ ፍዳቸውን ነበር የሚያዩት። ከሁሉም ግን እጅግ ከንቱ የሆነ ጥያቄ ያቀረበችው ሞሊ፣ ነጯ በቅሎ ነበረች። ስኖውቦልን የጠየቀችውም "ለመሆኑ **ከአመፁ** በኋላ ስኳር ይኖራልን?" የሚል ነበር።

"አይኖርም" ሲል መለሰ ስኖውቦል በቁርጠኝነት። "በዚህ እርሻ ጣቢያ ስኳር የማምረት አቅሙ የለንም። ለማንኛውም ስኳር ላንቺ አስፈላጊሽ አይደለም። የቻልሽውን ያህል አጃ እና ጭድ ግን ማግኘት ትችያለሽ"

"በጭራዬ ላይስ ሪቫን ማሰር እችላለሁ?" ስትል ጥያቄዋን ቀጠለች፣ ሞሊ።

"ጓዲት" አለ ስኖውቦል "እኒያ አቅልሽን የተቆጣጠሩት ሪቫኖች የባርነት ምልክት ናቸው። ነፃነት ከሪቫን የበለጠ መሆኑን መረዳት አትችዪምን?"

ሞሊ በስኖውቦል ንግግር መስማማቷን ብትገልፅም ቅሉ አምናበት ግን አልነበረም።

ከሁሉም በላይ አሳሞቹን ያስቸገራቸው የአቶ ጆንስ ታማኝ የቤት እንስሳ ጥቁሩ አሞራ ሙሴ የሚያሰራጨውን ውሸት ማስተባበል ነበር። ሙሴ የአቶ ጆንስ ሰላይ እና ነጭ ወሬ የሚያሰራጭ ከመሆኑም ሌላ የተዋጣለትም ምላሰኛ ነበር። እንደ ሙሴ ትረካ "እንስሳት ሁሉ ከሞቱ በኋላ በተድላ እና በደስታ የሚኖሩበት የሸንኮራገዳ ተራራ የሚባል ሀገር መኖሩን አውቃለሁ" ይላል። "ቦታውም የሚገኘው ከደመናዎች ትንሽ ከፍ ብሎ ሰማይ ላይ ነው" ሲል ይናገራል። "በሸንኮራገዳ ተራራ ላይ ሁሌም ከሳምንት እስከ ሳምንት እሁድ ሲሆን፣ አመቱን ሙሉ አደይ አበባ ይበቅልበታል፣ በየቁጥቋጦው ላይም ስኳርና የተልባ ኬክ ይበቅላል" ይላቸዋል። እንስሳቱ ከወሬ በቀር ስራ የማይወደውን ሙሴን ይጠሉታል። አንዳንዶች ግን በሸንኮራገዳ ተራራ ወሬ ያምኑ ስለነበር አሳሞቹ እንዲህ ያለ ስፍራ አለመኖሩን ለማሳመን አበክረው ይከራከሩዋቸዋል።

የአሳሞቹ ታማኝ ደቀመዛሙርት ሁለት ጎማ ጋሪ ጎታቾቹ ፈረሶች ቦክሰር እና ክሎቨር ነበሩ። እኒህ ሁለቱ የሚጠቅማቸውን ነገር በራሳቸው ህሊና የማሰብ ችግር አለባቸው። ይሁንና አሳሞቹን እንደ አስተማሪዎቻቸው አድርገው ከተቀበሉ በኋላ ግን የተነገራቸውን ሁሉ ማመን ብቻ ሳይሆን ያመኑበትንም ለሌሎች እንስሳት በቀላል አሳማኝ አገላለፆች ያስተላልፉሉ። በመጋዘኑ ውስጥ በምስጢር በሚካሄዱት ስብሰባዎች ሁሉ ያለማሳለስ ከመሳተፋቸውም ሌላ 'የእንግሊዝ አራዊት' በሚለው መዝሙር ሁሌም ለሚያበቃው ስብሰባ መሪ መዘምራንም ነበሩ።

እነሆ የተተነበየው **አመፅ** ማንም ከገመተው እና ከጠበቀው ውጪ አስቸጋሪ ባልሆነ መንገድ በቀላሉ ተሳካ። በቀዳማይ አመታት አቶ ጆንስ ቆፍጣና አስተዳዳሪና ታታሪ ገበሬ ቢሆንም ቅሉ ከቅርብ አመታት ወዲህ የክፉ ቀን ሰለባ ሆኗል። በፍርድ ቤት ሙግት በርካታ ገንዘብ ከከሰረ ወዲህ ጤናውን እስኪያቃውሰው ድረስ መጠጣት ጀምሯል። አንዳንድ ጊዜ ቀኑን ሙሉ ከቤት ሳይወጣ ተቀምጦ ጋዜጣ እያነበበ እና እየጠጣ አልፎ አልፎም ቁርስራሽ ዳቦ በቢራ አረስርሶ ለሙሴ እየሰጠ ጊዜውን ያሳልፋል። የጆንስ ረዳት የሆኑት ሰዎች ታማኝነት የጎደላቸው እና ሰነፎችም ነበሩ። እርሻው በአረም ተውጧል። የቤቶች ጣራ እድሳት ያስፈልጋቸዋል። ቁጥቋጦዎች ተረስተዋል። እንስሳቱ በቂ ምግብ አያገኙም።

ሰኔ ገባ። አዝመራውም ለመታጨድ ደረሰ። በእለተ ቅዳሜ፣ በበጋው እኩሌታ ዋዜማ፣ አቶ ጆንስ ወደ ዊልንገደን ሄዶ ቀይ አንበሳ ቡና ቤት ሲጠጣ ጥንብዝ ብሎ ከመስከሩ የተነሳ እስከ እሁድ እኩለቀን ድረስ አልተመለሰም ነበር። የጆንስ ሰዎች ጠዋት ላይ ላሞቹን ካለቡ በኋላ ጥንቸል አደና ሄደዋል። እንስሳቱን ለመመገብ እንኳን አልተጨነቁም። አቶ ጆንስ ከዊልንገደን እንደተመለሰም ሳሎን ውስጥ ሶፋ ላይ ፊቱን 'የአለም ዜና' በሚል ጋዜጣ ሸፍኖ ቋ ብሎ ተኛ። ቀኑ ለምሽት ቦታውን በተካ ጊዜም ቢሆን እንስሳቱን የመገባቸው አልነበረም። በመጨረሻም ረሀቡን መቋቋም አቃታቸው።

አንዲት ላም የእህል ማከማቻውን ክፍል በር በቀንዷ ሰበረችው። እናም ሁሉም እንስሳት ገብተው የቻሉትን ያህል መመገብ ጀመሩ። ይሄኔ ነበር ጆንስ ከእንቅልፉ የነቃው። ወዲያው ከአራቱ ረዳቶቹ ጋር ሆኖ ወደ ክፍሉ በመግባት እንስሳቱን በሁሉም አቅጣጫ በያዙዋቸው አለንጋዎች ይገርፉዋቸው ገቡ። ይህ ለተራቡት እንስሳት ከትእግስታቸው በላይ ነበር። ከቶውንም አንዳች ቅድመ ዝግጅት ባልተደረገበት ሁኔታ ሁሉም እንስሳት በአንድነት በተራብ አንጀታቸው በሚገርፉዋቸው ላይ ተነሱ። ጆንስና ግብረአበሮቹን በርግጫና በግንባራቸው እየመቱ ያራውጧቸው ጀመር። ሁኔታው ፍፁም ከእነ ጆንስ ቁጥጥር ውጪ ሆነ። በህይወታቸው በሙሉ እንስሳት እንዲህ ሲሆኑ አይተው አያውቁም። እንደፈለጉት የሚያንገላቷቸውና የሚያሰሯቸው እንስሳት ድንገት በህብረት ተነስተው በእንዲህ ያለ መንገድ ማመፃቸው ነፍስና ስጋቸውን አሸበራቸው። ለጥቂት ጊዜ ራሳቸውን ከጥቃቱ ለመከላከል ሞክረው ሲያቅታቸው እግር አውጪን ብለው ተፈተለኩ። ቁልቁለቱን እየተንደረደሩ ወደ ዋናው መንገድ በሙሉ ትንፋሻቸው ሲፈረጥጡ እንስሳቱ በድል አድራጊነት እየተከታተሉ ያባርሯቸው ጀመር።

ወ/ሮ ጆንስ በመኝታ ቤት መስኮት በኩል የሆነውን ሁሉ ተመለከተች። እየተጣደፈችም ጥቂት ጥሪቶችን በቦርሳ ከታታ በጓሮ በር ሾልካ ወጣች። ሙሴም ከተጋደመበት አፈፍ ብሎ ተነስቶ ክንፎቹን እያማታና በከፍተኛ ድምፅ እያንቋረረ ተከተላት። ይህ ሲሆን እንስሳቱ ጆንስንና ሰዎቹን ከግቢው አባርረው ካስወጧቸው በኋላ ትልቁን የውጪውን አጥር በር ጠርቅመው ተመለሱ።

እነሆ እንስሳቱ የሆነውን ሁሉ የማገናዘቢያ ፋታ ከማግኘታቸው በፊት አቶ ጆንስ ተባርሮ **አመፁ** በድል አድራጊነት ሲጠናቀቅ እነሱም *የማኖር እርሻ* ጣቢያ ባለቤቶች ሆኑ።

እንስሳቱ ከዚህ በኋላ ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ደቂቃዎች የሆነውን ሁሉ ማመን አቅቷቸው ነበር። በመጀመሪያ የእርሻውን ጣቢያ ግቢ ዙሪውን እየጋለቡ በውስጡ የተደበቀ የሰው ዘር አለመኖሩን የማረጋገጥ ፍላጎት አድሮባቸው ነበር። ወዲያው ግን የጆንስን ጨቋኝ የአስተዳደር ዘመን የሚያስታውሷቸውን ምልክቶች ሁሉ ለማጥፋት ወደ ዋናው ቤት አመሩ።

ከከብቶች ማደሪያዎች መጨረሻ የሚገኘውን የጭነት ክፍል ሰብረው በመግባት መለጎሚያና መሸበቢያ የሆኑትን የተለያዩ ብረታ ብረቶችን፣ የአፍንጫ ቀለበቶችን፣ የውሻ ሰንሰለቶችን፣ አቶ ጆንስ አሳሞችን እና በጎችን የሚያኮላሽበትን ቢላዎች በሙሉ አውጥተው ጉድጓድ ጨመሯቸው። ልጓሞች፣ ማነቆዎች፣ የፈረስ አይን መከለያዎች እና ክብረነክ የሆነውን በአፍንጫ ላይ የሚጠለቀውን ሁሉ ሰብስበው ሜዳ ላይ እየነደደ ከሚገኘው ቆሻሻ ጋር አብረው አቃጠሉት። የአለንጋዎች ሁሉ እጣ ፈንታም እሳት ሆነ። እንስሳቱ አለንጋዎቹ በእሳቱ ላንቃ ተለብልበው ሲንቀለቀሉ በደስታ ጦዙ። በገበያ ቀናት በፈረሶች አንገትና ጭራዎች ላይ ለጌጥ የሚታሰሩትን ሪቫኖች በሙሉ ስኖውቦል ሰብስቦ እሳቱ ውስጥ ዶላቸው።

*"ሪቫኖች"* አለ ስኖውቦል *"የሰው ልጅ ምልክቶች በመሆናቸው እንደ ልብስ ይቆጠራሉ። እንስሳት ሁሉ እርቃናቸውን ሊሆኑ ይገባል።"*

ቦክሰር ይህንን ሲሰማ በበጋው ወራት ጆሮዎቹን ከዝንቦች ለመከላከል የሚያደርገውን የሰሌን ባርኔጣ አምጥቶ ወደ እሳቱ ወረወረው።

በአጭር ጊዜ ውስጥም እንስሳቱ የጆንስን ዘመን የሚያስታዎሷቸውን ማንኛውንም ነገር ሁሉ አወዳደሙት። ይህ እንደተጠናቀቀም ናፖሊዮን ሁሉንም ወደ እህል ማከማቻው ክፍል ወስዶ ለእያንዳንዳቸው ሁለት እጅ የበቆሎ ራሽን፣ ለውሾቹ ደግሞ ሁለት፣ ሁለት ብስኩት አደላቸው። ከዚህ በኋላ 'የእንግሊዝ አራዊት' የሚለውን መዝሙር ሰባት ጊዜ በማከታተል ከዳር እዳር ዘምረው ሲያበቁ በህይወታቸው ተኝተው የማያውቁት እንቅልፍ ይዟቸው ጥርግ አለ።

በማግስቱ ከእንቅልፋቸው ማልደው እንደነቁ ባለፈው ምሽት ስለተቀዳጁት ታላቅ ድል አስታውሰው ሁሉም ወደ ግጦሹ መስክ በፍጥነት ሄዱ። የእርሻ ጣቢያውን ዙሪያ ገባ ከሚያሳየው ጉብታ ላይ ወጥተውም በንጋት ፀሀይ አካባቢያቸውን ቃኙ። አዎ! በአይናቸው የሚያዩት ነገር ሁሉ የእነርሱ ነበር። በደስታ ከመስከራቸው የተነሳ አየር ላየር እየተገለባበጡ፣ ክብ እየሰሩ ይጨፍሩ ጀመር። ጤዛው ላይ ተንከባለሉ። ጣፋጩን የበጋ ሳር ዠረገዱ። የጥቁሩን አፈር ኮረት ከስክሰው ማራኪ ጠረኑን አሸተቱ። ቀጥለውም የእርሻ ጣቢያውን እየተዘዋወሩ ጎበኙ። የሚታረሰውን መሬት፣ ማሳውን፡ የትንሹን የፍራፍሬ ተክል ስፍራ፣ መዋኛውን፣ መለስተኛውን ጫካ እየተመለከቱ ቃላት እስኪያጥሯቸው ድረስ አደነቁ። ይህንን ሁሉ ከዚህ በፊት አይተውት የማያውቁ ይመስል ነበር። ይህ ሁሉ አሁን የእነርሱ ንብረት መሆኑንም ማመን ከበዳቸው።

እነሆ ሁሉም ወደ አቶ ጆንስ መኖሪያ ቤት አመሩ። እንደደረሱም ከበሩ ፊት ለፊት በፀጥታ ቆሙ። እርግጥ ነው ይህም የእነርሱ ነበር። ግና ወደ ውስጥ ለመዝለቅ ፈሩ። ከጥቂት ማመንታት በኋላ ስኖውቦል እና ናፖሊዮን በሩን በትከሻቸው መንግለው እንስሳቱ በአንድ መስመር ሰልፍ ይዘው ወደ ውስጥ በጥንቃቄ እየተራመዱ ገቡ። ከክፍል ወደ ክፍል በዝግታ እየተዘዋወሩ እና እያንሾካሾኩ በየክፍሎቹ የሚገኙትን የማይታመኑ የቅንጦት ቁሳቁሶችን፣ አልጋዎቹ ላይ የሚገኙትን ምቾት ሰጪዎቹን ፍራሾች፣ ምቾታማውን ሶፋ፣ አረግራጊውን ምንጣፍ፣ በእንግዳ መቀበያው ክፍል ግርግዳ ላይ የተንጠለጠለውን የንግስት ቪክቶሪያን ምስል፣ በአድናቆት ተመለከቱ።

ከክፍሎቹ ወጥተው ደረጃዎቹን መውረድ እንደጀመሩም ከመኻላቸው ሞሊ አለመኖሯ ታወቀ። ተመልሰው ባደረጉት ፍለጋ ከመኝታ ቤቶቹ መካከል ምርጥ በሆነው ክፍል ውስጥ አገኟት። ከወ/ሮ ጆንስ የልብስ መሳቢያ ውስጥ አረንጓዴ ሪቫን ወስዳ ትከሻዋ ላይ እያስተካከለች በአስቂኝ ሁኔታ ራሷን በመስታወት ትመለከት ነበር። ለዚህ አድራጎቷ ግሳፄ ሰጥተዋት ተመልሰው ወጡ። በማብሰያ ክፍል ውስጥ ተንጠልጥሎ የነበረው ጥቂት የአሳማ ስጋ ውጪ እንዲቀበር ከመወሰዱና የቢራ ማጠራቀሚያው በርሜል በቦክሰር ከመረገጡ በስተቀር በቤቱ ውስጥ ባሉት ንብረቶች ላይ አንዳችም ጥፋት አልደረሰም። እንደውም እዛው ህንፃው ውስጥ እያሉ በአንድ ድምፅ ያፀደቁትን ውሳኔ አስተላለፉ። ይህም - የእርሻ ጣቢያው ህንፃ /የጆንስ መኖሪያ የነበረው/ በሙዚየምነት ያገለግላል - የሚል ነበር። *"የትኛውም እንስሳ በዚህ ህንፃ ውስጥ መኖር የለበትም"* ሲሉም ውሳኔያቸውን በህግነት አፀደቁ።

እንስሳቱ ቁርስ ከበሉ በኋላ ስኖውቦልና ናፖሊዮን ለስብሰባ ጠሩዋቸው።

"ጓዶች" አለ ስኖውቦል። "ከጠዋቱ ስድስት ሰዐት ተኩል ሆኗል። ከፊት ለፊታችን ረዥም ቀን ይጠብቀናል። ዛሬ ሰብል አጨዳ እንጀምራለን። ነገር ግን ከዛ በፊት ሌላ የምናስተናግደው ጉዳይ አለን።" አላቸው።

እናም አሳሞቹ በአለፉት ሶስት ወራት ውስጥ የአቶ ጆንስ ልጆች ድሮ ይማሩበት የነበረውን የፊደል መፃህፍ ከተጣለበት የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ አውጥተው ራሳቸውን በራሳቸው ማንበብና መፃፍ እንዳስተማሩ ይፋ አደረጉላቸው። ጥቁርና ነጭ ቀለም ከቡሩሽ ጋር እንዲመጣለት ናፖሊዮን ካዘዘ በኋላ በእርሱ ፊትአውራሪነት አውራ መንገዱ አጠገብ ወደሚገኘው ባለ አምስት ኮከቡ የእርሻው ግቢ አጥር በር አመሩ። እንደደረሱም ስኖውቦል (እሱ ነበርና በፅሁፍ በቂ ችሎታ የነበረው) በፊት እግሩ ሁለት ጣቶች መካከል ብሩሽ ይዞ በመዝጊያው አናት ላይ ያለውን 'ማኖር ፋርም' (Manor Farm) የሚለውን ፅሁፍ በማጥፋት *'የእንስሳ እርሻ'* (Animal Farm) በሚል ተካው።

እነሆ ከዛን ግዜ ጀምሮ የእርሻ ጣቢያው መጠሪያ *የእንስሳ እርሻ* ሆነ። ከዚህ በኋላ እንስሳቱ ወደ እርሻው ቤቶች ተመለሱ። እንደ ደረሱም ስኖውቦልና ናፖሊዮን መሰላል አስመጥተው ከትልቁ መጋዘን ግርግዳ ላይ አስቆሙት። አሳሞቹ ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ባደረጉት ጥናት መሰረት የእንስሳዊነት መርሆዎችን በመጭመቅ በሰባት ትእዛዛት እንዲጠቃለል ማድረጋቸውን አበሰሩዋቸው።

ሰባቱ ትእዛዛትም እነሆ በግርግዳው ላይ ይሰፍራሉ። በ*'እንስሳ እርሻ'* ከእንግዲህ የሚኖሩ እንስሳት ***የማይጣስና የማይቀለበስ*** የህይወታቸው መመሪያዎች እኒህ ሰባቱ ትእዛዛት መሆናቸው ተደነገገ። በከባድ ችግር (መቼም ቢሆን አሳማ መሰላል ላይ ሚዛኑን ጠብቆ ለመቆም ይከብደዋልና) ስኖውቦል ወጥቶ መፃፍ ጀመረ። ስኩለር ከስኖውቦል ትንሽ ዝቅ ብሎ በመቆም ቀለምና ብሩሽ ያቀብለዋል። ትእዛዛቱም ከሰላሳ ያርድ እርቀት መነበብ እንዲችሉ ሆነው በነጭ ቀለም በትልልቁ ተፃፉ። እነርሱም የሚከተሉት ነበሩ፤

***ሰባቱ ትእዛዛት***

1. *በሁለት እግር የሚሄድ ሁሉ ጠላት ነው።*
2. *በአራት እግር የሚሄድ ወይም ክንፍ ያለው ሁሉ ወዳጅ ነው።*
3. *ማንኛውም እንስሳ ልብስ መልበስ የለበትም።*
4. *ማንኛውም እንስሳ አልጋ ላይ መተኛት የለበትም።*
5. *ማንኛውም እንስሳ አልኮል መጠጣት የለበትም።*
6. *ማንኛውም እንስሳ ሌላ እንስሳ መግደል የለበትም።*
7. *ሁሉም እንስሳት እኩል ናቸው።*

በአጠቃላይ ፅሁፉ ጥራት የነበረው ሲሆን ከጥቂት ሆሄያት ግድፈት በስተቀር ምንም ስህተት አልነበረውም። ስኖውቦል ድምፁን ከፍ አድርጎ ትእዛዛቱን ለ እንስሳቱ አነበበላቸው። ሁሉም ጭንቅላቶቻቸውን ከፍ ዝቅ በማድረግ መስማማታቸውን ገለፁ። ከመኻከላቸው ብልህ የሆኑት ትእዛዛቱን በቃላቸው መያዝ ጀምረው ነበር።

"ጓዶች" ሲል ጮኸ ስኖውቦል፤ ብሩሽና ቀለሙን ወርውሮ "አሁን ወደ እርሻ! ማንነታችንን ለማሳየት፤ ጆንስና ሰዎቹ አዝመራውን ለመሰብሰብ ከሚወስድባቸው ጊዜ ባነሰ ማጠናቀቅ ይኖርብናል።"

በዚህ ሁሉ መካከል ለተወሰነ ጊዜ ተደብተው የቆዩት ሶስቱ ላሞች የጭንቀት 'እምቧ' ድምፅ አሰሙ። ለሃያ አራት ሰአታት ባለመታለባቸው ጡቶቻቸው አለቅጥ አግተው ሊፈነዱ ደርሰዋል። አሳሞቹ ጥቂት ካሰላሰሉ በኋላ ባልዲዎች አስመጥተው ያለምንም ስህተት ላሞቹን አለቡዋቸው፤ ጣቶቻቸው በዚህ ሙያ ልምድ ያላቸው እስከሚመስል። አምስት ባልዲዎች ሙሉ ቅባቱ የተንጣለለ ትኩስ ወተት ታለቡ። እንስሳቱም ወተቱን እያዩ ጎመጁ።

"ይህ ወተት ምን ይደረጋል?" ሲል አንዱ እንስሳ ጠየቀ።

"አንዳንድ ጊዜ ጆንስ የተወሰነውን ከፍርፋሪ ጋር ለውሶ ይሰጠን ነበር" አለ ከዶሮዎቹ አንዱ።

"ጓዶች፣ ስለ ወተቱ ሀሳብ አይግባችሁ።" ሲል ጮኸ ናፖሊዮን ከባልዲዎቹ ፊት ለፊት በመቆም። "የሚያስፈልገውን እናደርጋለን። ዋናው ነገር አዝመራው ነው። ጓድ ስኖውቦል ወደዛው ይመራችኋል። እኔም ዘግየት ብዬ እከተላችኋለሁ። ወደፊት ጓዶች! አዝመራው ይጠብቃችኋል።"

እናም እንስሳቱ ወደ እርሻው አመሩ። ደንገዝገዝ ብሎ ከስራ ሲመለሱ ግን ቀን ላይ የታለበው ወተት ደብዛው መጥፋቱን አስተዋሉ።

# ምእራፍ ሶስት

## የእንስሳዊነት መርሆ

ሰብሉን ለመሰብሰብ አቤት የደከሙት ድካም፤ አቤት ያፈሰሱት ላብ! ግና ልፋታቸው መና ሆኖ አልቀረም። ምርቱ ከቶውንም ከጠበቁት በላይ ሆኖላቸው ነበርና።

አንዳንድ ጊዜ ስራው እጅግ አድካሚ ነበር። መሳሪያዎቹ የተሰሩት ለሰው ልጅ እንጂ ለእንስሳት ባለመሆኑ በሁለት እግር ቆመው መስራት ለማይችሉት እንስሳት ፈተና ሆነውባቸዋል። ቢሆንም ግን ብልሆቹ አሳሞች ሁሌም ዘዴ ይፈጥራሉ። ፈረሶቹ ማሳዎቹንና የስራውን ባህሪ ከጆንስና ከሰዎቹ በላይ ጠንቅቀው ነበር የሚያውቁት።

አሳሞቹ የጉልበት ስራ አይሰሩም። የእነርሱ ተግባር መመሪያ መስጠትና መቆጣጠር እንጂ። በአላቸው ከፍተኛ እውቀት ሳቢያ የአመራሩን ቦታ የያዙትም እነሱ ነበሩ። ቦክሰር እና ክሎቨር ራሳቸውን በራሳቸው ለስራ አስታጥቀው (መቼም በዚህ ወቅት ጠፍር እና ልጓም የሉምና) ውድማውን እየዞሩ ሲወቁ፤ አሳሞቹ ከኋላቸው ሆነው " አይዞህ ጓድ! በርቺ ጓድ!" እያሉ ያሰሩዋቸዋል።

ሁሉም እንስሳት ደካማ የሚባለው እንኳን ሳይቀር በአዝመራው ውቂያ እና በስብሰባው ላይ ከልባቸው ነበር የሚደክሙት። ዶሮዎች እና ዳክየዎች በአቅማቸው እያንዳንዷን ደቃቅ ጥራጥሬ ሳትቀር በመልቀም ቀኑን ሙሉ በጠራራ ፀሀይ ሲሰሩ ይውላሉ። በመጨረሻም ጆንስ እና ሰዎቹ ከሚወስድባቸው ጊዜ ሁለት ቀን ቀድመው ጨረሱ። ምንም አይነት የባከነ ምርት አልነበረም። ዶሮዎቹና ዳክዬዎቹ በንቁ አይኖቻቸው ሌሎቹ ያላዩትን ጥራጥሬ ሁሉ ሰብስበው ነበር። በእርሻው ጣቢያ ከሚኖር የትኛውም እንስሳ አንድ ጉርሻ እንኳን ከምርቱ ላይ የሰረቀ አልነበረም።

በጋውን በሙሉ የእርሻው ስራ ሳይተጓጎል ቀጠለ። እንስሳቱ ደስታቸው ወሰን አልነበረውም። እራሳቸው ለራሳቸው ያመረቱትን ምግብ በእርካታ እያጣጣሙ ነበር የሚመገቡት፤ በቆንቋና ጌታ ይመፀወታቸው የነበረበት ጊዜ አብቅቷልና። ከንቱ የሆኑት ደም መጣጮቹ የሰው ልጆች ከተወገዱ በኋላ ሁሉንም አጥግቦ የሚትረፈረፍ ምግብ ሞልቷል። ልምዱ ባይኖራቸውም እንኳን የመዝናኛ ጊዜም ነበራቸው። ብዙ ፈተናዎችም ገጥመዋቸዋል። ለምሳሌ በዛው አመት መጨረሻ የበቆሎ አዝመራ ሲሰበሰብ እንደ ጥንቱ ዘመን ሽፋሉን በትንፋሻቸው ማስለቀቅ ነበረባቸው፤ የእርሻ ጣቢያው ለዚህ ስራ የሚሆን መሳሪያ አልነበረውምና። ታዲያ ቢሆንም፤ እድሜ ለብልሆቹ አሳሞችና ለጠንካራ ጡንቸኛው ቦክሰር ይሁንና የማይወጡት ችግር አልነበረም።

ቦክሰር በሁሉም ዘንድ የሚደነቅ ነበር። በዘመነ ጆንስም ጠንካራ ሰራተኛ የነበረ ቢሆንም ቅሉ፤ አሁን ግን የአንድ ሳይሆን የሶስት ፈረሶች ያህል ነበር የሚሰራው። አንዳንዴ የእርሻው ጣቢያ ስራ በሙሉ በእርሱ ጫንቃ ላይ የሚወድቅበት ጊዜ ነበር። ከጠዋት እስከ ማታ ከባዱ ስራ ባለበት ቦታ ሁሌም ሲገፋ እና ሲጎትት ይገኛል። ከአውራ ዶሮዎቹ መካከል ከአንደኛው ጋር ዘወትር ጠዋት ሌሎች ከእንቅልፋቸው ከመነሳታቸው ግማሽ ሰአት አስቀድሞ እንዲቀሰቅሰው ባደረገው ውል መሰረት ማልዶ በመነሳት አስቸጋሪ በሆኑት ተግባራት ላይ ተገኝቶ ያለ አስገዳጅ ይሰራል። ለማንኛውም ችግር ወይም ሽንፈት መልሱ "ከዚህ በበለጠ እሰራለሁ" የሚል ነበር። ይህንንም መመሪያው አድርጎታል።

እያንዳንዳቸው የሚሰሩት እንደችሎታቸው ነበር። ለምሳሌ ዶሮዎቹና ዳክዬዎቹ አምስት እንቅብ የሚሆን በየቦታው ተፈነጣጥሮ የነበረ ስንዴ ሰብስበዋል። ማንም አይሰርቅም። ማንም በሚሰጠው ራሽን አያጉረመርምም። በቀድሞ ጊዜ ይታይ የነበረው ድብድብ፤ መነካከስ እና መቀናናት ጠፍቷል ማለት ይቻላል። መጯጯህ ቀርቷል። እርግጥ ሞሊ ጠዋት መነሳት አይሆንላትም። ከስራ ቦታም ሸኾናየ ውስጥ ጠጠር ገብቷል የሚል አስባብ እየፈጠረች አቋርጣ ትሄዳለች። የድመቲቱ ፀባይማ ልዩ ነበር። ስራ አለ ከተባለ ደብዛዋ ይጠፋል። ለሰአታት የት እንዳለች የሚያውቅ አይኖርም። የምግብ ሰአት ሲደርስ ከች ትላለች። ወይም ስራ ካለቀ በኋላ፤ ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ፤ ከጠፋችበት ትመጣለች። ታዲያ ሁሌም ግሩም የሆነ ምክንያት የማቅረብ ችሎታ ነበራት። እየተቅለሰለሰች ስታንኳርር ምክንያቷን ላለማመን ይከብዳል።

ሽማግሌው አህያ፤ ቤንጃሚን፤ **ከአመፁ** በኋላም ቢሆን ፀባዩ አልተቀየረም። ስራውን እንደሁ ያኔ በዘመነ ጆንስ እየለገመ እንደሚሰራው ይሰራል። ለትርፍ ሰአት ስራ ግን በፍፁም በፈቃደኝነት አይሰለፍም። ስለ **አመፁ** እና ስላስከተለው ለውጥ አስተያየት አይሰጥም። የቀድሞ ጌታው ጆንስ በመባረሩ ደስታ ተሰምቶት እንደሆን ስሜቱን ሲጠየቅ፤ "አህዮች ረዥም እድሜ ይኖራሉ። አንዳችሁም አህያ ሞቶ አይታችሁ አታውቁም" የሚል መልስ ይሰጣል። ይህ መልሱ የጠያቂዎቹን አፍ ይዘጋል።

እሁድ ስራ የለም። ቁርስ ከተለመደው ጊዜ በአንድ ሰአት ይዘገያል። ከቁርስ በኋላ በየሳምንቱ የማይቀር ስነስርአት ይካሄዳል። መጀመሪያ ሰንደቅአላማ ይሰቀላል። ከወ/ሮ ጆንስ መልበሻ ክፍል ስኖውቦል ባገኘው አሮጌ አረንጓዴ የጠረጴዛ ልብስ ላይ ቀንድና ሸኾና በነጭ ቀለም ስሎበታል። ይህ ባንዲራ ዘወትር እሁድ ጠዋት በትልቁ ቤት የአትክልት ስፍራ ይሰቀላል። አረንጓዴው ቀለም የእንግሊዝን መሬት ለምለምነት የሚያመለክት፤ ሸኾናው እና ቀንዱ ደግሞ ከሰው ልጅ ድል መሆን በኋላ የሚመሰረተውን የእንስሳት ሪፐብሊክ የሚያሳይ ነው ሲል ስኖውቦል ገልፆላቸዋል። ከባንዲራ ስነስርአት በኋላ እንስሳቱ ወደ ትልቁ መጋዘን በሰልፍ ይሄዳሉ። በዚህ ስፍራ አጠቃላይ ስብሰባ ይካሄዳል። ይህም '**ስብሰባው**' በመባል ይታወቃል። በዚህ ስብሰባም የሚቀጥለው ሳምንት የስራ እቅድ ቀርቦ ውይይት እና ውሳኔ ይደረግበታል።

የውሳኔውን ሀሳብ ሁሌም የሚያቀርቡት አሳሞቹ ነበሩ። ሌሎቹ እንስሳት እንዴት ድምፅ መስጠት እንዳለባቸው ተምረዋል። ነገር ግን የራሳቸው የሆነ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ አይችሉም። በውይይቱ ስኖውቦል እና ናፖሊዮን ንቁ ተሳታፊ ነበሩ። ይሁንና እኚህ ሁለቱ በሃሳብ ተስማምተው እንደማያውቁ ግልፅ ነበር። ያንደኛውን ሀሳብ ሌላኛው ማፍረሻ በማቅረብ ይቃወማል። ስምምነት የተደረሰበት ጉዳይ ቢሆንም እንኳን። ለምሳሌ ከፍራፍሬው እርሻ ወዲያ ያለውን ትንሽ ባዶ መሬት ጡረታ ለሚወጡ እንስሳት መኖሪያ ይሁን በሚለው ቢስማሙም ለእያንዳንዱ የእንስሳ ዘር የጡረታ እድሜው ስንት ይሁን በሚለው ላይ የጦፈ

ክርክር ያካሂዳሉ። ስብሰባው ዘወትር የሚያበቃው 'የእንግሊዝ አራዊት' በሚለው መዝሙር ሲሆን የከሰአት በኋላው ጊዜ ለመዝናኛነት ተመድቧል።

አሳሞቹ የመጫኛ ክፍሉን ጠቅላይ ሰፈራቸው አድርገውታል። ማታ፤ማታ ቀጥቃጭነትን፤ አናጢነትን እና ሌሎች አስፈላጊ የእጅ ሙያ ጥበባትን ከአቶ ጆንስ ቤት ከወሰዱት መፅሀፍ ያጠናሉ። ስኖውቦል 'የእንስሳ ኮሚቴዎች' ብሎ በሰየመው ተግባር የተጠመደ ሲሆን ለዚህ ተልእኮውም እንደ ብረት የጠነከረ ፅናት ነበረው።

ለዶሮዎቹ የእንቁላል ምርት ኮሚቴን፤ ለላሞቹ የንፁህ ጭራ ሊግን፤ ለዱር ጓዶች የተሃድሶ ትምህርት ኮሚቴን (የዚህ ኮሚቴ ግብ አይጦችን እና ጥንቸሎችን ማላመድ ነበር)፤ ለበጎቹ የነጭ ጥጥ ንቅናቄ ኮሚቴን እና ሌሎችንም ኮሚቴዎች አቋቋመ። ከነዚህ ሌላ የመሰረተ ትምህርት ክፍሎችን ያካሂድ ነበር። በአጠቃላይ እኒህ ፕሮጀክቶች በሙሉ ውጤት አልባ ነበሩ። ለምሳሌ የዱር እንሰስሳቱን ለማላመድ የተዋቀረው ኮሚቴ ወዲያው ነበር የፈረሰው። እኒህ እንስሳት ያው እንደ ዱር አውሬነታቸው መኖር ቢቀጥሉም፤ ካቀረቧቸው እና ጥቅም የሚያገኙበት ከመሰላቸው ብቻ ነበር መስለው የሚያድሩት።

ድመት የተሃድሶ ትምህርት ኮሚቴን ተቀላቅላ ለተወሰነ ጊዜ ሽር ጉድ አብዝታ ነበር። አንድ ቀን ለምሳሌ ጣራ ላይ ተቀምጣ ከመዳፏ ርቀው ከሚገኙ ግራጫ ትንንሽ ወፎች ጋር ስትነጋገር ታይታለች። "እነሆ አሁን ሁልም እንስሳት ጓዶች በመሆናቸው ማንኛውም ወፍ መጥቶ ክንዴ ላይ የማረፍ መብት አለው" በማለት ሰብካቸው ነበር። ድንቢጦቹ ወፎች ግን 'ጎመን በጤና' ብለው አልቀረቧትም።

መሰረተ ትምህርቱ ታላቅ ውጤትን አስመዝግቧል። በልግ በገባ ወቅትም በ እርሻው ጣቢያ ያሉት እንስሳት ከሞላ ጎደል 'ጥቁር መጋረጃ' ቀድደው ነበር።

አሳሞቹ እንደሆን ማንበብ እና መፃፍን ከተካኑ ሰንብተዋል። ውሾቹ ማለፊያ የማንበብ ችሎታ ቢኖራቸውም ከሰባቱ ትእዛዛት ውጪ የማንበብ ፍላጎት የላቸውም። ፍየሏ ሙሬል፤ ከውሾቹ የተሻለ የማንበብ ችሎታ ነበራት። ከተከመረ ቆሻሻ ላይ ያገኘቻቸውን የጋዜጣ ቅዳጆች አንዳንዴ ለሌሎች እንስሳት ታነብላቸዋለች።

ቤንጃሚን ማንኛውም አሳማ ማንበብ የሚችለውን ያህል የማንበብ ክህሎት ቢኖረውም ችሎታውን ሲተገብር ግን አይታይም። "ለንባብ የሚበቃ ነገር አልተፃፈም" ይላል ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር።

ክሎቨር ሆሄያቱን በሙሉ አውቃለች። ቦክሰር ከ'ዲ' ፊደል በላይ መጥራት አይሆንለትም። አቧራማው መሬት ላይ ' ኤ ቢ ሲ ዲ'ን በግዙፍ ሸኾናው ይፅፍና ጆሮዎቹን ወደ ኋላው ቀልብሶ ፈዝዞ ይመለከታቸዋል፤ ቀጥሎ የሚመጡትን ፊደላት ለማስታወስ በብርቱ እያሰበ። ግን አይሳካለትም። እርግጥ በተደጋጋሚ ጊዜያት 'ኢ ኤፍ ጂ ኤች' የሚባሉትን ሆሄያት ተምሯል። ይሁንና እኒህ ፊደላትን አጥንቶ ማስታወስ ሲጀምር ግን 'ኤ ቢ ሲ ዲ'ን መማሩን ፈፅሞ ይረሳል። ከቶም አያስታውሳቸውም። በመጨረሻም በመጀመሪያዎቹ አራት ፊደላት እውቀቱ በመርካት እነሱንም ደግሞ እንዳይረሳቸው በቀን አንዴ ወይም ሁለቴ እየፃፈ ያጠናቸዋል።

ሞሊ ስሟ ከሚፃፍባቸው አምስት ፊደላት ውጪ ለመማር አሻፈረኝ አለች። እኒህን ፊደላት በግሩም ሁኔታ በሀረግ ላይ ትቀርፃቸውና በአበባ አስጊጣቸው ዙሪያቸውን እየዞረች ስታደንቅ ትውላለች።

የተቀሩት እንስሳት ግን ከ'ኤ' በላይ መዝለቅ ተስኗቸዋል። እንደ በጎች፣ ዶሮዎችና ዳክየዎች አይነቶቹ የለየላቸው ደደቦች ሰባቱን ትእዛዛት በቃላቸው መያዝ እንዳልቻሉም ተደርሶበታል። ስኖውቦል ይህንን ጉዳይ ካብሰለሰለ በኋላ "ሰባቱ ትእዛዛት ቅልብጭ ባለ አንድ መርህ ስር ይጠቃለላሉ" ሲል አወጀ። ***"አራት እግሮች ጥሩ፤ ሁለት እግሮች መጥፎ"*** — "ይህ" አለ ስኖውቦል "የእንስሳዊነትን መሰረታዊ መርሆዎች ጨምቆ ይዟል። ይህንን መሪ ቃል በልቦናው ያሳደረ ከሰው ልጆች መሰሪ ተንኮል ይድናል።"

ወፎች ሁለት እግራማ በመሆናቸው በመሪ ቃሉ ላይ ተቃውሟቸውን አሰሙ። ስኖውቦል ግን የወፎች ተቃውሞ ስህተት መሆኑን ለማሳመን ጊዜ አልፈጀበትም።

"ጓዶች፣ የወፍ ክንፍ መንቀሳቀሻ የሰውነት ክፍል እንጂ ነገሮችን እንደ እጅ ማወሳሰቢያ አካል አይደለም። ስለሆነም መታየት ያለበት እንደ እግር ነው። የሰው ልጅ መለያ ምልክቱ እጅ ነው። እጅ ነው የጥፋቶች ሁሉ መሳሪያ።" ሲል አስረዳቸው ስኖውቦል።

ወፎቹ የስኖውቦል የተወሳሰበ ንግግር አልገባቸውም። ምክንያቱን ግን ተቀበሉት። እነሆ በአእምሮ ብቃታቸው ዝቅተኛ የሆኑት ሁሉም እንስሳት መሪ ቃሉን በልቦናቸው ለማሳደር ያጠኑ ጀመር። **"አራት እግሮች ጥሩ፤ ሁለት እግሮች መጥፎ"** ይህ መሪ ቃል ከመጋዘኑ ግርግዳ መጨረሻ ከሰባቱ ትእዛዛት በላይ በጉልህ ፊደላት ተፃፈ። በጎቹ መሪ ቃሉን አጥንተው በልቦናቸው ማስታወስ ከቻሉ በኋላ አብዝተው ወደዱት። ሳይሰለቻቸው፤ ለብዙ ሰአታት ሜዳ ላይ ተኝተው *"አራት እግሮች ጥሩ፤ ሁለት እግሮች መጥፎ"* እያሉ ሲያላዝኑ ይውላሉ።

ናፖሊዮን ለስኖውቦል የኮሚቴዎች ጋጋታ ምንም ስሜት አልነበረውም። እንደርሱ አባባል፤ ከሽማግሌዎች ይልቅ እጅግ አስፈላጊው ወጣቶችን በትምህርት ማነፅ ነበር። ሰብሉ እንደተሰበሰበ ጄሲ እና ብሉቤል በድምሩ ዘጠኝ ቡችሎች ወለዱ። ቡችሎቹን ገና በእንጭጭነታቸው ናፖሊዮን ከእናቶቻቸው ጉያ ወሰዳቸው። ወደፊት በትምህርት ይታነፁ ዘንድ ሃላፊነቱ የእርሱ መሆኑን በመግለፅ። በመጫኛው ክፍል በኩል በመሰላል ብቻ ከሚደረስበት ቆጥ ላይ ወስዶ አኖራቸው። ቡችሎቹ ለብቻቸው ተገልለው እንዲኖሩ በመደረጋቸው በሌሎች እንስሳት ፊፅሞ ከነመኖራቸውም ተረሱ።

እነሆ የወተቱ ደብዛ መጥፋት ምስጢር በየቀኑ የአሳሞቹ ምግብ እየተለወሰበት ለመሆኑ በቅርቡ ለእንስሳቱ ግልፅ ሆነላቸው። በአትክልቱ ማሳ ላይ የነበረው አፕል የደረሰ ሲሆን ሳሩም በረገፉ አፕሎች ተሞልቷል። በእንስሳቱ አስተሳሰብ፤ ይህ እንግዲህ ለሁሉም እኩል ይከፋፈላል። ይሁንና ከመሪዎቻቸው በተላለፈው ቀጭን ትእዛዝ መሰረት በሳሩ ላይ የወዳደቁት ፍራፍሬዎች በሙሉ ተሰብስበው ለአሳሞቹ ፍጆታ ወደ ጠቅላይ ሰፈር እንዲወሰዱ ሆነ። ይህ የተወሰኑ እንስሳትን እንዲያጉረመርሙ ቢያደርጋቸውም ዋጋ አልነበረውም። ሁሉም አሳሞች፤ ስኖውቦል እና ናፖሊዮን እንኳን ሳይቀሩ በአፕሎቹ ጉዳይ አቋማቸው አንድ ነበርና። ስኩለር ስለሁኔታው ማብራሪያ እንዲሰጥ ወደ እንስሳቱ ተላከ።

"ጓዶች" ሲል ጮኸ ስኩለር "መቼም እኛ አሳሞች ይህንን ያደረግነው ከግለኝነት እና ጥቅመኝነት ስሜት ተነሳስተን ይሆናል ብላችችሁ አስባችሁ ይሆን? እንደ እውነቱ ከሆነ ብዙዎቻችን ወተት እና አፕል እንጠላለን። እኔ ራሴ አብዝቼ ነው የምጠላቸው። እንዲህ የማድረጋችን አቢይ ምክንያት ጤንነታችንን ለመጠበቅ ስንል ነው። ወተት እና አፕል (ይህ በሳይንስ የተረጋገጠ ነው፤ ጓዶች) ለአሳሞች መልካም ጤንነት የግድ የሚሉ ንጥረ ነገሮችን የያዙ ናቸው።

"እኛ አሳሞች የአእምሮ ሰራተኞች ነን። የዚህ እርሻ ጠቅላላ አስተዳደርና መዋቅር በእኛ ጫንቃ ላይ ነው የወደቀው። ማእልት ከሌት የምንደክመው ስለ እናንተ ደህንነትና ብልፅግና

ስንል ነው። እኛ አሳሞች ይህንን ተልእኮ በአግባቡ መወጣት ባንችል የሚከተለውን ታውቃላችሁን? ጆንስ ይመለሳል። አዎ! ጆንስ ያለ ጥርጥር ተመልሶ ይመጣል። እንደ እውነቱ ከሆነ፤" ሲል ጮኽ ስኩለር፤ ከጎን ወደ ጎን እየነጠረ እና ጭራውን እያወናጨፈ፤ "እንደ እውነቱ ከሆነ ከእናንተ መኻል ጆንስ ተመልሶ እንዲመጣ የሚፈልግ ይኖራልን?"

የእንስሳቱ ሁሉ የጋራ የሆነ እምነት ቢኖር ጆንስ ተመልሶ እንዲመጣባቸው አለመፈለጋቸው ነበር። እናም ጥያቄው ስኩለር ባቀረበላቸው መልክ ሲሆንባቸው - ማንም ትንፍሽ አላለም። አሳሞቹን በጤና ተንከባክቦ የማቆየት ጥቅሙ ከስኩለር ገለፃ ግልፅ ሆኖላቸው ነበርና። እነሆ በዚህ መንገድ ወተቱ እና በፍራፍሬው ማሳ ላይ የረገፉት አፕሎች (ወደፊት ደግሞ በስለው የሚሰበሰቡትን ጨምሮ) ለአሳሞች ፍጆታነት ብቻ እንዲሆኑ እንስሳቱ ሁሉ በአንድ ድምፅ ተስማሙ።

# ምእራፍ አራት

## የላም በረት ጦርነት

*በእንስሳ እርሻ ስለተፈፀመው ድርጊት በበጋው ወራት መገባደጃ ዜናው የሀገሪቱን ግማሽ አካለለ። ስኖውቦል እና ናፖሊዮን በየቀኑ ወደ ጎረቤት እርሻዎች ርግቦች እንዲበሩ ያደርጋሉ። የሚሰጧቸውም መመሪያ፤ በድንበር ዙሪያ ከሚኖሩ እንስሳት ጋር ተቀላቅለው ስለ **አመፁ** እንዲነግሯቸውና 'የእንግሊዝ አራዊት'ን ዜማም እንዲያስተምሩዋቸው ነበር።*

*አቶ ጆንስ አብዛኛውን ጊዜ በዊሊንግደን ቀይ አንበሳ ቡና ቤት ባንኮኒ ላይ ተቀምጦ፤ የሚሰማው ካገኘ፤ በማይረቡ ወሮበላ እንስሳት ንብረቱን ተነጥቆ በግፍ ከ እርሻው ስለመባረሩ ሲያወራ ይውላል። ሌሎች ገበሬዎች በሀሳብ ደረጃ ቢደግፉትም የረባ እርዳታ ግን አላደረጉለትም። ይሁን እንጂ እያንዳንዳቸው በጆንስ ላይ የደረሰውን መከራ እንዴት ለራሳቸው ጥቅም ሊለውጡት እንደሚችሉ በውስጣቸው ያሰላስላሉ። ደግነቱ የእንስሳ እርሻን የሚዋሰኑት ሁለቱ ጎረቤቶች እርስ በርሳቸው ደግሞ እሳትና ጭድ ነበሩ።*

*'ፎክስዉድ' ተብሎ የሚጠራው እርሻ ሰፊና እንክብካቤ የጎደለው፤ ዘመን ያለፈበት፤ በቁጥቋጦ የተሞላና የግጦሽ መስኩም የተራቆተ ነበር። ባለቤቱ አቶ ፒልኪንግተን እንደ አየሩ ወቅት ጊዜውን የሚያሳልፈው ወይ አሳ በማጥመድ አልያም በአደን ነበር። ተጫዋችና የተከበረ ሰው ነበር - ፒልኪንግተን።*

*'ፒንችፊልድ' በመባል የሚታወቀው ሌላው እርሻ መለስተኛ እና በጥሩ ሁኔታ የተያዘ ሲሆን ባለቤቱም አቶ ፍሬድሪክ ይባላል። እሱም ቆፍጣና፤ ብልጣ ብልጥ እና በህግ ክፍል ውስጥም የሚሰራ ብርቱ ተሟጋች ነበር። እነዚህ ሁለቱ እርስ በርሳቸው ከመጠላላታቸው የተነሳ የጋራ በሆነ ጥቅማቸው ላይ እንኳ መስማማት አይችሉም።*

*ይሁንና በእንስሳ እርሻ ውስጥ በተነሳው **አመፅ** ክፉኛ የደነገጡ ሲሆን **አመፁ** ወደ እርሻዎቻቸው እንዳይዛመት እና እንስሳቶቻቸውም ስለ **አመፁ** ግንዛቤ እንዳይኖራቸው መከላከላቸው አልቀረም። በፊት ሰሞን፤ እንስሳት ራሳቸውን ችለው እርሻ ጣቢያ ያስተዳድራሉ - የሚለውን ሀሳብ እያላገጡበት ይስቁ ነበር። ሁሉም ነገር በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ድራሹ ይጠፋል፤ ይላሉ። በ'ማኖር ፋርም' (ሰዎቹ 'የእንስሳ እርሻ' የሚለውን ስም የሚጠሉት በመሆኑ አሁን ድረስ 'ማኖር እርሻ' ነበር የሚሉት) የሚኖሩት እንስሳት እርስ በርሳቸው እየተፋለሙ ሲሆን በረሀብም እያለቁ ናቸው፤ በማለት ወሬ ያናፍሳሉ።*

*ጊዜው እየገፋ እና እንደ ወሬው እንስሳቱ በረሀብ አለማለቃቸው ሲታወቅ ፍሬድሪክ እና ፒልኪንግተን የወሬ ዘመቻቸውን አቅጣጫ ቀይረው "በእንስሳ እርሻ ለጆሮ*

የሚዘገንን ድርጊት እየተፈፀመ ይገኛል” ማለት ጀመሩ። “በዚያ የሚኖሩት እንስሳት እርስ በርሳቸው ይበላላሉ፤ አንዱ እንስሳ ሌላውን በጋለ ብረት ይደበድባል፤ ሴቶቻቸው በሙሉ ለሁሉም የጋራ ሆነዋል። በተፈጥሮ ህግ ላይ ማመፅ እንዲህ ያለ መዘዝን ያስከትላል” ይላሉ ፍሬድሪክ እና ፒልኪንግተን።

ይሁን እንጂ ይህ የፍሬደሪክና የፒልኪንግተን ታሪክ የሚታመን አልነበረም። ይልቁንም፤ “እንስሳት የሰው ልጅን አባርረው ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት ግሩም እርሻ ጀምረዋል” የሚለው ጭምጭምታ መልኩን እና አይነቱን እየቀየረ በመዛመት ላይ ነበር። በዚያን አመት በገጠር በሚገኙ እርሻዎች ሁሉ **አመፁ** እንደ ሰደድ እሳት ተዛመተ። ለምሳሌ ብዙውን ጊዜ ታዛዥ የነበሩ ኮርማዎች በእንቢተኝነት ማስቸገር ጀመሩ። በጎች አጥር እየሰበሩ ጎመን መጨርገድ ያዙ። ላሞች ባልዲ በርግጫ ማለት አመጡ። አዳኞችን ከኮርቻዎቻቸው ላይ ፈረሶቹ ያሽቀነጥሯቸው ጀመር። ከሁሉም በላይ ግን ‘የእንግሊዝ አራዊት’ ዜማ እና ስንኞቹ ጭምር በሁሉም ዘንድ ታዋቂ ሆነ።

ሰዎች ‘የእንግሊዝ አራዊት’ የሚለውን መዝሙር ሲሰሙ በንዴት ይጦፋሉ፤ ላይ ላዩን የሚንቁት ቢመስሉም። “እንስሳት እንዴት እንዲህ ያለ እንቶ ፈንቶ መዝሙር ሊዘምሩ እንደቻሉ ሊገባን አልቻለም” ይላሉ። ‘የእንግሊዝ አራዊት’ን ሲዘምር የተገኘ እንስሳ እዛው በጅራፍ ይገረፋል። ያም ሆኖ የመዝሙሩን ሰደድ ማቆም አልተቻለም። ቁራዎች በየቅርንጫፉ ያንቋርሩታል። ርግቦች በየዛፉ ኩኩ ይሉታል። በቀጥቃጮች ሰፈር እና በአብያተክርስቲያናት ደወሎች ውስጥ ሁሉ ይገኛል። የሰው ልጆች ቅላፄውን ሲሰሙት ውስጣቸው ይርዳል፤ የሰው ዘር ማክተሚያው የምፅአት ዘመን ትንቢት መቃረቡ እየታወሳቸው።

በጥቅምት ወር መባቻ፤ በቆሎው እንደታጨደ እና እንደተከማቸ፤ የተወሰነውም ተወቅቶ እንዳለቀ፤ በከፍተኛ ስሜት የተዋጡ ርግቦች በእንስሳ እርሻ ጣቢያ አየር ላይ አንዣበው ከመስኩ አረፉ። ጆንስ እና ባልደረቦቹ፤ ከደርዘን በላይ ከሚሆኑ የፎክስዉድ እና ፒንችፊልድ ግብረ አበሮቻቸው ጋር በመሆን የእርሻ ጣቢያውን አጥር በር አልፈው በጋሪ ፈረስ መንገድ በኩል ወደ ዋናው ቤት እየገሰገሱ መሆናቸውን ተናገሩ። ሁሉም ዱላዎች መያዛቸውን እና ጆንስ ግን ጠመንጃ አንግቦ በፊታውራሪነት እየመራቸው መሆኑንም መረጃ ሰጡ። አመጣጣቸው የእርሻ ጣቢያውን ከእንስሳቱ ቁጥጥር ነፃ በማውጣት ለመያዝ መሆኑ ግልጥ ነበር።

እንዲህ ያለው ጥቃት ሊመጣ እንደሚችል አስቀድሞ ተገምቶ ነበርና አስፈላጊው መሰናዶ ሁሉ ተጠናቋል። ከትልቁ ቤት ያገኘውን ስለ ጁሊየስ ቄሳር የሚያትተውን መፅሀፍ ጠንቅቆ ያጠናው ስኖውቦል የመከላከያ ሃይሉን ሃላፊነት ወስዶ ነበር። እርሱም ባስተላለፈው አስቸኳይ ትእዛዝ ሁሉም እንስሳት በየምድብ ቦታቸው ከመቅፅበት መሸጉ።

ሰዎቹ ወደ ህንፃዎቹ እንደተቃረቡ ስኖውቦል የመጀመሪያውን የማጥቃት ትእዛዝ ሰጠ። በድምሩ ሰላሳ አምስት ርግቦች አየር ለአየር እየተምዘገዘጉ በሰዎቹ አናት ላይ የኩስ መአት ደጋግመው አዘነሙባቸው። የደረሰባቸውን የአየር ጥቃት እየተከላከሉ ሳሉ ቁጥቋጦዎች ውስጥ መሽገው የነበሩት ዳክዬዎች ወጥተው የሰዎቹን ባቶች ይቦተርፉ ጀመር። ይህ እንግዲህ

መለስተኛው የውጊያው ስትራቴጂ ሲሆን ዋናው ግቡም ወራሪዎቹን በማዋከብ ከስርአት ውጪ ማድረግ ነበር።

ወራሪዎቹ ዳክዬዎቹን በዱላዎቻቸው ተከላክለው በቀላሉ አባረሩዋቸው። ይሄኔ ስኖውቦል ሁለተኛውን ዙር የጥቃት ትእዛዝ አስተላለፈ። ሙሬል፣ ቤንጃሚን እና በጎቹ በሙሉ በስኖውቦል አዝማችነት ወደፊት ተምዘገዘጉ። ሰዎቹን ከያቅጣጫው በግንባራቸው እየገጩ እና በቀንዶቻቸው እየወጉ አጣደፏቸው። ቤንጃሚን እየተሽከረከረ የአህያ እርግጫ አቀመሳቸው። ይሁንና ሰዎቹ በዱላዎቻቸው እና በጠንካራ ቧት ጫማዎቻቸው ጥቃቱን ተከላከሉ። ይህ ለእንስሳቱ ከአቅማቸው በላይ መሆኑን የተረዳው ስኖውቦል በቅድመ ጥቃት ዝግጅት በተስማሙበት ምልክት መሰረት ቀጭን ዘግናኝ የአሳማ ድምፅ ሲያሰማቸው ሁሉም ወደ ኋላ በማፈግፈግ በማምለጫው በኩል ሾልከው ወደ መስኩ ሸመጠጡ።

ሰዎቹ በድል አድራጊነት ፎከሩ። ጠላቶቻቸው በፍርሃት ርደው በሽሽት ላይ ናቸው ብለው ስለገመቱም በየአቅጣጫው ተበትነው ተከተሏቸው። የስኖውቦል እቅድም ይህ ሁኔታ እንዲፈጠር ነበር። ሁሉም ሰዎች ከህንፃዎቹ አቅራቢያ በሚገኘው መስክ ውስጥ እንደገቡ በላም በረት ውስጥ አድፍጠው የነበሩት ሶስቱ ፈረሶች፣ ሶስቱ ላሞችና አሳሞቹ በሙሉ ከኋላቸው መጡባቸው፣ እንዳያፈገፍጉም ከበቡዋቸው። እነሆ ስኖውቦል ጥቃቱ ይጀመር ዘንዳ ምልክት ሰጣቸው። እሱ ራሱ በግንባር ቀደምነት ወደ ጆንስ ተፈተለከ።

ጆንስ ስኖውቦል እየተንደረደር እንደመጣበት ሲመለከት አነጣጥሮ ተኮሰበት። ጥይቱም የስኖውቦልን ጀርባ ጭሮ በማለፍ አንድ በግ ገደለ። ስኖውቦል ለቅፅበት እንኳን ቆም ሳይል እንደተምዘገዘገ ደርሶ ዘጠና አምስት ኪሎ ግራም ክብደቱን ከጆንስ ቅልጥም ላይ ለተመው። ጆንስ ወደ ኋላው ተሽቀንጥሮ የተከመረ እበት ላይ ሲዘፈቅ ጠመንጃውም ከእጁ አምልጦ ተሽቀነጠረ። ከሁሉም እጅግ በፍርሃት የሚያንቀጠቅጥ ጥቃት የፈፀመው ቦክሰር ነበር። ብረት የለበሱ የኋላ እግሮቹን ግዙፍ ሸኾናዎች በአየር ላይ እያወናጨፈ ድባቅ የሚከት እርግጫ ያቀምሳቸው ጀመር። የመጀመሪያው ምት ያረፈው ከፎክስዉድ ከመጡት መካከል በአንድ ወጣት ጭንቅላት ላይ ነበር። ልጁም ነፍሱን ስቶ ጭቃ ውስጥ ወደቀ። ይህንን የተመለከቱት ሌሎቹ ሰዎች በፍርሃት ተሸመድምደው ዱላዎቻቸውን እየወረወሩ ለማምለጥ ሞከሩ።

እንስሳቱ በሙሉ ወራሪዎቹን የሰው ዘሮች በሜዳው ዙሪያ እያራወጡ በቀንዶቻቸው እየወጉ፣ በርግጫ እየጠለዙ፣ ሌሎቹም እየነካከሱ፣ የወደቁትንም እየረጋገጡ መሹለኪያ አሳጧቸው። ከእንስሳቱ መኻል የአቅሙንና የችሎታውን ያህል ያለተበቀላቸው ከቶ አልነበረም። ድመቲቷ እንኳን ሳትቀር ከጣራ ዘላ አንዱ
ገበሬ ትከሻ ላይ በማረፍ በጥፍሮቿ አንገቱን ብትሰቀስቀው አሰቃቂ ኡኡታ አሰማ። በግርግሩ መኻል ሰዎቹ ባገኙት ማምለጫ ክፍተት ከተከበቡበት ተፈትልከው ወደ ዋናው መንገድ ሸመጠጡ። እነሆ ወረራውን ባካሄዱ አምስት ደቂቃ ውስጥ በመጡበት መንገድ በአሳፋሪ ሁኔታ ሽሽታቸውን ቀጠሉ። እስከ ግቢው አጥር በር ድረስም ዳክዬዎቹ ከኋላቸው በመከታተል ባቶቻቸውን እየነካከሱ አባረሩዋቸው።

ወራሪዎቹ በሙሉ አምልጠዋል፣ ከአንዱ በስተቀር። ሜዳው ውስጥ በደረቱ ጭቃ ላይ የተኛውን ወጣት ቦክሰር በሸሆናው እየነካካ በጀርባው ሊገለብጠው ቢሞክርም ሊንቀሳቀስለት አልቻለም።

“ሞቷል” አለ ቦክሰር በሀዘን ተውጦ። “የመግደል ፍላጎት ኖሮኝ አልነበረም፣ የብረት ጫማ ማጥለቄን ዘንግቼው እንጂ። ታዲያ አሁን ይህንን ሰው ሆን ብዬ አልገደልኩትም ብል ማን ያምነኛል?”

“ምንም ፀፀት አይሰማህ፤ ጓድ” ሲል ጮኸ ስኖውቦል። ከጆንስ የጥይት ጭረት ደሙ አሁንም ከጀርባው ይንጠባጠብ ነበር። “ጦርነት ማለት፤ ጦርነት ነው። የሰው ጥሩ የሞተ ብቻ ነው።”

“ህይወት የመቅጠፍ ፍላጎት የለኝም፤ የሰው ልጅ ቢሆንም እንኳን” ሲል ደገመ ቦክሰር አይኖቹ እንባ አቅርረው።

“ለመሆኑ ሞሊ የት አለች?” ጠየቀ ከመኻላቸው አንዱ።

በእርግጥ ሞሊ ጠፍታ ነበር። ሁሉም በድንጋጤ ተዋጡ። ሳይታወቅ በሰዎቹ ተጎድታ ይሆናል፤ እንደውም ተሸክመው ወስደዋትም ሊሆን ይችላል ብለው አሰቡ። በተካሄደው ፍለጋ ማደሪያዋ ውስጥ በታሰሩ የጭድ ክምሮች መኻል ጭንቅላቷን ቀብራ ተደብቃ ተገኘች። ልክ ጠመንጃው ሲተኮስ ነበር ሞሊ በድንጋጤ የፈረጠጠችው። ሞሊን አግኝተው ወደ ሜዳው ሲመለሱ አቅሉን ስቶ ተዘርሮ የነበረው ልጅ በቦታው የለም። ለካስ ጉዳት ደርሶበት ሳይሆን ከመጠን ያለፈ ድንጋጤ ነበር ህሊናውን እንዲስት ያደረገው። እናም እንስሳቱ ባካባቢው አለመኖራቸውን ሲመለከት ብን ብሎ ጠፋ።

እነሆ እንስሳቱ ሁሉ ከየአቅጣጫው ተሰባስበው አንዱ የሌላኛውን መስማት እስኪያቅተው እያንዳንዳቸው በጦርነቱ ውስጥ ስለፈፀሙት አስደናቂ ጀብድ ባንድ ድምፅ ያወራሉ። ወዲያው የተቀዳጁትን ድል ለማክበር ፌሽታ አካሄዱ። ባንዲራቸው ተውለበለበ። ‘የእንግሊዝ አራዊት’ መዝሙር ተደጋግሞ ተዘመረ። ከዚያም በውጊያው ህይወቷ ያለፈውን በግ በሀዘን ስነስርአት ቀብረው በመቃብሯም ላይ ተክል አኖሩ። በቀብሩ ስነስርአት ላይ ስኖውቦል ባደረገው ንግግር - *ለእንስሳ እርሻ* ህልውና ሲባል ሁሉም እንስሳት መስዋእት ለመሆን ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው በአፅንዖት ተናገረ።

ወታደራዊ የጀግኖች ሜዳሊያ ሽልማት ይኖር ዘንዳም እዛው ወሰኑ። “ጀግና እንስሳ አንደኛ ደረጃ” ለስኖውቦል እና ለቦክሰር ተሰጠ። ይህም የነሀስ ሜዳሊያ ነበር። (እንደ እውነቱ ከሆነ ሜዳሊያዎቹ ከመጫኛው ክፍል የተገኙ ያረጁና ለፈረስ ሸኾና ግልጋሎት የዋሉ ነበሩ።) ሜዳሊያዎቹ የሚደረጉት እሁድ እና በአመት በአል ቀን እንዲሆን ተወሰነ። ለሞተችውም በግ “የእንስሳ ጀግና ሁለተኛ ደረጃ” እንዲሰጣት ወሰኑ።

ጦርነቱ በምን ስም መጠራት እንደሚኖርበት ሰፊ ውይይት አካሄዱ። በመጨረሻም የላምበረት ጦርነት የሚለው ፀደቀ። ምክንያቱም ጥቃቱን መፈፀም የቻሉት እዚያ በማድፈጣቸው ነበርና። ጭቃ ውስጥ ወድቆ የተገኘው የአቶ ጆንስ ጠመንጃ በርካታ ጥይቶች በትልቁ ህንፃ ወስጥ እንደሉት ይታወቃል። ጠመንጃው ከሰንደቅ አላማው መስቀያ ምሶሶ ስር እንደ አንድ የጦር መሳሪያ ምልክት ሆኖ እንዲቆም ተወሰነ። እሱም በአመት ሁለት ጊዜ ይተኮሳል ተባለ። አንዱ ኦክቶበር 12 ሲሆን ይህም የላም በረት ጦርነትን ለመዘከር፤ ሁለተኛው ደግሞ በበጋው አጋማሽ **የአመፁን** ፍንዳታ ቀን ለማስታወስ በሚደረገው በአል ላይ የሚተኮስ ይሆናል።

# ምእራፍ አምስት

## የስኖውቦል እጣ

*“የእንስሳ እርሻ ሞኝ ነሽ ተላላ ፤ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ”*

ክረምት እየተቃረበ ሲመጣ ሞሊ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ አስቸጋሪ እየሆነች ሄደች። ዘወትር ጠዋት ለስራ እንዳረፈደች ሲሆን፤ ምክንያቷም “እንቅልፍ ተጫጭኖኝ መነሳት አልቻልኩም” የሚል ይሆናል። የመብል ፍላጎቷ ያልተቃወሰ ቢሆንም፤ ግልፅ ያልሆነ ህመም አለብኝ ትላለች። ባጋጠማት ሰበብ ሁሉ ስራዋን አቋርጣ ወደ ውሃ ኩሬው ትሄዳለች። እንደ ቂላ ቂልም ቆማ የራሷን ምስል ከኩሬው ውስጥ ፈዝዛ ትመለከታለች። ስለ ሞሊ ሌላ የከፋ ሀሜት መናፈስ ጀምሯል። አንድ ቀን ሞሊ ረጅሙን ጭራዋን በቄንጥ እየነሰነሰች እና ጭድ እያላመጠች ወደ ሜዳ ስታዘግም ክሎቨር ተከትላት ከጎኗ መራመድ ጀመረች።

“ሞሊ” አለች ክሎቨር፤ “አንድ የማነጋግርሽ ከባድ ጉዳይ አለኝ። ዛሬ ጠዋት የ እኛን እርሻ ከፎክስዉድ በሚለየው ቁጥቋጦ በኩል አሻግረሽ ስትመለከቺ አየሁሽ። ከአቶ ፒልኪንግተን ሰዎች አንዱ ከወዲያ ቆሞ ነበር። ምንም እንኳን የቆምኩት ራቅ ብሎ ቢሆንም፤ እሱ ሲያዋራሽና አፍንጫሽንም ፈቅደሽለት ሲደባብስ - ለመመልከቴ እርግጠኛ ነኝ። ለመሆኑ ምን እያደረግሽ ነው ያለሽው፤ ሞሊ?”

“አልደባበሰኝም! አልፈቀድኩለትም! እውነት አይደለም” ስትል ጮኸች ሞሊ፤ መሬቱን እየጫረች።

“ሞሊ፤ እስቲ ፊት ለፊት ተመልከቺኝ። ያ ሰው አፍንጫዬን አልደባበሰኝም ስትይ ትምይልኛለሽ?”

“እውነት አይደለም” ስትል ደገመች ሞሊ። ግን የክሎቨርን ፊት ማየት አልደፈረችም። ወዲያው እየጋለበች ወደ ሜዳው ሸመጠጠች።

ክሎቨር አንድ ሀሳብ ብልጭ አለላት። ለሌሎች ሳትተነፍስ ወደ ሞሊ ማደሪያ ሄደች። በሸሆናዋም ጭዱን ገለባበጠች። በዛም የተደበቁ የስኳር እንኳሮችን እና በርካታ የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ሪቫኖች አገኘች።

ይህ በሆነ በሶስተኛው ቀን ሞሊ ጠፋች። ለጥቂት ሳምንታት ዱካዋን ማግኘት አልተቻለም ነበር። ቆይቶ ርግቦቹ ዊሊንግደን ውስጥ እንዳዩዋት ተናገሩ። ጥቁርና ነጭ ቀለም ያለው ሰረገላ እየጎተተች ከ’ፓብሊክ ሀውስ’ ውጪ ቆማ አይተናታል አሉ
- ርግቦቹ። እስከ ቁርጭምጭሚቱ የሚደርስ ሱሪ የለበሰ፤ ታክስ ሰብሳቢ የሚመስል ቀይ ፊት ያለው ወፍራም ሰው፤ አፍንጫዋን እየደባበሰ ስኳር ያበላት ነበር። አዲስ ኮት ተሰፍቶላት መልበሷን፤ በጭራዋ ላይም የሚያብረቀርቅ ሪቫን ማሰሯን፤ በጣም ደስተኛ እንደምትመስልም
- ርግቦቹ ተናገሩ። እነሆ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሞሊን ስም ያነሳ እንስሳ አልነበረም።

በጥር ወር አየሩ የከፋ ሆነ። መሬቱ የድንጋይ ያህል በመጠጠሩ ምንም መስራት አልተቻለም። በትልቁ መጋዘን ውስጥ በርካታ ስብሰባዎች ተካሄዱ። አሳሞቹ ለሚቀጥለው

የእርሻ ወቅት ፕላን በማውጣት ተጠመዱ። አሳሞቹ ከሌሎቹ እንስሳት ይልቅ በግንዛቤ ችሎታቸው ይልቃሉ በሚለው የወል አስተሳሰብ ሳቢያ ስለ እርሻው ፖሊሲ የሚነሱ ጥያቄዎችን በሙሉ ውሳኔ የሚሰጡት እነሱው ነበሩ፤ ምንም እንኳን ውሳኔዎቹ ለጉባኤ ቀርበው በድምፅ ብልጫ መፅደቅ አለባቸው የሚል ደንብ ቢኖርም። በስኖውቦል እና በናፖሊዮን መካከል የማያባራ አለመግባባት ባይኖር ኖሮ ይህ አሰራር መልካም ሊሆን ይችል ነበር።

ስኖውቦል እና ናፖሊዮን በማንኛውም ነገር ካለመስማማታቸው የተነሳ ውሃ ቀጠነ ብለው ይጋጫሉ። ለምሳሌ አንደኛው ገብስ በርከት አድርገን እንዝራ ሲል፤ ሌላኛው ገብስ ሳይሆን መዝራት ያለብን አጃ መሆን አለበት ብሎ ይነሳል። አንዱ ለጎመን ይህኛው የእርሻ ቦታ ምቹ ነው ሲል፤ ሌላኛው ከችግኝ በስተቀር ለሌላ ምርት የማይረባ የቦታ ምርጫ ነው በማለት ቡራ ከረዩ ይላል። እያንዳንዳቸው የራሳቸው ተከታዮች አሉዋቸው። አንዳንዶቹ ክርክሮች ዱላ ቀረሾች ነበሩ። በየስብሰባዎቹ ላይ በሚያደርጋቸው ድንቅ ንግግሮች አብዛኛውን ጊዜ የብዙሃኑን ድጋፍ የሚያገኘው ግን ስኖውቦል ነበር።

ናፖሊዮን የራሱን ደጋፊዎች በማሰባሰብ ረገድ ከስኖውቦል ይበልጣል። በተለይ በጎቹን በሙሉ በቁጥጥሩ ስር አውሏቸዋል። ሰሞኑን በሚደረጉት ስብሰባዎች ላይ *"አራት እግሮች ጥሩ፤ ሁለት እግሮች መጥፎ"* የሚለውን መፈክር እያወረዱ ስብሰባዎችን ማሰናከል ተያይዘዋል። ስኖውቦል ወሳኝ የሆኑ ንግግሮች በሚያደርግበት ወቅት ላይ *"አራት እግሮች ጥሩ፤ ሁለት እግሮች መጥፎ"* መፈክራቸውን በማውረድ ሆን ብለው ንግግሩን ሲያውኩ ተስተውለዋል።

ስኖውቦል ከትልቁ ቤት ያገኘውን 'ገበሬ እና ከብት አርቢ' የሚለውን መፅሀፍ በጥልቅ በመመርመር ለአዳዲስ ፈጠራዎችና መሻሻሎች ሰፊ እቅድ አዘጋጅቷል። ስለ መስክ መስኖ፤ ስለ እንስሳት ደረቅ ምግቦች አያያዝ፤ እና ስለ መሰረታዊ የማዳበሪያ አመራረት ምሁራዊ ገለፃ ያደርጋል። ሁሉም እንስሰሳት በየቀኑ በሜዳው ውስጥ በተለያዩ ስፍራዎች ላይ እንዴት መፀዳዳት እንዳለባቸው የሚያሳይ የተወሳሰበ ፕላን አውጥቶላቸዋል። ይህም ለጠረጋ እና ለማጓጓዝ የሚውለውን ጉልበት ይቀንሳል ይላል።

ናፖሊዮን ምንም አይነት የራሱ የሆነ የሀሳብ ንድፍ አያቀርብም። ግን የስኖውቦል እቅዶች ከንቱዎች መሆናቸውን ይናገራል። አኳኋኑ ሁሉ ምቹ ጊዜን የሚጠብቅ ይመስላል። ከሁሉም ልዩነቶቻቸው ከፍተኛው እና የመረረ ፍጭት የተካሄደው በዊንድሚል (የንፋስ ሃይል ማመንጫ) ጉዳይ ላይ ነበር።

ከትልቁ ህንፃ ብዙም ሳይርቅ በሚገኘው መስክ መኻል የእርሻው ጣቢያ ከፍተኛ ነጥብ የሆነ ጉብታ ይገኛል። ስኖውቦል የጉብታውን ይዞታ ካጠና በኋላ ዊንድሚሉን ለመገንባት የሚያስፈልገው ቦታ ይኸው መሆኑን ተናገረ። ዳይናሞን በመትከል እርሻው የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ይኖረዋል ሲል አስረዳ። "በረቶች ብርሃን ይኖራቸዋል፤ ተሽከርካሪ ማጭድን ያንቀሳቅሳል፤ ለጭድ መቆራረጫ፤ ለመሽንሸኛ እና ለኤሌክትሪክ ላም ማለቢያ ሁሉ ያገለግላል" አላቸው። እንስሳቱ እንዲህ ያለ ነገር ከዚህ ቀደም ሰምተው አያውቁም። (የእርሻው ጣቢያ እንደሆን ዘመናዊ ያልነበረና እጅግ ኋላ ቀር መሳሪያዎችን የሚጠቀም ነበርና)

አስገራሚ የሆኑ የመሳሪያዎቹን ስእሎች እየቀረፀ እቅዱን ሲያቀርብላቸው አፋቸውን ከፍተው ለጉድ ያዳምጡታል። የመሳሪያዎቹ ጥቅም፦ የእናንተን ስራ ተክተው የሚያከናውኑ ሲሆን እናንተ ደግሞ ጊዜያችሁን እየተዝናናችሁ በየመስኩ ለመጋጥ ወይም የእውቀት አድማሳችሁን የሚያሰፋ ንባብ ወይም ውይይት ለማድረግ በቂ ጊዜ ይኖራችኋል - ይላቸዋል እንስሳቱን።

በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ስኖውቦል የዊንድሚሉን ፕላን ነድፎ ጨረሰ። የዊንድሚሉ ሜካኒካዊ አሰራር ዝርዝር የተገኘው የአቶ ጆንስ ንብረት ከነበሩት ሶስት መፃህፍት ነበር። 'ቤት ውስጥ ሊሰሩ የሚችሉ አንድ ሺህ ነገሮች'፣ 'ሁሉም ሰው ለራሱ ግንበኛ ነው' እና 'ኤሌክትሪክ ለጀማሪዎች' የሚሉ ነበሩ። ስኖውቦል ጥናቱን ያካሄድ የነበረው በቀድሞው የእንቁላል መፈልፈያ ዛኒጋባ ውስጥ ሲሆን ወለሉ የለሰለሰ ጣውላ መሆኑ ስእሎቹን ለመንደፍ ረድቶታል። አንዳንድ ጊዜ ለሰአታት በር ዘግቶ ይሰራል። የተከፋፈቱት መፃህፍት እንዳይታጠፉ ድንጋይ አኑሮባቸው፡ በሁለት ጣታማው እግሩ ጠመኔ ይዞ በፈጣን እንቅስቃሴ ላይ እና ታች እየተንጎራደደ፡ በመስመር ላይ መስመር እየጨመረ ይነድፋል። በየመኻሉ በስሜት ያጉተመትማል። በመጨረሻ የተወሳሰበና የተለያዩ የመሳሪያ አይነቶችን የያዘውን ንድፍ አቀረበላቸው።

እንስሳቱ ንድፉን ሲመለከቱት ለአይናቸው በጣም ቢወዱትም ነገረ ስራው ግን አንዳችም አልገባቸውም ነበር። ሆኖም እይታ የሚስበውን የስኖውቦልን ስእል ሁሉም እንስሳት ቢያንስ በቀን አንዴ ይጎበኙታል። ዶሮዎቹና ዳክዬዎቹ ሳይቀሩ ሄደው ተመልክተውታል፣ በወለሉ ላይ ያለውን የጠመኔ ስእል ላለመርገጥ አሳራቸውን እያዩ። ለናፖሊዮን ግን ቁብ አልሰጠውም። ገና ከጠዋቱ የዊንድሚሉን ግንባታ እንደሚቃወም ግልፅ አድርጓልና።

አንድ ቀን ናፖሊዮን በድንገት ተነስቶ የስኖውቦልን ፕላን ሊጎበኝ ሄደ። በዛኒጋባው ውስጥ ተንጎራደደ። የፕላኑን እያንዳንዱን አባጣ ጎርባጣ በአይኑ መርምሮ አንድ ሁለቴ አሸተተው። ስእሉን የጎሪጥ እየተመለከተ በሀሳብ እንደተዋጠ
ሁሉ ለጥቂት ጊዜ ባለበት ፀጥ ብሎ ቆመ። ቀጥሎም ሳይታሰብ እግሩን አነስቶ በፕላኑ ላይ ሸንበቆበት ቃል ሳይተነፍስ ክፍሉን ለቅቆ ወጣ።

እነሆ የእርሻው ጣቢያ እንስሳት በዊንድሚሉ ጉዳይ በአደገኛ ሁኔታ ተከፋፈሉ። እርግጥ ግንባታውን ለማከናወን ከባድ እንደሚሆንባቸው ስኖውቦል አልካደም፦ ድንጋይ ከስክሶ ግርግዳ መገንባት፣ ከዛም ሸራዎቹን ሰርቶ መወጠር፣ ይህ ሲጠናቀቅ ደግሞ ዳይናሞና የኤሌክትሪክ ሽቦዎች ማዘጋጀት። (እኒህ አቅርቦቶች ከየት እንደሚገኙ በስኖውቦል በኩል የተገለፀ ነገር የለም)። ይሁንና "ግንባታው በአንድ አመት ሊጠናቀቅ ይችላል" ይላል። "ዊንድሚሉ የጉልበት ስራ የሚቀንስ በመሆኑ በሳምንት ሶስት ቀን ብቻ ይሆናል የምትሰሩት" በማለት ስኖውቦል ለእንስሳቱ ገለፀላቸው።

ናፖሊዮን በበኩሉ "የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ የምግብ አቅርቦት ምርትን መጨመር እንጂ ዊንድሚል መገንባት አይደለም። በዚህ ከንቱ ፕላን ጊዜያችሁን የምታጠፉ ከሆነ በረሀብ ታልቃላችሁ" በማለት የመከራከሪያ ሀሳቡን አቀረበላቸው።

እንስሳቱ ለሁለት ተከፈሉ። በአንድ በኩል የስኖውቦል ደጋፊዎች *"ለስኖውቦል እና ለሶስት ቀን በሳምንት ስራ ድምፅ ስጡ"* የሚል መፈክር ሲይዙ፣ በአንፃሩ *"ለናፖሊዮን እና ለሚይራብ አንጀት ድምፅ ስጡ"* የሚል መፈክር ያነገቡ የናፖሊዮን ደጋፊዎች ተነሱ።

ከሁለቱም አንጃዎች ያልወገነው ቤንጃሚን ብቻ ነበር። "ምግብም እንደሁ አይትረፈረፍም፣ ዊንድሚልም ቢገነባ ድካም እንደሁ አይቀርም" በማለት የሁለቱንም አንጃዎች ሰበካ እንደማያምን ተናገረ። "ዊንድሚል ኖረ አልኖረ፣ ህይወት እንደሁ እንደነበረው ይቀጥላል - በአስከፊነቱ" ሲል ማጠናከሪያም አከለበት።

በዊንድሚል ግንባታ ጉዳይ ከተነሳው ውዝግብ ሌላ የእርሻው ጣቢያ የመከላከያ ጥያቄም አጨቃጫቂ ነበር። ምንም እንኳን በላም በረት በተካሄደው ጦርነት ሰዎች ድል ቢደረጉም፤ ራሳቸውን አደራጅተው የእርሻውን ጣቢያ እንደገና በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ እና ጆንስን በቦታው ለመመለስ ሌላ ወሳኝ ሙከራ ሊያደርጉ ይችላሉ የሚል አጠቃላይ ግንዛቤ ነበር - በእንስሳቱ መካከል። ለሁለተኛው ዙር ጦርነት መቀስቀስ ምክንያት ይሆናል ተብሎ የታመነበት ጉዳይ፦ የሰዎች ድል መሆን ዜናው በገጠር ሁሉ ተሰምቶ ስለነበር በአጎራባች እርሻዎች ውስጥ የሚኖሩ እንስሳትን የበለጠ ለአመፅ የተነሳሱ አድርጓቸዋል የሚል ነበር።

ስኖውቦል እና ናፖሊዮን እንደተለመደው በመከላከያው ጉዳይ ላይም አይስማሙም። እንደ ናፖሊዮን እምነት እንስሳቱ ማድረግ ያለባቸው "የጦር መሳሪያዎችን ማግኘት እና ራሳቸውን ማሰልጠን ነበር"። ስኖውቦል ደግሞ "ወደ ጎረቤት እርሻዎች በርካታ ርግቦችን በየጊዜው በመላክ አመፅ እንዲነሳሳ ቅስቀሳ ማድረግ አለብን" ይላል። አንደኛው ራሳቸውን ከጥቃት መከላከል ካልቻሉ በጠላቶቻቸው ድል እንደሚሆኑ ሲከራከር፤ ሌላኛው በየጎረቤት እርሻዎች **አመፅ** ከተቀሰቀሰ ራሳቸውን ለመከላከል የሚያስገድዳቸው ሁኔታ አይፈጠርም ይላል። እንስሳቱ መጀመሪያ ናፖሊዮንን ቀጥሎ ስኖውቦልን አዳመጡ። የትኛው ትክክል እንደሆነ ግን መወሰን አቃታቸው። ይሁንና ሁልጊዜም ስምምነታቸውን የሚያሳዩት መጨረሻ ከተናገረው ጋር ነበር።

እነሆ በተጠናቀቀው የስኖውቦል ፕላን ላይ በሚቀጥለው እሁድ ዊንድሚሉን በመገንባት እና ባለመገንባት ድምፅ ይሰጥበታል። በትልቁ መጋዘን ውስጥ እንስሳቱ ለውሳኔ እንደተሰበሰቡም ስኖውቦል ተነስቶ ዊንድሚሉን መገንባት መጀመር አስፈላጊ ስለመሆኑ ምክንያቶቹን ለጉባኤው አቀረበ - ምንም እንኳን በየመኻሉ በጎቹ ንግግሩን ቢያቋርጡትም።

ናፖሊዮን መልስ ለመስጠት ተነሳ። "ዊንድሚል ከንቱ ነው። የምለግሳችሁ ምክር ማንኛችሁም ብትሆኑ የድጋፍ ድምፃችሁን ለስኖውቦል እንዳትሰጡ ነው" በማለት በርጋታ ተናግሮ ተቀመጠ። ሰላሳ ሰከንድ እንኳን የማይሞላ በመናገሩ በእንስሳቱ አቋም ላይ ተፅእኖ ስለማሳደር አለማሳደሩ ደንታ የሰጠው አይመስልም።

ስኖውቦል አፈፍ ብሎ ሲነሳ ንግግሩን ለማቋረጥ መፈክራቸውን የጀመሩት በጎች ላይ ጮኸባቸው። ዊንድሚሉን መገንባት ለምን እንደሚያስፈልግም በስሜት መናገር ጀመረ። እስካሁን እንስሳቱ በድጋፍ እና በተቃውሞ እኩል ነበር የተከፋፈሉት። የስኖውቦል ጠንካራ ንግግር ቀልባቸውን መቆጣጠር ይዟል። ማራኪ በሆኑ አረፍተ ነገራት አስከፊ የሆነው የጉልበት ስራ ከጫንቃቸው ላይ በሚወርድበት ወቅት ስለሚፈጠረው የእንስሳ እርሻ ውብ ህይወት ተረከላቸው።

ከውቂያ እና የከብት መኖ ሸንሻኝ ከሆነ መሳሪያ ባሻገር በምናቡ መጥቆ ሄደ። "የኤሌክትሪክ ሃይል" አለ ስኖውቦል "የሰብል መውቂያ መሳሪያዎችን፤ ማረሻዎችን፤ መጎልጎያዎችን፤ መዳመጫዎችን፤ ማበጠሪያዎችን እና ማሽጊያዎችን ያንቀሳቅሳል። ለእያንዳንዱ በረት መብራትን፤ ቀዝቃዛ እና ሙቅ ውሃን እንዲሁም የኤሌክትሪክ መሞቂያን ሁሉ ያመነጫል" በማለት አብራራላቸው። ስኖውቦል ንግግሩን እንደጨረሰ እንስሳቱ የድምፅ ድጋፋቸውን ለማን እንደሚሰጡ የሚያጠራጥር አልነበረም።

እነሆ በዚህ ወሳኝ ሰአት ላይ ናፖሊዮን ከተቀመጠበት በመነሳት ስኖውቦልን ልዩ በሆነ የንቀት አስተያየት ተመለከተው። ቀጥሎም እንስሳቱ ከዚህ ቀደም ሰምተውት የማያውቁትን ቀጭን ሰቅጣጭ ድምፅ አውጥቶ ጮኸ።

በዚሁ ቅፅበት አንገታቸው ላይ ቀበቶ ያጠለቁ፣ ዘጠኝ የደለቡ ውሾች እጅግ በሚያስፈራ ድምፅ እየጮሁ፣ በከፍትኛ ፍጥነት ወደ መጋዘኑ ገቡ። በቀጥታም ወደ ስኖውቦል ተወረወሩ። ስኖውቦል ከተቀመጠበት ተስፈንጥሮ ሲነሳ የውሾቹ መንጋጋዎች ለጥቂት ሳቱት። ጊዜ ሳይወስድ በበሩ ተፈትልኮ ወጣ። ውሾቹም ያሳድዱት ጀመር። በድንጋጤ ተሽመድምደው ለመናገር የፈሩት እንስሳት መጨረሻውን ለማየት ተንጋግተው ወደ በሩ ሄዱ።

ስኖውቦል ወደ ዋናው መንገድ ለመድረስ ሜዳውን በሩጫ እያቋረጠ ነበር። አሳማ ሊሮጥ የሚችውን ያህል ይሮጣል፣ ውሾቹ ግን ደርሰውበታል። ድንገት አንሸራትቶት ሲወድቅ ያበቃለት መስሎ ነበር። ወዲው ተነስቶ የነፍስ አውጪኝ ሩጫውን ቀጠለ። ከሚያሳድዱት ውሾች አንዱ ደርሶበት ጭራውን ለቀም ሊያደርገው አፉን ሲከፍት ለጥቂት ዳነ። የቀረውን ጥቂት ርቀት የሙት ሙቱን ሮጦ በቁጥቋጦው በኩል ባገኘው ቀዳዳ ሾልኮ አመለጠ።

እንስሳቱ በፍርሃት እንደተዋጡ በፀጥታ ወደ መጋዘኑ ተመልሰው ገቡ። ወዲያው ውሾቹ መጡ። እንዲህ ያሉ ፍጥረታት ከየት እንደተገኙ እንስሳቱ ግራ ገብቷቸው ነበር። ብዙም ሳይቆዩ መልሱ ተገለጠላቸው። ናፖሊዮን በቡችልነት ዘመናቸው ከእናቶቻቸው ነጥሎ የወሰዳቸውና በግሉ ያሳደጋቸው መሆናቸውን ተገነዘቡ። እድሜያቸው ገና ለጋ ቢሆንም እንደ ተኩላ የሚያስፈሩ ግዙፍ ውሾች ወጥቷቸዋል። ናፖሊዮንን በአይነ ቁራኛ ይጠብቃሉ። ሌሎች ውሾች ለአቶ ጆንስ ጭራቸውን ይቆሉ እንደነበር እነዚህም ለናፖሊዮን እንደዛው ሲያደርጉ ተስተዋሉ።

እነሆ ናፖሊዮን በውሾቹ ታጅቦ አዛውንቱ ሜዠር ንግግር አድርጎ ወደ ነበረበት መድረክ ወጣ። “የእሁድ ስብሰባዎች አላስፈላጊ እና ጊዜ አባካኝ በመሆናቸው ከዛሬ ጀምሮ ታግደዋል” ሲል አወጀ። ከዚህ በኋላ እርሻውን አስመልክቶ የሚነሱ ጥያቄዎች በሙሉ እሱ በሚመራው የአሳሞች ልዩ ኮሚቴ መልስ ይሰጥባቸዋል። እኒህ የኮሚቴ አባላት በግል በሚያካሂዷቸው ስብሰባዎች የተደረሰባቸውን ውሳኔዎች ለሌሎቹ ያሳውቃሉ። ሆኖም እንስሳቱ በየሳምንቱ መሰብሰባቸው ግን አይቀርም፦ ባንዲራ ለመስቀል፣ ‘የእንግሊዝ አራዊት’ን ለመዘመር እና ሳምንታዊውን የስራ ትእዛዛት ለመቀበል። ከእንግዲህ ውይይት የሚባል ነገር በፍፁም አይኖርም።

እንስሳቱ በስኖውቦል መባረር የደረሰባቸው ድንጋጤ ከፍተኛ ቢሆንም የናፖሊዮን ውሳኔዎች ደግሞ ይበልጥ አበሳጪቸው። ትክክለኛውን የመከራከሪያ ነጥብ ቢያውቁ ኖሮ ተቃውሟቸውን ዘርዝረው ባቀረቡ ነበር። ቦክሰር እንኳን ሳይቀር ጉዳዩ ከንክኖታል። ጆሮዎቹን ወደ ኋላው ቀስሮ ጋማውን ደጋግሞ አርገፈገፈ። ሀሳቡን ለማሰባሰብ ሞከረ። ሊናገር የሚችለው ብልጭ ያለለት ሀሳብ ግን ምንም አልነበረም።

ከፊት ለፊት የተቀመጡት አራቱ ወጣት አሳሞች የእሁድ ስብሰባዎች በመታገዳቸው አለመስማማታቸውን ለመግለጥ ሁሉም ባንዴ ተነስተው መናገር ጀመሩ። ወዲያው ናፖሊዮንን ከበው የተቀመጡት ውሾች አስፈሪ ድምፅ እያወጡ ወጣቶቹ አሳሞች ላይ ክራንቻዎቻቸውን አፋጩ። ወጣቶቹም ውሾቹን በመፍራት አፋቸውን ዘግተው ተመልሰው ተቀመጡ። ይህን የተመለከቱት በጎች በጋራ “አራት እግሮች ጥሩ፣ ሁለት እግሮች መጥፎ” የሚለውን መፈክር ያወርዱት ጀመር። ይህም ለሩብ ሰአታት ያህል ቀጠለ። ከዚህ በኋላ በእሁድ ስብሰባ መታገድ ላይ ተቃውሞ የማቅረብ እድል አበቃለት።

ስብሰባው እንደተበተነም ዘግየት ብሎ ስኩለር ስለ አዲሱ ውሳኔና ሃላፊነት ለእንስሳቱ እየዞረ ማብራሪያ እንዲሰጥ ተላከ።

“ጓዶች” ሲል ጀመረ ስኩለር “ጓድ ናፖሊዮን ተጨማሪ የስራ ሃላፊነት በመውሰድ ስለከፈለው መስዋእትነት ሁላችሁም ከልባችሁ የምታደንቁለት ነው ብዬ አምናለሁ። ስልጣን ያስደስታል ብላችሁ ከቶም እንዳታስቡ - ጓዶች። በተቃራኒው እንደ አለት የከበደ ጥልቅ ሃላፊነት እንጂ። ከጓድ ናፖሊዮን በላይ ሁሉም እንስሳት እኩል ናቸው የሚለውን የሚያምን ማንም የለም። እራሳችሁ ስለራሳችሁ የሚበጁችሁን ውሳኔዎች ማስተላለፍ ብትችሉ እጅግ ደስተኛ በሆነ ነበር። ነገር ግን አንዳንዴ የተሳሳተ ውሳኔ ልትወስኑ ትችላላችሁ። ታዲያ ያኔ ምን ይከተላል? አሁን እንደተረዳነው ከወንጀለኞች ያልተሻለውን የስኖውቦልን ‘ላም አለኝ በሰማይ’ ዊንድሚል ቅዠት ተከትላችሁ ቢሆንስ኏ ኖሮ?”

“በላምበረት ጦርነት በጀግንነት ተዋግቷል” አለ አንድ እንስሳ።

“ጀግንነት በቂ አይደለም” ሲል መለሰ ስኩለር *“ታማኝነትና ታዛዥነት ከሁሉም በላይ ዋነኞቹ ናቸው።* በላምበረቱ ጦርነት የስኖውቦል የጀግንነት ሚና እዚህ ግባ የማይባል ግን የተጋነነ ለመሆኑ እውነቱ የሚወጣበት ጊዜ ይመጣል ብዬ አምናለሁ። ዲሲፕሊን፣ ጓዶች፣ እንደ ብረት የጠነከረ ዲሲፕሊን! የዛሬው መሪ ቃል ይህ ነው። አንድ የተሳሳተ ርምጃ፣ ጠላቶቻችንን በላያችን ላይ መልሶ ያመጣብናል። እውነት ጓዶች፣ ጆንስ ተመልሶ እንዲመጣ ትፈልጋላችሁን?”

ይህ የመከራከሪያ ነጥብ መልስ የሌለው ነበር። እንስሳቱ ጆንስ እንዲመለስባቸው ከቶም እንደማይፈልጉ እርግጠኞች ናቸው። በየእሁዶቹ ይካሄድ የነበረው ስብሰባ ጆንስን የሚያመጣባቸው ከነበረ - በርግጥ መታገድ ነበረበት። በዚህ ሎጂክ ጉዳዩን የማሰላሰል ፋታ ያገኘው ቦክሰር የእንስሳቱን አጠቃላይ ስሜት እንደሚከተለው ገለፀ። “ጓድ ናፖሊዮን ከተናገረ፣ እውነት መሆን አለበት”። እነሆ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ “ናፖሊዮን ሁሌም ትክክል ነው” የሚል መፈክር ጀመረ። ይህ እንግዲህ የግሉ መመሪያ መግለጫ ከሆነው “ይበልጥ ጠንክሬ እሰራለሁ” ከሚለው ሌላ መሆኑ ነበር።

ፀደይ ሲገባ የአየሩ ጠባይም ተቀየረ። የእርሻ ወቅት ጀመረ። ስኖውቦል የዊንድሚሉን ፕላን የነደፈበት ዛኒጋባ ተዘግቷል፣ ፕላኑም ከወለሉ ላይ ጠፍቷል ተብሎ በእንስሳቱ ተገምቷል። ዘወትር እሁድ ጠዋት በአስር ሰአት እንስሳቱ በትልቁ መጋዘን እየተሰበሰቡ የሳምንቱን የስራ መመሪያ ይቀበላሉ። የሜዠር የራስ ቅል፣ (አሁን በላዩ ላይ ምንም ስጋ የለበትም) ከተቀበረበት ከፍራፍሬው እርሻ ወጥቶ ከጠመንጃው ጎን ተደርጓል። ከሰንደቅ አላማ ማውጣት ስነስርአት በኋላ፣ እንስሳቱ ወደ መጋዘኑ ከመግባታቸው በፊት በሜዠር የራስ ቅል ፊት ለፊት በሰልፍ ሆነው በጥልቅ የአክብሮት ስሜት ማለፍ ይጠበቅባቸዋል።

አሁን ዘመን እንስሳቱ እንደ ድሮው መጋዘኑ ውስጥ አብረው አይቀመጡም። ናፖሊዮን እና ስኩለር ሚኒመስ ከተባለ ግጥምና መዝሙር የመድረስና የማቀናበር ልዩ ችሎታ ካለው አሳማ ጋር ሆነው መድረክ ላይ ከፊት ለፊት ይቀመጣሉ። ዘጠኙ ቅልብ ጠባቂ ውሾች በግማሽ ክብ ቅርፅ በሶስቱ ዙሪያ ይሆናሉ። የተቀሩት እንስሳት በመጋዘኑ ወለል ላይ ፊቶቻቸውን ወደ ሶስቱ አዙረው ይቀመጣሉ። ከዚያም ናፖሊዮን የሳምንቱን ትእዛዛት በወታደራዊ ድምፅ ያስተላልፍላቸዋል። ‘የእንግሊዝ አራዊት’ መዝሙር አንዴ ተዘምሮ ስብሰባው ይበተናል።

ስኖውቦል በተባረረ በሶስተኛው ሳምንት እሁድ እለት ናፖሊዮን “ዊንድሚል ይገነባል” ብሎ ሲናገር እንስሳቱ በጣም ነበር የተገረሙት። ሃሳቡን የመቀየሩ ምክንያት ምን እንደሆነ የገለፀላቸው ነገር አልነበረም። ለዚህ ተጨማሪ ተግባር ጠንክረው መስራት እንደሚጠበቅባቸው አስጠነቀቃቸው። ምናልባትም የእለት ፍጆታቸውን /ራሽናቸውን/ ሊያስቀንስባቸው እንደሚችልም ገለፀላቸው። ፕላኑ ከሀ እስከ ፐ በሚገባ ተዘጋጅቷል። ላለፉት ሶስት ሳምንታት

የአሳሞች ልዩ ኮሚቴ ይህንኑ ሲሰራ ነበር። የዊንድሚሉ ግንባታ ሌሎች ማሻሻያዎች ተጨምረውበት በሁለት አመት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ተገምቷል።

ያን ምሽት ስኩለር ለሌሎቹ እንስሳት እየዞረ “ናፖሊዮን ዊንድሚሉን የተቃወመው ከልቡ አልነበረም። እንደውም በተቃራኒው ናፖሊዮን ራሱ ነበር የመጀመሪያ ሃሳብ አመንጪው። በእንቁላል መፈልፈያ ዛኒጋባ ወለል ላይ ስኖውቦል የነደፈው ፕላን ከናፖሊዮን ከተሰረቁት ሰነዶች /ዶክመንቶች/ ውስጥ አንዱ ሲሆን ዊንድሚሉም የናፖሊዮን የራሱ ፈጠራ ነበር” በማለት ገለፀላቸው።

የስኩለርን ማብራሪያ ከሰሙት እንስሳት መካከል አንዱ “ታዲያ ለምን ነበር ናፖሊዮን እንደዛ አምርሮ የተቃወመው?” ሲል ጠየቀው።

ስኩለር ምስጢር አዘል ፈገግታን አሳያቸው። ቀጥሎም “ያ የጓድ ናፖሊዮን ዘዴ ነበር። ዊንድሚሉን የተቃወመ የመሰለው አደገኛ ባህሪ የነበረውን እና መጥፎ ተምሳሌ የሆነውን ስኖውቦልን ለማስወገድ የተጠቀመበት ጥበብ ነበር። እነሆ የስኖውቦል እንቅፋትነት ስለተወገደ ፕላኑ ያለሱ ጣልቃ ገብነት ተግባራዊ ይሆናል። ይህ አይነቱ መንገድ ደግሞ ‘ታክቲክ’ ይባላል” በማለት አብራራላቸው፤ ጭራውን ሽው ሽው እያደረገና የደስታ ሳቅ እየሳቀ። “ታክቲክ ጓዶች፤ ታክቲክ” እያለ ደጋገመላቸው።

እንስሳቱ የ’ታክቲክ’ ትክክለኛ ፍቺ አልገባቸውም። ነገር ግን ስኩለር በስሜት ሲናገር እና ጠባቂዎቹ ሶስት ቅልብ ውሾች ደግሞ ዙሪያውን እየተሽከረከሩ የማስፈራሪያ ድምፅ ሲያሰሙ፤ ያለ ተጨማሪ ጥያቄዎች ማብራሪያውን ተቀበሉት።

# ምእራፍ ስድስት

## ዊንድሚል ግንባታ

ሙሉውን አመት እንስሳቱ እንደ ባሪያ ሰሩ። በስራቸው ደስተኞች ከመሆናቸውም በላይ ድካማቸውም ሆነ መስዋእትነታቸው ቅሬታን አልፈጠሩባቸውም። እንዲህ የሚለፉት ደግሞ ለራሳቸው እና ከእነሱ በኋላ ለሚመጡት ትውልዶች ብልፅግና እንጂ ለሌቦቹ መንጋ የሰው ልጆች እንዳልሆነ ተገንዝበዋል።

ፀደዩን እና በጋውን ሙሉ በሳምንት ስልሳ ሰአት ነበር የሚሰሩት። በሀምሌ ወር ናፖሊዮን አዲስ ትእዛዝ አስተላለፈ። ትእዛዙም "ከእንግዲህ እሁድ ከሰአት በኋላ የስራ ጊዜ ይሆናል" የሚል ነበር። ይህ ግን "በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ" ይሆናል ቢባልም ቅሉ ከስራ የቀረ ማንኛውም እንስሳ ግን የቀን አበሉ በግማሽ ይቀነስበታል። በዚህን ወቅት አንዳንድ ተግባራትን ማዘግየት አስፈላጊ ሆኖ ነበር። ምርቱ ከአምናው ሲነፃፀር ቀንሷል። ለምሳሌ ሁለት መስኮች ከበጋው ወራት በፊት ታርሰው ባለመዘጋጀታቸው ሊዘራባቸው አልተቻለም። እናም መጪው ክረምት የችግር ወቅት እንደሚሆን ይገመታል።

የዊንድሚሉ ስራ ያልተጠበቀ ችግር አስከተለ። በእርሻው ጣቢያ በቂ የሆነ ለግንባታ የሚሆን ድንጋይ ሲኖር በግቢው ከሚገኙት ቤቶች ውስጥም በአንደኛው በርካታ አሸዋ እና ሲሚንቶ ተገኝቷል። ለግንባታው የሚያስፈልጉ ነገሮች ዝግጁ ነበሩ። እንስሳቱን የገጠማቸው የመጀመሪያ ፈተና ድንጋዩን እንደምን አድርገው ለግንባታው በሚሆን መልክ እንደሚሰባብሩት ነበር። ከመዶሻ እና ከመከስከሻ የብረት ዘንግ ውጪ መስራት የሚቻል አይመስልም። እነሱ ደግሞ እኒህን መሳሪያዎች መጠቀም አይችሉም። ምክንያቱም የትኛውም እንስሳ በሁለት እግሩ መቆም አይችልምና። እናም ለሳምንታት በከንቱ ከደከሙ በኋላ፤ ከመካከላቸው አንዱ ሀሳብ አፈለቀ። ይህም "የስበት (ግራቪቲ) ሃይልን መጠቀም" የሚል ነበር።

ከባድ እና ትልልቅ መጫኛዎች ከድንጋዩ ማውጫ ስፍራ ላይ ነበሩ። እንስሳቱ እኒህ መጫኛዎችን በገመድ አሰሩዋቸው። ሁሉም በህብረት ላሞች፤ ፈረሶች፤ በጎች፤ ማንኛውም ገመድ መያዝ የቻለ እንስሳ ሁሉ፤ አንዳንድ ጊዜ ወሳኝ በሆነበት ሰአት አሳሞቹም ሳይቀሩ፤ ወደ አለቶቹ አናት እንደ ኤሊ ጉዞ በተንቀራፈፈ ሁኔታ እየጎተቱ ያወጧቸዋል። አናቱ ላይ ደርሰው መጫኛዎቹን ቁልቁል ሲገለብጧቸው ድንጋዩ ወርዶ የአለቱ ወለላ ላይ ይፈረካከሳል። በአንፃሩ የተሰባበረውን ድንጋይ ማጓጓዝ ቀላል ነበር። ፈረሶቹ ጋሪ ሙሉ ይሸከማሉ። በጎቹ የሚችሉትን ያነሳሉ። ሙሬል እና ቤንጃሚን ሳይቀሩ አሮጌ ጋሪ ይዘው በትጋት አጓጓዙ። እነሆ በበጋው ማብቂያ አካባቢ በቂ የሆነ የድንጋይ ክምር ተዘጋጅቶ በአሳሞቹ ካቦነት ግንባታው ተጀመረ።

አዝጋሚና አድካሚ ሂደት ነበር። ብዙ ጊዜ አንድ ጭነት ጎትቶ ከመሰባበሪያው ከፍታ ላይ ለማድረስ የሙሉ ቀን ድካምን ይጠይቃል። አንዳንዴ ደግሞ ከጫፍ ላይ አድርሰው ቁልቁል ሲለቁት ድንጋዩ ሳይሰባበር ይቀራል። ቦክሰር ባይኖር ኖሮ አንዳችም መስራት አይቻልም ነበር። የቦክሰር ጉልበት የእንስሳቱ ሁሉ ተዳምሮ እኩል ይሆናል። ለምሳሌ ትልቁን መጫኛ ሲጎትቱ ከክብደቱ የተነሳ ወደ ኋላ መንሸራተት ይጀምርና እንስሳቱን ይዞ ቁልቁል ሲወርድ፤ ጎታቾቹ በፍርሃትና በጭንቀት ሲጯጯሁ፤ ቦክሰር ግን ጥርሱን ነክሶ ደም

ስሩ እየተግተረተረ፣ እንደምንም ታግሎ ያቆመዋል። ትንፋሹ እየተቆራረጠ፣ ሰውነቱ በላብ ተጠምቆ፣ መሬቱን እየቧጠጠ፣ እርከን በእርከን ጭነቱን እየጎተተ ዳገቱን ሲወጣ የተመለከተው ሁሉ በከፍተኛ አድናቆት ይዋጣል።

አንዳንድ ጊዜ ክሎቨር ራሱን መጉዳት እንደማይኖርበት ትመክረዋለች። ቦክሰር ግን ፍፁም አይሰማትም። "ይበልጥ ጠንክሬ እሰራለሁ" እና "ናፖሊዮን ሁሌም ትክክል ነው" የሚሉት መርሆዎቹን የችግሮች ሁሉ መፍቻ አድርጎ ወስዷቸዋል። ከአንዱ አውራ ዶሮ ጋር ባደረገው ስምምነት ዘወትር ማለዳ ከግማሽ ሰአት በፊት ሳይሆን አርባ አምስት ደቂቃ ከሌሎቹ አስቀድሞ እንዲቀሰቅሰው አድርጓል። ባገኘው ትርፍ ሰአት ሁሉ (ትርፍ ሰአት የሚባል እንኳን የለውም) ወደ ድንጋይ ማውጫው ስፍራ ይወርድና የተሰባበሩ ድንጋዮችን ጭኖ ያለረዳት ዊንድሚሉ ግንባታ ቦታ ድረስ ይወስዳል።

ምንም እንኳን የስራ ጫና ቢበዛባቸውም ቅሉ በነዚያ የበጋ ወራት እንስሳቱ የሚያስከፋ ህይወት ውስጥ አልነበሩም። በጆንስ ዘመን ያገኙት ከነበረው የምግብ መጠን የጨመረ ነገር ባይኖርም፣ ያነሰ ግን አልነበረም። በራሳቸው ላብ ራሳቸውን ብቻ እንጂ አምስት የማይጠረቁ የሰው ልጆችን መቀለብ ማቆማቸው ያጎናፀፋቸው ደስታ ሰፊ ስለነበር የገጠሟቸው ውድቀቶች ደስተኝነታቸውን ሊያደበዝዙት አልቻሉም። በብዙ መልኩ የእንስሳ የአሰራር ዘዴ ይበልጥ የተሻለ እና ጉልበትን የቀነሰ ነበር። ለምሳሌ የአረም ስራ የሰው ልጆች በፍፁም ሊያደርጉት በማይችሉት አይነት ቅልጥፍና እና ጥራት ይከናወናል።

የትኛውም እንስሳ ባሁኑ ጊዜ የማይሰርቅ በመሆኑ፣ የግጦሽ መሬትን ከሰብል እርሻ ለመለየት አጥር ማጠር አስፈላጊ አልነበረም። ይህም ቁጥቋጦ ለመንከባከብ እና የአጥር መዝጊያዎችን ለማደስ ተጨማሪ ጊዜን አትርፏል።

በጋው እየገፋ ሲሄድ የበርካታ ቁሳቁስና ፍጆታ እጥረት እንዳለ ግልፅ መሆን ጀመረ። የፓራፊን ዘይት፣ ምስማሮች፣ መወጠሪያ ገመድ፣ የውሻ ብስኩት፣ የፈረስ ጫማ የሚሰራበት ብረት፣ በበቂ ደረጃ የሉም። እነዚህ ከእርሻው ጣቢያ የሚመረቱ አልነበሩም። የዘር ፍሬ እና ሰው ሰራሽ የማዳበሪያ አስፈላጊነትም እየጨመረ መጣ። የተለያዩ ቀላል መሳሪያዎች እና ለዊንድሚል የሚሆን ከባድ ማሽነሪ አለመኖራቸው አሳሳቢ ሆነ። እኒህ ሁሉ ከየት ሊገኙ እንደሚችሉ ያወቀ አልነበረም።

አንድ እሁድ ቀን፣ እንሰሳቱ ሳምንታዊ ትእዛዛትን ሊቀበሉ እንደተሰበሰቡ፣ ናፖሊዮን ሌላ አዲስ ፖሊሲ ማውጣቱን እና ማፅደቁን ነገራቸው። "ከእንግዲህ *የእንስሳ እርሻ* ጣቢያ ከጎረቤት እርሻዎች ጋር የንግድ ልውውጥ ያደርጋል። ይህ የተወሰነው ባጣዳፊ መልኩ የሚያስፈልጉ እቃዎችን ለማግኘት እንዲያስችል እንጂ በንግድ ለሚገኝ ትርፍ ተብሎ አይደለም። ለዊንድሚል ግንባታ ሲባል ሌላው ነገር ሁሉ ወደ ጎን መገለል አለበት" አለ ናፖሊዮን። "በመሆኑም" ሲል ቀጠለ "የተወሰነ ክምር ጭድ እና ከዚህ አመት የስንዴ ምርት ግማሹ የሚሸጥበትን መንገድ አመቻችቻለሁ። ዘግየት ብሎ፣ ምናልባት ተጨማሪ ገንዘብ ካስፈለገ፣ እንቁላሎችን መሸጥ ሊኖርብን ይችላል፣ ሁሌም በዊሊንግደን የእንቁላል ገበያ አለ። ለዊንድሚል ግንባታ አስተዋፅዖ ሲባል፣ ዶሮዎች ይህንን ልዩ መስዋእትነት መክፈል በመቻላችሁ ልትደሰቱ ይገባችኋል።"

የናፖሊዮን ውሳኔ በእንስሳቱ ህሊና ብዥታን ፈጠረ። ጆንስ እንደተባረረ በተደረገው የድል አድራጊነት ስብሰባ ላይ ከተላለፉት ቀደምት ውሳኔዎች መካከል፦ *ከሰው ልጆች ጋር ምንም ግንኙነት አለመፍጠር፣ ምንም የንግድ ልውውጥ አለማድረግ፣ በገንዘብ በፍፁም አለመጠቀም - የሚሉ አልነበሩበትምን?* አዎ! ሁሉም እንስሳት እንዲያ ያሉ ውሳኔዎችን

ማስተላለፋቸውን ያስታውሳሉ። ወይም ቢያንስ እንዳዛ አይነት ውሳኔዎች እንደነበሩ ትዝ ይላቸዋል።

የእሁድ የውይይት መድረክን ናፖሊዮን በዘጋበት ወቅት ተቃውሞ አሰምተው የነበሩት አራት ወጣት አሳሞች ፈራ ተባ እያሉ በዚህኛው የናፖሊዮን ውሳኔ ላይ ድምፃቸውን ቢያሰሙም ውሾቹ ከፍተኛ የሆነ የቁጣ ድምፅ ማውጣት በመጀመራቸው ተቃውሟቸውን አቁመው ተቀመጡ። ወዲያው በጎቹ "አራት እግሮች ጥሩ፣ ሁለት እግሮች መጥፎ" እያሉ ያነበንቡ ጀመር። በዚህ መኻል ተፈጥሮ የነበረው ያለመረጋጋት ስሜት ሟሸሸ። በመጨረሻም ፀጥታ ይሰፍን ዘንድ ናፖሊዮን አንደኛውን የፊት እግሩን አነሳ። አከታትሎም ለውሳኔው ተፈፃሚነት አስፈላጊውን ዝግጅት ማጠናቀቁን አወጀ። ለእንስሳቱ ደህንነት ሲባል ከሰው ልጆች ጋር አለመገናኘታቸው አስፈላጊ በመሆኑ ከዚህ አንፃር ምንም ስጋት ሊያድርባቸው እንደማይገባ ገለፀላቸው። ይህንን ተጋባራዊ በማድረግ ረገድ ሃላፊነቱን በሙሉ እሱ ይሸከማል።

አቶ ዊምፐር የተባለ የዊሊንግደን ነዋሪ ጠበቃ፣ በ*እንስሳ እርሻ* እና በውጪው አለም መካከል በድልድይነት ለመስራት መስማማቱንና ዘወትር ሰኞ ጠዋትም በእርሻው ጣቢያ እየተገኘ መመሪያዎችን እንደሚቀበል ገለፀላቸው። እንደ ተለመደው ናፖሊዮን ንግግሩን ሲያበቃ "የ*እንስሳ እርሻ* ለዘለዓለም ይኑር!" ብሎ ጮኸ። 'የእንግሊዝ አራዊት' መዝሙር ተዘምሮም ስብሰባው ተበተነ።

ከዚህ በኋላ ስኩለር የእንስሳቱን መንፈስ እንዲያረጋጋ ተላከ። "*የንግድ ልውውጥ አለማድረግ እና በገንዘብ አለመጠቀም* የሚል ውሳኔ አስቀድሞ ተላልፎ እንደማያውቅ እንደውም ሀሳቡም እንዳልቀረበ እርግጠኛ ነኝ" አላቸው። "ፍፁም ህልም ካልሆነ በስተቀር - ምናልባት ገና ከጠዋቱ ስኖውቦል ያሰራጫቸው ከነበሩት ውሸቶች መካከል ሊሆን ይችላል" አለ ስኩለር። ጥቂት እንስሳት የንግግሩን እውነተኛነት ተጠራጠሩ። "ጓዶች፣ ይህ አስተሳሰባችሁ ህልማችሁ ላለመሆኑ እርግጠኞች ናችሁን? ለመሆኑ እንደዛ የሚል ውሳኔ ስለመተላለፉ ማስረጃ አላችሁን? የተፃፈበት ቦታስ የት ነው?" ሲል አፋጠጣቸው። እነሆ በፅሁፍ የተያዘ ማስረጃ አለመኖሩ እውነት በመሆኑ እንስሳቱ መሳሳታቸውን አምነው ተቀበሉ።

ዘወትር ሰኞ በስምምነቱ መሰረት አቶ ዊምፐር የእርሻ ጣቢያውን ይጎበኛል። ግራና ቀኝ የረዘመ ፂም ያለው፣ ብልጣብልጥ ትንሽ ሰው ሲሆን በመጠነኛ ካፒታል ለሚንቀሳቀስ ነጋዴም በጠበቃነት ይሰራል። *የእንስሳ እርሻ* ጣቢያን ከውጪው አለም ጋር የሚያገናኝ ደላላ አስፈላጊ እንደሆን ከሌሎች ቀድሞ የተረዳ ብልህ ከመሆኑም በተጨማሪ ይህንን በማድረጉ የሚያገኘው ኮሚሽን ቀላል አለመሆኑን ተገነዝቧል።

እንስሳቱ ዊምፐር ሲመጣና ሲሄድ በጥላቻ ይመለከቱታል። በተቻላቸው መጠን ከእርሱ ጋር ላለመገናኘት ይርቃሉ። ይሁንና ባለ አራት እግሩ ናፖሊዮን ባለ ሁለት እግሩ ዊምፐርን ትእዛዝ ሲሰጠው ሲመለከቱ ኩራት እየተሰማቸው በተደረገው ስምምነት ላይ የነበራቸው ቅሬታ በከፊል እየቀነሰ ነበር። ከሰው ዘር ጋር ያላቸው ግንኙነት ፍፁም ተቀይሯል።

የሰው ልጆች *የእንስሳ እርሻ* ጣቢያን ቀድሞ ከሚጠሉት ያነሰ አልነበረም ጥላቻቸው። እንደውም አሁን በብልፅግናው ጥላቻቸው የከፋ ሆኗል። "ይዘግይ፣ ይፍጠን እንጂ፣ *የእንስሳ እርሻ* መንኮታኮቱ አይቀርም" የሚል እምነት ነበራቸው። ከሁሉም በላይ የዊንድሚሉ ግንባታ እንዳይሳካ ይፈልጋሉ። በየቤቱ እየተሰበሰቡ ዊንድሚሉ ቢገነባም እንኳን ተመልሶ እንደሚፈርስ ስእል እየሳሉ እርስ በእርሳቸው ይገላለፃሉ። ወይም ደግሞ ግንባታው ቢሳካ መሳሪያው አይሰራም ይላሉ። በዚህ ሁሉ መኻል ግን እንስሳቱ ራሳቸውን በራሳቸው

በማስተዳደር ችሎታቸው በተወሰነም ደረጃ ቢሆን፣ ከፍላጎታቸው ውጪ፣ ከበሬታን ይሰጧቸው ጀምረዋል። ለዚህ አንዱ ዋቢ፣ *የእንስሳ እርሻ* የሚለው ስም እንደሌለ አድርገው በቀድሞው ስሙ "ማኖር እርሻ" እያሉ መጥራታቸውን ማቆማቸው ነበር። ጆንስ በበኩሉ እርሻውን ዳግም እንደማያገኘው ቁርጡን አውቆ አካባቢውን ለቅቆ ሄዷል።

*የእንስሳ እርሻ* እስካሁን ከውጪው አለም ጋር ያለው ግንኙነት በአቶ ዊምፐር በኩል ብቻ ነበር። ነገር ግን በተደጋጋሚ እንደሚሰማው ጭምጭምታ ከሆነ ናፖሊዮን ከፎክስዉድ እርሻ ባለቤት ከአቶ ፒልኪንግተን ወይም ከፒንችፊልድ ባለቤት ከአቶ ፍሬደሪክ ጋር (ከሁለቱ አንዳቸው እንጂ መቼም ከሁለቱም ጋር ግን አይሆንም) የንግድ ልውውጥ ስምምነት ሊያደርግ ተዘጋጅቷል ይባላል።

እነሆ በዚህን ወቅት ነበር አሳሞቹ ሳይታሰብ ጓዛቸውን ጠቅልለው ወደ ዋናው ህንፃ (የቀድሞው አቶ ጆንስ መኖሪያ) የተዘዋወሩት። እንስሳቱ ይህንን መኖሪያ ቤት አስመልክቶ በቀድሞው ጊዜ አንድ የጋራ ውሳኔ ማስተላለፋቸው ትዝ ይላቸዋል። ይሁንና ስኩለር፣ ምንም አይነት ውሳኔ እንዳልተላለፈና ትውስታቸውም የተሳሳተ መሆኑን በመግለፅ አሳመናቸው። የእርሻው ጣቢያ አእምሮ ሞተር የሆኑት አሳሞች ሃላፊነታቸውን በብቃት ይወጡ ዘንዳ ፀጥታማ ስፍራ እንደሚያስፈልጋቸውም ነገራቸው። "ከሁሉም በላይ ለመሪው ክብር ዛኒጋባ ሳይሆን የተስተካከለ ቤት ውስጥ መኖር ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል" ሲል አብራራላቸው ስኩለር። (ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ናፖሊዮንን 'መሪው' /ሊደር/ እያለ መጥራት ጀምሯል።)

አሳሞቹ ምግባቸውን በምግብ ማብሰያ ክፍል መመገብና ሳሎኑንም መዝናኛ ማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን አልጋ ላይ እንደሚተኙም ሲሰሙ እንስሳቱ ተረበሹ። ቦክሰር እንደተለመደው "ናፖሊዮን ሁሌም ትክክል ነው" በሚለው መዝሙሩ ጉዳዩን አቃሎት አለፈ። በመጋዘኑ ግርግዳ ላይ ከተፃፉት ሰባቱ ትእዛዛት አንዱ *አልጋ ላይ መተኛትን የሚያግድ* ለመሆኑ በእርግጠኝነት ያስታወሰችው ክሎቨር ትእዛዛቱን ለማንበብ ወደዛው ሄደች። ከተወሰኑ ሆሄያት በላይ መዝለቅ ባለመቻሏ ሙሬልን ጠራቻት።

"ሙሬል፣ አራተኛውን ትእዛዝ እስቲ አንብቢልኝ፣ አልጋ ላይ መተኛት የተከለከለ ነው አይደለም እንዴ የሚለው?"

ሙሬል ለማንበብ ትንሽ ከተቸገረች በኋላ ሙሉውን አነበበችላት።

**"ማንኛውም እንስሳ አልጋ ላይ መተኛት የለበትም፣** *አንሶላ ለብሶ* " ይላል አለቻት።

የሚገርመው ክሎቨር አራተኛው ትእዛዝ ሲደነገግ *አንሶላ ለብሶ* የሚል ቃል እንዳልነበር ታስታውሳለች። ነገር ግን ሰባቱ ትእዛዛት የሰፈሩበት ግርግዳ ላይ የሚገኘው ይህ የሰማችው ትእዛዝ በመሆኑ የተሳሳተች መሰላት። እንዳጋጣሚ ሆኖ፣ በሁለት ወይም በሶስት ጠባቂ /ቦዲጋርድ/ ውሾች ታጅቦ ያልፍ የነበረው ስኩለር ጉዳዩን በመስማቱ የማያዳግም እልባት ሰጣቸው።

"እኛ አሳሞች በትልቁ ቤት ውስጥ አልጋ ላይ እንደምንተኛ ሰምታችኋላ - ጓዶች? ታዲያ ብንተኛስ? አልጋ ላይ መተኛትን የሚከለክል ህግ አለ ብላችሁ አስባችሁ ይሆን? አልጋ ማለት የመተኚያ ስፍራ ማለት ብቻ ነው። በግርግም ውስጥ የሚገኝ የተነጠፈ ደረቅ ሳር አልጋ ይባላል - በእውነተኛ ትርጉሙ ከሄድን። ህጉ የሚያግደው አንሶላዎችን ነው፣ የሰው ልጅ ፈጠራ ውጤቶችን። አንሶላዎቹን ደግሞ ከህንፃው ውስጥ አስወግደናል። እኛ የምንተኛው ብርድልብስ ብቻ ለብሰን ነው። እርግጥ አልጋዎቹ እጅግ ምቹ ናቸው። ነገር ግን ምቾታቸው ከምንፈልገው በላይ አይደለም፣ ከምንሰራው የአእምሮ ስራ ጋር ሲነፃፀር። ይህንን ልትረዱልን

ይገባል - ጓዶች። በተረጋጋ መንፈስ ለማሰብ የምንችልበትን ሁኔታ ልትገፉን ትፈልጋላችሁን? ሃላፊነታችንን በድካም ምክንያት በብቃት እንዳንወጣ ትሻላችሁን? መቼም ጆንስ ተመልሶ እንዲመጣ የሚፈልግ ይኖር ይሆን?"

እንስሳቱ የጆንስ ስም ሲነሳባቸው ስኩለር በተናገረው ሁሉ መስማማታቸውን ወዲያው ገለፁለት። እነሆ ከዚህ በኋላ አሳሞቹ አልጋ ላይ የመተኛታቸው ጉዳይ አጠያያቂነቱ አከተመለት። እናም ጥቂት ቀናት እንዳለፉ *"አሳሞች ከእንቅልፋቸው የሚነሱት ሌሎች እንስሳት ከተነሱ ከአንድ ሰአት በኋላ ይሆናል"* የሚለው አዋጅ ሲወጣ የተቃወመ አልነበረም።

በልግ በገባ ጊዜ እንስሳቱን የስራ ድካም ቢጫናቸውምና አመቱም አስቸጋሪ የፈተና ወቅት ቢሆንባቸውም ቅሉ ደስተኞች ግን ነበሩ። ከጭድና ከበቆሎ ሽያጭ ተገዝቶ በማከማቻው የሚገኘው ምግብ ምንም እንኳን ብዛት ባይኖረውም ዊንድሚሉን በግማሽ ገንብተው መጨረስ መቻላቸው አካክሶላቸዋል። ከሰብል ወቅት በኋላ ረጅም የድርቅ ጊዜ ተከተለ። የእንስሳቱም ስራ ከመቼውም በላይ በእጥፍ ጨመረ። ቀኑን ሙሉ ከላይ እታች ድንጋይ እያመላለሱ የዊንድሚሉን ግርግዳ በአንድ ክንድም እንኳን ቢሆን ከፍ ለማድረግ ፍዳቸውን ሲያዩ ይውላሉ። ቦክሰርማ ጨረቃ ስትወጣም እየሄደ አንድና ሁለት ሰአት ብቻውን ይሰራል።

እንስሳቱ በትርፍ ጊዜያቸው በግማሽ የተጠናቀቀውን ግንባታቸውን ዙሪያውን እየዞሩ፤ የግርግዳውን ጥንካሬና ቀጥተኝነት በማድነቅ እንዲህ ያለ ታላቅ ግርማ ሞገስ ያለውን ግንባታ ማከናወን በመቻላቸው ይደሰታሉ። ሽማግሌው ቤንጃሚን ብቻ ነበር የዊንድሚሉ ግንባታ ደንታ ያልሰጠው። እንደተለመደው "አህዮች ብዙ ዘመን ይኖራሉ" ከሚለው አጭር አስተያየቱ በቀር ሌላ ነገር አይናገርም።

እነሆ ከደቡብ - ምእራብ በመጣ አደገኛ ንፋስ ታጅቦ ህዳር ገባ። በእርጥበት ምክንያት ሲሚንቶ መቀላቀል የማይቻል በመሆኑ የዊንድሚሉ ግንባታ መቆም ነበረበት። አንድ ቀን ሌሊት አገር ምድሩን ያናወጠ ንፋስ ተነሳ። የእርሻውን ጣቢያ ህንፃዎች መሰረት አናጋ። በርካታ የበረት ጣራ ነቃቀለ። ዶሮዎቹ በፍርሃት ኳኳታቸውን አቀለጡት፤ ምክንያቱም ሁሉም በህልማቸው ከሩቅ ስፍራ የተተኮሰ የጠመንጃ ድምፅ ሰምተው ነበርና። ነግቶ እንስሳቱ ከየማደሪያዎቻቸው ሲወጡ የሰንደቅ አላማው መስቀያ ወድቆና በፍራፍሬው እርሻ የሚገኘው ዛፍ ከስሩ ተመንግሎ አገኙ። ወዲያው ደግሞ ከእያንዳንዱ እንስሳ የሰቆቃ ጩኸት ተሰማ። ማመን የሚያስቸግር ትእይንት ነበርና ያዩት፤ ዊንድሚሉ ፈራርሶ።

እየተሯሯጡ ዊንድሚሉ ግንባታ ስፍራ ደረሱ። አዎ! እውነት ነበር። የዛ ሁሉ ድካማቸው ውጤት ከመሰረቱ ተንዷል። እንደዛ ላባቸውን እያንጠፈጠፉ ሲሰባብሩና ሲሸከሙት የነበረው ድንጋይ በያለበት ተበታትኗል። መናገር አቅቷቸው፤ በድንጋጤ ፈዘው፤ ፍርስራሹ ላይ አፍጥጠው ቀሩ። ናፖሊዮን ወደ ላይና ወደ ታች በፀጥታ ይንጎራደዳል። አልፎ አልፎ መሬቱን ያሸታል። ጭራው ቀጥ ብሎ ከግራ ወደ ቀኝ ይንቀጠቀጣል፤ በጥልቅ ሀሳብ ላይ እንደሆን የሚያመለክት ነበር። ድንገት መንጎራደዱን አቆመ። አንዳች ውሳኔ ላይ የደረሰ ይመስላል።

"ጓዶች" ሲል በዝግታ ጀመረ። "ለዚህ ጥፋት ተጠያቂው ማን እንደሆን ታውቃላችሁ? ጨለማን ተገን አድርጎ በመምጣት ዊንድሚሉን ያፈረሰውን ጠላታችንን ታውቁታላችሁን?" ሲል ጠየቀ። ቀጥሎ እንደ ነጎድጓድ በሚያስገመግም ድምፅ "ስኖውቦል" በማለት ጮኸ። "ይህንን የፈፀመው ስኖውቦል ነው። በምቀኝነት። ፕላናችንን ለማጨናገፍና መባረሩን ለመበቀል ሲል ይህ ከሃዲ ጨለማ ለብሶ በመምጣት ለአንድ አመት ገደማ የደከምንበትን

ግንባታ አወደመው። ጓዶች፤ በስኖውቦል ላይ እዚህና አሁን የሞት ቅጣት ወስኜበታለሁ። ለፍርድ እንዲቀርብ ለሚያደርግ እንስሳ ግማሽ እንቅብ አፕል እና 'የጀግና እንስሳ ሁለተኛ ደረጃ' ሜዳሊያ ይሸለማል። ከነህይወቱ ይዞት ለሚያመጣው ደግሞ  እንቅብ ሙሉ አፕል ይሸለማል" በማለት ናፖሊዮን አስታወቀ።

እንስሳቱ ስኖውቦል እንዲህ ያለ ወንጀል መፈፀሙ ሲነገራቸው ድንጋጤያቸው ወደር አልነበረውም። በውስጣቸው የበቀል ስሜት ተቀሰቀሰባቸው። እናም ስኖውቦል ከእንግዲህ ቢመጣ እንዴት አድርገው እጅ ከፍንጅ እንደሚይዙት በየፊናቸው ያሰላስሉ ጀመር። ብዙም ሳይቆይ ከጉብታው ጥቂት ርቀት በሳሩ ላይ የአሳማ እግር አሻራ ተገኘ። አሻራውን ጥቂት ሜትሮች እንደተከተሉት ከቁጥቋጦው አቀራቢያ ካለ ጉርጓድ ሲደርስ ይቆማል። ናፖሊዮን አሻራዎቹን በጥልቅ አሽትቶ "የስኖውቦል ናቸው" ሲል ጮኸ። ስኖውቦል ከፎክስዉድ እርሻ አቅጣጫ ሳይመጣ እንዳልቀረም አስተያየቱን ሰጠ።

"ከቶም ቢሆን ወደ ኋላ አንመለስም!" ሲል ጮኸ ናፖሊዮን - የእግር አሻራውን ከመረመረ በኋላ። "ተልእኮ አለብን። ዛሬውኑ የዊንድሚሉን ግንባታ እንጀምራለን። ፀሀይ ወጣ፤ ዶፍ ወረደ፤ እስከ ክረምት ድረስ ዘልቀንም ቢሆን እንገነባለን። ይህ ከንቱ ከሃዲ አላማችንን እንዲህ በቀላሉ ማጨናገፍ እንደማይችል ትምህርት እንሰጠዋለን። ልብ በሉ ጓዶች! በእቅዳችን ላይ አንዳችም ለውጥ አናደርግም። በታቀደው የጊዜ ሰሌዳ ይጠናቀቃል። ወደፊት ጓዶች! ዊንድሚል ለዘላለም ይኑር! *የ እንስሳ እርሻ* ለዘላለም ይኑር!"

# ምእራፍ ሰባት

## አምባገነናዊነት

እጅግ የከፋ ክረምት ነበር። ነጎድጓዳማው የአየር ፀባይ በዶፍና በበረዶ ተተካ። ይህም በተራው እስከ የካቲት የዘለቀ ውርጭ አስከተለ። የውጪው አለም ትኩረት እነሱ ላይ መሆኑን በመገንዘባቸውና ደግሞም የዊምድሚሉ ግንባታ በታቀደለት ወቅት ባይጠናቀቅና ቢከሽፍ ምቀኞቹ የሰው ልጆች በደስታ ጮቤ እንደሚረግጡ በማወቅ፤ እንስሳቱ የቻሉትን ያህል የዊንድሚሉን ግንባታ አካሄዱ።

የሰው ልጆች *ለእንስሳ እርሻ* ካላቸው ጥላቻ የተነሳ ስኖውቦል ለዊንድሚሉ መፍረስ ተጠያቂ አይደለም ብለው ያምናሉ። "የዊንድሚሉ ግርግዳዎች በቂ ውፍረት ስላልነበራቸው ነበር የፈራረሱት" ይላሉ። እንስሳቱ ግን ይህ ሀሰት መሆኑን ያውቃሉ። ይሁንና እንደፈራረሰው ግርግዳ አስራ አምስት ኢንች ሳይሆን የአሁኑ ዊንድሚል ግርግዳ ውፍረት ሶስት ጫማ እንዲሆን ተወስኗል። ይህ ማለት ብዙ ድንጋይ መሰብሰብ ነበረባቸው። የድንጋይ ማውጫው ለረጅም ወቅት በበረዶ ብናኝ ተሸፍኖ በመክረሙ ምንም መስራት አልተቻለም።

በውርጫማው የደረቁ አየር ወቅት መጠነኛ የሆነ ግንባታ ቢያካሂዱም እጅግ አስከፊ ከሆነው የስራው ፀባይ ጋር ተዳምሮ እንስሳቱ በዊንድሚሉ ግንባታ ላይ ብሩህ ተስፋ አይታያቸውም ነበር። ምክንያቱም ሁሌም እንደበረዳቸው ነበር። ቦክሰርና ክሎቨር ብቻ ተስፋ መቁረጥ አይታይባቸውም። ስኩለር ስለ ስራ ክቡርነትና ይህም ስለሚሰጠው ደስታ ምርጥ ዲስኩሮች ቢያደርግላቸውም እንስሳቱ ግን ከእሱ ዲስኩር ይልቅ የቦክሰር ጥንካሬና "የበለጠ እሰራለሁ" የሚለው መርሆው ነበር የሚያነቃቃቸው።

ጥር ውስጥ የምግብ እጥረት ገባ። የበቆሎ ቀለብ /ራሽን/ በእጅጉ ቀነሰ። ይህንንም ለማካካስ ተጨማሪ የድንች ቀለብ ይታደላል ተባለ። ሆኖም አብዛኛው የድንች ተክል በሚገባ ተሸፍኖ ባለመቆየቱ በውርጩ ሳቢያ መበላሸቱ ተገለፀ። ድንቾቹ የሞቀሞቁና መልካቸውንም የቀየሩ በመሆናቸው ለምግብነት የሚውለው ጥቂት ብቻ ሆነ። ለተከታታይ ቀናት እንስሳቱ ከደረቅ ሳር በስተቀር የሚመገቡት ነገር አልነበራቸውም። እነሆ ከረሀብ ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጡ።

ድርቅ መግባቱንና ረሀብ መሆኑን ከውጪው አለም እውቀት መደበቅ ፍፁም አስፈላጊ ነበር። የዊንድሚሉን መፈራረስ አስታከው የሰው ልጆች *በእንስሳ እርሻ* ላይ አዲስ የፈጠራ ወሬ ዘመቻ ጀምረዋል። "እንስሳቱ በድርቅና በበሽታ እያለቁ ናቸው" በማለት ያስወራሉ። "እርስ በርሳቸው ይጣላሉ፤ አንዱ የሌላውን ስጋ ይበላል፤ የህፃናት ሞት በርክቷል" ይላሉ።

*በእንስሳ እርሻ* ድርቅ መግባቱን የውጪው አለም ቢያውቅ የሚያስከትለውን መጥፎ ውጤት ናፖሊዮን ጠንቅቆ ተረድቷል። እናም ተፃራሪ ወሬ ለማሰራጨት አቶ ዊምፐርን በመሳሪያነት ሊጠቀምበት ወሰነ።

እንስሳቱ እስከ አሁን ከዊምፐር ጋር ምንም አይነት አካላዊ ግንኙነት አልነበራቸውም። አሁን ግን ጥቂት የተመረጡ እንስሳት፣ በአብዛኛው በጎች፣ በአቶ ዊምፐር አካባቢ በመገኘት እንደዋዛ እያደረጉ የቀለብ ጭማሪ እንደተደረገላቸው እንዲያወሩ ታዘዙ። ከዚህ ሌላ ርጋፊ ባቄላ ብቻ የቀረባቸው ድብኝቶች በሙሉ በአሸዋ እንዲሞሉና ርጋፊው ባቄላ በላያቸው እንዲነሰነስ ናፖሊዮን ትእዛዝ አስተላለፈ።

በተለያዩ አስባቦች ዊምፐር የእህል ድብኝቶቹ በሚገኙበት በኩል እንዲያልፍ ተደርጎ እስካፍጢማቸው በባቄላ የተሞሉትን ድብኝቶች እንዲመለከት ተደረገ። እነሆ ዊምፐር በአይኑ ያየውን አመነ። ለውጪው አለምም፣ "*በእንስሳ እርሻ ድርቅ አልገባም፣ የምግብ እጥረትም የለም*" እያለ መስበክ ጀመረ።

ጥር መገባደጃ ላይ ተጨማሪ ጥራጥሬ ማግኘት እንደሚኖርባቸው ግድ ሆነ። በዚህ ወቅት ናፖሊዮን አደባባይ የሚታየው እጅግ አልፎ አልፎ ነበር። ጊዜውን የሚያሳልፈው በትልቁ ህንፃ ውስጥ ሲሆን፣ የህንፃውም እያንዳንዱ በር በአደገኞቹ ውሾች ይጠበቃል። ከህንፃው ከወጣም እንኳን ስድስት ውሾች ዙሪያውን አጅበውት በንቃት እየጠበቁትና ማንም እንዳይጠጋው በማስፈራራት ነበር። ለበርካታ ሳምንታት እሁድ ጠዋት ታይቶ የማያውቅ ሲሆን፣ ትእዛዞቹን የሚያስተላልፈው ከአሳሞቹ መካከል በአንዱ ፣ አብዛኛውን ጊዜ ግን በአፈቀላጤው በስኩለር በኩል ነበር።

አንድ እሁድ ጠዋት፣ ስኩለር "ዶሮዎች ሁሉ ከዛሬ ጀምሮ የሚጥሏቸውን እንቁላሎች ማስረከብ አለባቸው" የሚል ትእዛዝ መውጣቱን ተናገረ። "ናፖሊዮን ከዊምፐር ጋር በተዋዋለው ስምምነት መሰረት በሳምንት አራት መቶ እንቁላሎች ለገበያ ይቀርባሉ። ከሽያጩ በሚገኘው ገቢ ሁኔታዎች እስኪሻሻሉ ድረስ እስከ በጋው የሚዘልቅ ጥራጥሬና ምግብ ለእርሻው ጣቢያ ይገዛል" አላቸው ስኩለር።

ዶሮዎቹ ይህንን ሲሰሙ ኡኡታቸውን አቀለጡት። ቀደም ሲል እንዲህ ያለ መስዋእትነት ሊከፍሉ እንደሚችሉ የተነገራቸው ቢሆንም ተግባራዊ ይሆናል የሚል እምነት አልነበራቸውም። እነሱ በፀደይ ወቅት ለሚፈለፍሏቸው ጫጩቶች መታቀፊያዎቻቸውን በማዘገጃጀት ላይ ነበሩ። "በእንዲህ ያለ ጊዜ እንቁላሎቻችንን መውሰድ ግድያ እንደመፈፀም ማለት ይሆናል" ሲሉ አምርረው ተቃወሙ። ከጆንስ መባረር በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ አመፅ የተቀሰቀሰ መሰለ።

ዶሮዎቹ በሶስት ጥቋቁር የስፓኒሽ ዶሮዎች እየተመሩ የናፖሊዮንን እቅድ ለማክሸፍ ቆርጠው ተነሱ። ከትግላቸውም ስልቶች አንዱ ቆጦቻቸው ላይ በረው በመውጣት እንቁላሎቻቸውን ከላይ በመጣል ወለሉ ላይ ወድቀው እንዲሰባበሩ ማድረግ ነበር። ናፖሊዮን ፈጣንና ቆራጥ እርምጃ ወሰደ። የዶሮዎቹ ቀለብ በ አስቸኳይ እንዲቆም ትእዛዝ አስተላለፈ። "የትኛውም እንስሳ አንዲት ፍሬ እንኳን ሰጥቷቸው ቢገኝ በሞት ይቀጣል" ሲል አወጀ። ለአዋጁ አስፈፃሚነትም ውሾቹ ተመደቡ።

ዶሮዎቹ ለአምስት ቀናት በቆራጥነት ቢታገሉም በመጨረሻ ግን ድል ሆነው እንቁላሎችን ወደየሚጥሉባቸው ሳጥኖች ውስጥ መግባት ተገደዱ። በዚህ ፍልሚያ ዘጠኝ ዶሮዎች ሞተዋል።ሬሳቸውም ከፍራፍሬው እርሻ ላይ ተቀበረ። አሟሟታቸው በዶሮ በሽታ ምክንያት ነበር በሚል ተገለፀ። ዊምፐር ስለሆነው ነገር ሁሉ ምንም ፍንጭ አልነበረውም። በሳምንት አንድ ቀን የግሮሰሪ መጫኛ መኪና ይዞ እየመጣ እንቁላሎቹን ይረከባል።

ይህ ሁሉ ሲደረግ የስኖውቦል ድምፅ አልተሰማም። ከጎረቤት እርሻዎች ወይ በፎክስዉድ አልያም በፒንችፊልድ ተደብቋል የሚል ጭምጭምታ አለ። ናፖሊዮን በዚህን ወቅት ከሌሎች ገበሬዎች ጋር በመጠኑም ቢሆን በመልካም ግንኙነት ላይ ይገኝ ነበር። ከአስር አመት በፊት መለስተኛው ጫካ ሲመነጠር ዛፎቹ ተቆርጠውና ተሸንሽነው የተከመረ ጣውላ በእርሻው ጣቢያ ይገኛል። ዊምፐር ይህንን ተመልክቶ ናፖሊዮን ጣውላዎቹን እንዲሸጥ አማከረው።

አቶ ፒልኪንግተን እና አቶ ፍሬደሪክ ጣውላዎቹን የመግዛት ፍላጎት ነበራቸው። ናፖሊዮን ከሁለቱ የቱን እንደሚመርጥ ግን መወሰን አልቻለም። ከፍሬደሪክ ጋር ስምምነቱን ሊቋጭ ሲቃረብ፣ ስኖውቦል የተደበቀው ፎክስዉድ ውስጥ መሆኑ ይነገራል። ከፒልኪንግተን ጋር ሲደራደር ደግሞ ስኖውቦል ፒንችፊልድ መመሸጉ ይነገራል።

በፀደይ መጀመሪያ ሳይታሰብ አስደንጋጭ ሁኔታ ተሰማ። "ስኖውቦል በምስጢር ዘወትር ምሽት *የእንስሳ እርሻን* ይጎበኛል" ተባለ። እንስሳቱ ከመሸበራቸው የተነሳ በየማደሪያቸው መተኛት አልቻሉም። እንደሚወራው ከሆነ ስኖውቦል ጨለማን ተገን አድርጎ በመምጣት የተለያዩ አሻጥሮችን ይፈፅማል። በቆሎ ይሰርቃል። የወተት ማከማቻውን ይገለብጣል። እንቁላሎችን ይከሰክሳል። ማሳውን እየዘለለ ይረጋግጣል። የፍራፍሬ ተክሎችን ልጥ ይግጣል።

እነሆ *በእንስሳ እርሻ* ጣቢያ ለሚፈጠረው ችግር ሁሉ ስኖውቦል ተጠያቂ መሆኑ ይነገር ጀመር። መስኮት ቢሰበር ወይም የውሃ መውረጃ ቧንቧ ቢደፈን የስኖውቦል አሻጥር ለመሆኑ ወንጅሎት የሚናገር ሁሌም ይኖራል። የማከማቻው ክፍል በር ቁልፍ ጠፋ ሲባል ሁሉም ስኖውቦል ወስዶት ጉርጓድ ለመጨመሩ እርግጠኞች ነበሩ። ምንም እንኳን ጠፋ የተባለው ቁልፍ ከተከመረ ምግብ ስር ቢገኝም፣ እንስሳቱ ግን በቀድሞው እምነታቸው ፀኑ።

ላሞቹ እንዳስታወሱት፣ ስኖውቦል በረታቸው ውስጥ በሌሊት እየገባ በህልማቸው ሲያልባቸው ያድራል። በዛን ክረምት ችግር ፈጣሪ ሆነው የተገኙት አይጦች ከስኖውቦል ጋር ሽርክና ነበራቸው ተባለ።

ናፖሊዮን በስኖውቦል ጉዳይ ሙሉ ምርመራ እንዲካሄድ ወሰነ። በጠባቂ ውሾቹ ታጅቦ፣ እንስሳቱ በተወሰነ ርቀት እየተከተሉት፣ የእርሻውን ህንፃዎች እየተዘዋወረ ጎበኘ። "የስኖውቦልን ኮቴ በማሽተት አውቃለሁ" ስላለ በየተወሰኑ ሜትሮች እየቆመ መሬቱን ያሸታል። በየጠመዝማዛው፣ በየግርግዳው ዙሪያ፣ በላሞች በረት፣ በዶሮዎች ቆጦች፣ በአትክልት እርሻ ሁሉ የስኖውቦል ዱካ ጠረን ተገኘ። ናፖሊዮን አፍንጫውን ከመሬት አስጠግቶ በጥልቀት አየር ከሳበ በኋላ በሚያስፈራ ድምፅ "ስኖውቦል! እዚህ ነበር! ልዩ ጠረኑን አሸተትኩት!" ይላል። የስኖውቦል ስም ሲጠራ ሁሉም ጠባቂ ውሾች ጥርሶቻቸውን አግጥጠው ደም የጠማው ጩኸት ያሰማሉ።

ይህ በሚሆንበት ሰአት እንስሳቱ በፍርሃት ይርዳሉ። ስኖውቦል ዙሪያቸውን የከበባቸውና ለብርቱ አደጋ ያጋለጣቸው የማይታይ ክፉ መንፈስ መስሎ ታያቸው። ያን እለት ምሽት ስኩለር ለስብሰባ ጠራቸው። በተረበሸ ገፅታ አሳሳቢ በሆነ ጉዳይ ላይ ሪፖርት እንደሚያቀርብላቸውም ነገራቸው።

"ጓዶች" ሲል ጮኸ ስኩለር ባልተረጋጋ ስሜት እየነጠረ። "እጅግ አስከፊ ሁኔታ ተፈጥሯል። ስኖውቦል ለፒንችፊልድ ባለቤት ለፍሬደሪክ ቅጥረኛ ሆኗል። በዚህች ሰ አት የእርሻ ጣቢያችንን ለማጥቃትና ከእኛ ለመንጠቅ እያሴሩ ይገኛሉ። ጥቃቱ ሲጀመር ስኖውቦል በግንባር ቀደም ጠቋሚነት ይሰለፋል። ሆኖም ከዚህም የከፋ ነገር አለ። የስኖውቦል ማመፅ ከደካማነቱና ከስልጣን ፍላጎቱ የመነጨ መስሎን ነበር። ለካስ ተሳስተናል፣ ጓዶች።

*እውነተኛ ምክንያቱ ምን እንደሆን ታውቃላችሁን? ስኖውቦል ከጆንስ ጋር ገና አህዱ ሲባል ጀምሮ ግንኙነት ነበረው። ስኖውቦል የጆንስ ሰላይ ነበር። ይህንንም በቅርቡ ባገኘነውና እሱ ጥሎት በሸሸው ዶክመንቶች አረጋግጠናል። ለእኔ ህሊና ይህ ብዙ እውነቶችን አስጨብጦኛል። አልተሳካለትም እንጂ፣ በላምበረቱ ጦርነት ቢቻለው ኖሮ እንድንሸነፍና እንድንደመሰስ ጥረት አድርጎ እንደነበር አላየንምን?"*

*እንስሳቱ ዞረባቸው። ይህ የስኩለር መረጃ ዊንድሚሉን ከማፍረስ በላይ የሆነ ወንጀል ነበር። ሆኖም የክሱ መንፈስ የገባቸው ዘግይቶ ነበር። ሁሉም አስታወሱ፣ ወይም ያስታወሱ መሰላቸው። በላምበረቱ ጦርነት ስኖውቦል እንዴት በግንባር ቀደምትነት እንደተዋጋ፣ እንደምን አድርጎ ያደፋፍራቸውና ያበረታታቸው እንደነበር፣ የጆንስ ጥይት ትከሻውን ጭሮት እየደማ እንኳን ለቅፅበት ሳይቆም ወደፊት ተንደርድሮ እንደነበር ትዝ አላቸው። ሆኖም ይህ ትውስታቸው የጆንስ ሰላይ ነበር ከሚለው ጋር እንዴት እንደሚስማማ ሊገባቸው አልቻለም። ጥያቄ የማያበዛው ቦክሰር እንኳን ሳይቀር በጉዳዩ ግራ ተጋባ። ጋደም አለ። የፊት እግሮቹን አጥፎ ደረቱ ስር አደረጋቸው። አይኖቹን ጨፍኖ ሃሳቡን ለመግራት ሞከረ።*

*"የተባለውን ማመን አልችልም" አለ። "ስኖውቦል በላምበረቱ ጦርነት በጀግንነት ተዋግቷል። በአይኔ በብረቱ አይቼዋለሁ። ጦርነቱ እንዳበቃ 'የእንስሳ ጀግና አንደኛ ደረጃ ' ሜዳሊያ ሸልመነው አልነበረምን?"*

*"ስህተታችን እዛ ላይ ነበር፣ ጓድ። አሁን እንዳወቅነው (ባገኘናቸው ምስጢራዊ ዶክመንቶች ላይ ሁሉም ነገር ተፅፏልና) በድርጊቱ ግን ወደ መቃብራችን እየወሰደን ነበር።"*

*"ቆስሎ ነበር" አለ ቦክሰር "ደሙን እያንዠቀዠቀ ሲዋጋ ሁላችንም አይተናል።"*

*"ያ'ማ የሚስጢራዊው ስምምነታቸው አንዱ አካል ነበር።" ሲል ጮኸ ስኩለር። "የጆንስ ጥይት ጭሮት ብቻ ነበር ያለፈው። ማንበብ ብትችል ኖሮ ይህንን በፅሁፍ የሚገኝ ስምምነታቸውን አሳይህ ነበር። በሴራው መሰረት ስኖውቦል በጦርነቱ ወሳኝ ሰአት ለውጊያ ምልክት ሰጥቶን እሱ ከመድረኩ ለመሰወር ነበር። በጀግናው መሪያችን ጓድ ናፖሊዮን ምክንያት እንጂ፣ አላማው ተሳክቶለት ነበር ማለት እችላለሁ፣ ጓዶች። ጆንስና ሰዎቹ ገና ወደ ግቢያችን እንደገቡና ውጊያው እንደተጀመረ ስኖውቦል ቀኛኋላ ዞሮ ሲፈረጥጥ ሁሉም እንስሳት እንዴት እንደተከተሉት አታስታውሱምን? ደግሞስ በድንጋጤ ተረብሸን፣ ሁሉም ነገር ያበቃለትና ሽንፈታችንም እውን የሆነ በመሰለበት በዛን ፈታኝ ቀውጢ ሰአት ላይ አልነበረምን ጓድ ኖፖሊዮን 'ሞት ለሰው ዘር' ብሎ ወደፊት በመወርወር የጆንስን ባት በጥርሶቹ የሰቀሰቀው? መቼም ያንን የማያስታውስ ከቶስ ይኖራልን?" ሲል በ አድናቆት ጠየቃቸው፣ ከጎን ወደ ጎን እየነጠረ።*

*እነሆ ስኩለር ባደረገላቸው ስእላዊ ገለጣ ሳቢያ እንስሳቱ የሆነውን ሁሉ አስታወሱ። አዎ! በዛን የጦርነቱ ጭንቅ ሰአት ስኖውቦል መፈርጠጡ ትዝ አላቸው። ቦክሰር ግን የስኖውቦል ፍርጠጣ ታሪክ አሁንም ሊዋጥለት አልቻለም።*

*"ስኖውቦል ገና ከጠዋቱ ጀምሮ ከሀዲ ነበር ብዬ አላምንም። ከዛ በኋላ የሰራው ስራ ሌላ ጉዳይ ነው። ነገር ግን በላምበረቱ ጦርነት ወቅት ጥሩ ጓድ ነበር።" አለ ቦክሰር፣ በመጨረሻ።*

*"መሪያችን ጓድ ናፖሊዮን" ሲል ጀመረ ስኩለር፣ በርጋታና ቃላቱን እየረገጠ "በማያሻማ፣ አዎ ፍፁም በማያሻማ መንገድ እንደገለጠው፣ ስኖውቦል ከጅምሩ አንስቶ የጆንስ ሰላይ ነበር - አዎ፣* ***አመፅ*** *ከመታሰቡ ብዙ ዘመን አስቀድሞ ሰላይ ነበር።"*

"አኽ፣ ይህማ ሌላ ጉዳይ ነው!" አለ ቦክሰር። "ጓድ ናፖሊዮን ከተናገረ፣ እውነት መሆን አለበት።"

"እንዲህ ነው ሀቀኝነት፣ ጓድ!" ሲል ጮኸ ስኩለር። ይህንን ሲናገር በነዚያ ተርገብጋቢ አይኖቹ ጤናማ ባልሆነ አስተያየት ቦክሰርን እንደተመለከተው ተስተውሎ ነበር። ስኩለር ፊቱን አዙሮ ጥቂት ሜትሮች ሄዶ ተመለሰ። ቀጥሎም "በዚህ እርሻ ላይ የሚገኝ እንስሳ ሁሉ በንቃት እንዲጠባበቅ አስጠነቅቃለሁ። የስኖውቦል ሰላዮች የሆኑ ሰርጎ ገቦች በመኻከላችን ይኖራሉ ብለን የምናምንባቸው በቂ ምክንያቶች አሉን።" በማለት አስገራሚ ንግግር አደረገ።

ከአራት ቀናት በኋላ፣ ጀንበር እንዳዘቀዘቀች ናፖሊዮን እንስሳቱ ሁሉ በመስኩ ላይ እንዲሰበሰቡ አዘዘ። እንስሳቱ እንደተሰበሰቡም፣ ናፖሊዮን በደረቱ ላይ ሁለት ሜዳሊያዎችን አንጠልጥሎ (በቅርቡ 'የእንስሳ ጀግና አንደኛ ደረጃ' እና 'የእንስሳ ጀግና ሁለተኛ ደረጃ' ሜዳሊያዎችን ለራሱ ሸልሞ ነበርና)፣ አስፈሪና ቅልብ በሆኑት ዘጠኝ ውሾች ዙሪያውን ተከቦ፣ ጠባቂዎቹም ደም እንደጠማቸው ሁሉ እየደነፉ፣ ከትልቁ መኖሪያ ቤት ብቅ አለ።

በስብሰባው ላይ የተገኙት እንስሳትም በጀርባቸው ነጭ ላብ ይወርድ ጀመር። ሁሉም በፍርሃት ዝምታ ተዋጡ። ታላቅ መከራ እንደሚከሰትም የታያቸው ይመስላል።

ናፖሊዮን ቆፍጣና አቋቋም ቆሞ ተሰብሳቢዎቹን ከዳር እስከ ዳር ቃኛቸው። ቀጥሎም የሚሰቀጥጥ ከፍተኛ ድምፅ አሰማ። ወዲያው ውሾቹ ወደ ፊት ተወርውረው አራት አሳሞችን ጆሮዎቻቸውን ነክሰው፣ በፍርሃትና በስቃይ እያስጮሁዋቸው ጎትተው ናፖሊዮን እግር ስር ጣሉዋቸው። ከአሳሞቹ ጆሮዎች ደም ይንዠቀዠቃል። ደም የቀመሱት ውሾችም እንደ እብድ አድርጓቸዋል። ሌሎች ሶስት ውሾች ቦክሰር ላይ መዝለላቸው እንደ ተአምር ታየ።

ቦክሰር አመጣጣቸውን እንደተመለከተ ግዙፍ ሸኾናውን አንስቶ አንዱን ቅልብ ውሻ በአየር ላይ ቀለበው። ተጠቅልሎ እግሩ ስር ወደቀ። ምህረት እንዲያደርግለት ቢጮህም ረግጦ ያዘው። ይህንን የተመለከቱት ሁለቱ ውሾች ጭራዎቻቸውን ቆልፈው ወደ መጡበት ተመለሱ። ቦክሰር በሸኾናው ረግጦ የያዘውን ውሻ ሊጨርሰው ወይም ነፃ ሊለቀው ይችል እንደሁ ለማወቅ ናፖሊዮንን ተመለከተው። የናፖሊዮን ገፅታ ተቀያየረ። ውሻውን እንዲለቀው ቁጣ አዘል ትእዛዝ ሰጠው። የተለቀቀው ውሻ እያቃሰተ ተመለሰ። የተነሳሳው አለመረጋጋትም በዚሁ በረደ።

አራቱ አሳሞች በፍርሃት እየተንቀጠቀጡ ቀጣዩን ይጠባበቁ ጀመር። በገፅታቸው ጥፋተኝነት ይነበብባቸዋል። ናፖሊዮን ወንጀሎቻቸውን እንዲናዘዙ ጠየቃቸው። እኒህ አራት ወጣት አሳሞች ናፖሊዮን የእሁድን ስብሰባ ባገደ ጊዜ ተቃውሞ ያቀረቡ ነበሩ። እናም በፍርሃት የተዋጡት አሳሞች መናዘዝ ጀመሩ።

ከተባረረው ስኖውቦል ጋር በምስጢር ግንኙነት እንዳላቸው፣ ዊንድሚሉን በማፍረስ ከስኖውቦል ጋር እንደተባበሩ፣ *የእንስሳ እርሻን ለአቶ ፍሬደሪክ ለማስረከብ ከስኖውቦል ጋር መፈራረማቸውን እና ስኖውቦል ከአያሌ አመታት ጀምሮ የጆንስ ሰላይ መሆኑን* እንደገለፀላቸው - ተናዘዙ። ኑዛዜያቸውን እንደጨረሱ ውሾቹ ጉሮሮዎቻቸውን ዘነጠሏቸው። ቀጥሎ ናፖሊዮን እጅግ በሚያስፈራ ድምፅ ከመኻከላቸው ወንጀሉን የሚናዘዝ ሌላ እንስሳ መኖር አለመኖሩን ጠየቃቸው።

የእንቁላሎችን መወረስ በመቃወም የዶሮዎችን አመፅ የመሩት ቀንደኞቹ ሶስቱ ጥቋቁር ዶሮዎች ለኑዛዜ ቀረቡ። በናፖሊዮን ትእዛዝ ላይ ለማመፃቸው ምክንያቱ ስኖውቦል በህልማቸው ተከስቶ ባደረገላቸው ቅስቀሳ ሳቢያ መሆኑን ተናዘዙ። ኑዛዜያቸውን እንደጨረሱም አንገቶቻቸውን ተቀነጠሱ።

ቀጥሎ ዳክዬ ቀረበች። ባለፈው የመኸር ወቅት አራት የበቆሎ እሸቶችን በምስጢር ወስዳ ማታ ማታ እየበላች መጨረሷን አመነች። በግ ቀጠለች። በስኖውቦል ግፊት በመጠጥ ውሃ ጉድጓድ ውስጥ መሽናቷን ተናገረች። ሁለት በጎች ደግሞ - በጉንፋን ህመም ይሰቃይ የነበረን የናፖሊዮን ታማኝ ተከታይ የሆነን ያልተኮለሸ ሽማግሌን በግ በደመራው እሳት ዙሬያ እያባረሩ ለሞት እንደዳረጉት አመኑ። የሁሉም ተናዛገሮች እጣ ፈንታ ሞት ሆነ።

እነሆ አየሩ በደም ጠረን እስኪበከል፣ በናፖሊዮን እግር ስርም የሬሳ ክምር እስኪቆለል ድረስ ኑዛዜና ግድያው ያለማቋረጥ ቀጠለ። እንዲህ ያለ መአት ጆንስ ከተባረረ ወዲህ ታይቶ አያውቅም ነበር።

ግድያውና ኑዛዜው ሲያበቃ ሁሉም እንስሳት በአንድነት (ከአሳሞቹና ከውሾቹ በስተቀር) አንገታቸውን ደፍተው ተነስተው ሄዱ። መንፈሳቸው በሽብር፣ ሰውነታቸው በፍርሃት ርዷል። የተናዘዙት እንስሳት ከስኖውቦል ጋር መመሳጠራቸውን መግለፃቸው ይሁን ወይም በአይናቸው የተመለከቱት አሰቃቂ ጭፍጨፋ፣ ከሁለቱ የትኛው ህሊናቸውን እንዳሸበራቸው ግን ማወቅ አልቻሉም። በድሮ ጊዜም ቢሆን አሰቃቂ የደም ማፍሰስ ጭካኔ ነበር። ይሁንና የአሁኑ እርስ በርሳቸው የመሆኑ ጉዳይ ሁኔታውን የከፋ እንዳደረገው ይሰማቸዋል።
ጆንስ ከእርሻው ጣቢያ ከተባረረ ወዲህ፣ እስከዚህ ቀን ድረስ፣ የትኛውም እንስሳ ሌላ እንስሳን አልገደለም። አይጥ እንኳን ተገድሎ አያውቅም። እንስሳቱ ሁሉ ተያይዘው በግማሽ የተጠናቀቀው ዊንድሚል ወደሚገኝበት ኮረብታ ወጡ። ብርድ እንዳንዘፈዘፋቸውና ሙቀት እንደሚፈልጉ ሁሉ፣ ሁሉም በአንድነት ተቃቅፈው ተጋደሙ - ክሎቨር፣ ሙሬል፣ ቤንጃሚን፣ ላሞቹ፣ በጎቹ፣ ዳክዬዎቹና ዶሮዎቹ ሁሉ። ድመት ግን በመኻከላቸው አልነበረችም። ናፖሊዮን የስብሰባውን ትእዛዝ ከማስተላለፉ አስቀድማ ነበር በድንገት ተነስታ የጠፋችው።

እርጭ ያለ ፀጥታ ሰፈነ። ማንም ምንም አልተናገረም። ቦክሰር ብቻ ነበር ጋደም ያላለው። ጥቁር፣ ረጅም ጭራውን ግራና ቀኝ እያወናጨፈ፣ አልፎ አልፎም የመገረም ማጉተምተም እያሰማ ይንጎራደዳል።

"ፍፁም ሊገባኝ አልቻለም። እንዲህ ያለ ነገር በእኛ እርሻ ውስጥ ይፈፀማል የሚል ሀሳብ አልነበረኝም። በውስጣችን ባለ የራሳችን ስህተት መሆን አለበት። እኔ እንደሚታየኝ ከሆነ፣ መፍትሂው የበለጠ ጠንክሮ መስራት ነው። ከዛሬ ጀምሮ ጠዋት ጠዋት አንድ ሰአት አስቀድሜ እነሳለሁ።" አለ ቦክሰር በመጨረሻ።

ይህንን ተናግሮ ወደ ድንጋይ ማውጫው ሄደ። ሁለት ጭነት ድንጋይ አመላልሶ ሲያበቃ ተኛ።

እንስሳቱ በክሎቨር ዙሪያ ተሰባሰቡ። በመካከላቸው ግን ንግግር አልነበረም። የተጋደሙበት ጉብታ የእይታቸውን አድማስ ባላገር ድረስ ፍንትው አድርጎ ያሳያቸዋል። የእንስሳ እርሻ አብዛኛው ክልልም ይታያቸዋል። እስከዋናው መንገድ የሚዘልቀው ረጅሙ የእርሻ መሬት፣ አውድማው፣ መለስተኛው ጫካ፣ የመጠጥ ውሃው ጉድጓድ፣ ያጋሸበ የገብስ እርሻ፣ የህንፃዎቹ ቀያይ ጣራዎችና ከየጭስ መውጫው የሚተምመው ጭስ፣ ይህ ሁሉ ይታያቸዋል።

ጥርት ያለ የፀደይ ምሽት ነበር። ቄጤማውና ቁጥቋጦው ቀድሞ ባረፈባቸው የፀሀይ ጨረር ሳቢያ አብረቅርቀው ይታያሉ። ይህ የሚያዩት እርሻ፣ ከዚህ ቀደም ተሰምቷቸው የማያውቅ ልዩ የሆነ እርካታን በውስጣቸው ፈጠረ። በዚህ ስሜት ውስጥ እንዳሉም እርሻው የእነሱ መሆኑን፣ እያንዳንዱ ኢንች የእነርሱ ንብረት እንደሆነም - ድንገት በግርምት አስታወሱ። ክሎቨር ዳገቱ ላይ ሆና ቁልቁል ስትመለከት አይኖቿ በእንባ ተሞሉ። ስሜቷን መናገር ብትችል ኖሮ እንደሚከተለው ነበር የምትገልፀው፦

*ከአመታት በፊት የሰውን ልጅ ለማስወገድ የተነሱትና ለራእያቸው እውን መሆን የታገሉት ዛሬ የተከሰተው ይሆናል ብለው አልመው አልነበረም፣ በዛን ምሽት አዛውንቱ ሜዠር **ለአመፁ** ሲያነሳሳቸው ተስፋ ያደረጉትና ያለሙት ይህ ዛሬ የተካሄደውን ጭፍጨፋና ሽብር እናያለን ብለው አልነበረም፣ ራእያቸው ከረሀብና ከግርፋት ነፃ የሚሆኑበት፣ የእኩልነት መብታቸው የተረጋገጠበት፣ እያንዳንዱ የችሎታውን ያህል የሚሰራበት፣ ብርቱው ደካማውን የሚደግፍበት (ሜዠር ንግግሩን ባደረገበት ምሽት እናታቸው ጠፍታባቸው ሲንከራተቱ የነበሩትን ዔጩት ዳክዬዎች እንደተንከባከበቻቸው)፣ የእንስሳት ስርአት እንዲፈጠር ነበር ህልማቸው። በተቃራኒው፣ ለምን እንደሆን ባይገባትም - ማንም የልቦናውን መናገር የማይደፍርበት ወቅት ላይ ደርሰዋል። አደገኛና አፋኝ ውሾች አገር ምድሩን ተቆጣጥረውት አስደንጋጭ የሆነ ወንጀል መፈፀማቸውን የተናዘዙ ጓዶችን ያለርህራሄ ሲተለትሏቸው እያዩ አንገታቸውን የደፉበት ዘመን ውስጥ ገብተዋል። በአእምሮዋ **የአመፅ** ወይም የእንቢተኝነት ሀሳብ የላትም። ነገሮች አሁን ባሉበት ሁኔታ ቢሆኑም እንኳን ከዘመነ ጆንስ በኢያሌው የተሻለ ዘመን ውስጥ እንዳሉ ታውቃለች። ከሁሉም በላይ ግን የሰው ዘር ተመልሶ እንዳይገዛቸው ማድረጉ እጅግ አስፈላጊ ነበር። የመጣው ቢመጣ በእርሷ በኩል ታማኝነቷ አይጓደልም። ጠንክራ ትሰራለች። የሚሰጣትንም ትእዛዛት ትፈፅማለች። የናፖሊዮንን ትእዛዛት ትቀበላለች። ይህ ሁሉ ይሁንና ግን፦ **እሷና ሌሎቹ እንስሳት ተስፋ ያደረጉትና የደከሙት ለዚህ ብለው አልነበረም። ዊንድሚሉን የገነቡትና የጆንስን ጠመንጃ የተጋፈጡት ለዚህ ብለው አልነበረም።***

ውስጣዊ ስሜቷን በቃላት ድርድር መግለፅ ቢያዳግታትም የክሎቨር ሀሳቦች እንዲህ ነበሩ።

በመጨረሻም፣ የልቦናዋን መግለፅ የሚያስችሉ ቃላትን ማውጣት አለመቻሏን የሚተካላትን 'የእንግሊዝ አራዊት' መዝሙርን ትዘምር ጀመር። በዙሪያዋ የተቀመጡት እንስሳትም አጀቧት። ከዚህ ቀደም ከቶም ዘምረውት በማያውቁት ግሩም ቅላፄ፣ ነገር ግን በሀዘን ተውጠው፣ በዝግታ ሶስት ጊዜ ደጋግመው ዘመሩት።

ለሶስተኛ ጊዜ ዘምረው እንደጨረሱ ስኩለር በሁለት ውሾች ታጅቦ፣ የሚያስተላልፍላቸው መልእክት ይዞ የመጣ በሚመስል ገፅታ ቀረባቸው። "በጓድ ናፖሊዮን ልዩ ትእዛዝ 'የእንግሊዝ አራዊት' መዝሙር ከእንግዲህ ታግዷል። ከዛሬ ጀምሮ 'የእንግሊዝ አራዊት'ን መዘመር ተከልክሏል" በማለት አዋጁን አስተላለፈላቸው።

እንስሳቱ በድንጋጤ ደርቀው ቀሩ።

"ለምን?" ስትል ጮኸች ሙሬል።

"ከእንግዲህ አስፈላጊነቱ አክትሟል፣ ጓድ" አላት ስኩለር ቆፍጠን ብሎ። "የ እንግሊዝ አራዊት **የአመፁ** ማነሳሻ መዝሙር ነበር። አሁን **አመፁ** ግቡን መትቷል። ዛሬ ከቀትር በኋላ በከሃዲዎች ላይ የተወሰደው የማያዳግም ርምጃ የመጨረሻው ምእራፍ ነበር። በውጪ እና በውስጥ ያሉ ጠላቶቻችን በሙሉ ተደምስሰዋል። 'የእንግሊዝ አራዊት'ን ስንዘምር የነበረው

መጪውን የተሻለ ስርአት በመመኘት ነበር። እነሆ ያ የምንመኘው ስርአት አሁን ተመስርቷል። እናም ይህ መዝሙር በዚህ ስርአት ውስጥ ቦታ የለውም።”

እንስሳቱ በፍርሃት ቢሸበቡም ቅሉ አንዳንዶቹ ተቃውሞ ማሰማታቸው አይቀርም ነበር። ነገር ግን ልክ ከስኩለር አዋጅ ቀጥሎ በጎቹ “አራት እግሮች ጥሩ፤ ሁለት እግሮች መጥፎ” በማለት እንደተለመደው ማላዘን ጀመሩ። ይህም ለረጅም ደቂቃዎች በመቀጠሉ በአገዳው ላይ ሊነሳ ይችል የነበረውን ውይይት እልባት ሰጠው።

እነሆ ‘የእንግሊዝ አራዊት’ መዝሙር ከዛን ወዲህ ተዘምሮ አያውቅም። በምትኩ ሚኒመስ ገጣሚው አሳማ ሌላ ግጥምና ዜማ አዘጋጀ።

*የእንስሳ እርሻ፤ የእንስሳ እርሻ*
*የመጣው ቢመጣ፤ እኔ አንቺን አልጎዳም እስከ መጨረሻ!*

ይህ መዝሙር ዘወትር እሁድ ጠዋት ባንዲራ ሲወጣ ይዘመራል። ለእንስሳቱ ግን ቃላቱም ሆኑ ዜማው ‘የእንግሊዝ አራዊት’ን ያህል ትርጉም ሊሰጣቸው አልቻለም።

# ምእራፍ ስምንት

## ኢኮኖሚስት ስኩለር

በተካሄደው ግድያ ሳቢያ የተፈጠረው መሸበር ጋብ እንዳለና ጥቂት ቀናት እንዳለፉ እንስሳቱ ስድስተኛውን ትእዛዝ አስታወሱ። ወይም ያስታወሱ መሰላቸው። *"ማንኛውም እንስሳ ሌላ እንስሳን መግደል የለበትም"*። ምንም እንኳን በአሳሞቹና በውሾቹ ፊት ይህንን ትእዛዝ ባያነሱትም፤ የተካሄደው ጭፍጨፋ ከዚህ ትእዛዝ ጋር የማይጣጣም መሆኑ ግን ተሰምቷቸዋል።

ክሎቨር ቤንጃሚንን ስድስተኛውን ትእዛዝ እንዲያነብላት ጠየቀችው። እሱ ግን እንዲህ ያለ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ እንደማይገባ ገለፀላት። ሙሬል አነበበችላት፤ ትእዛዙን። ***"ማንኛውም እንስሳ ሌላ እንስሳን መግደል የለበትም** - ያለ ምክንያት "* ይላል። በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እንስሳቱ የመጨረሻዎቹን ሁለት ቃላት ሊያስታውሷቸው አልቻሉም። ሆኖም አሁን ትእዛዙ አለመጣሱን ከፅሁፉ ተመለከቱ። ከስኖውቦል ጋር የተመሳጠሩት ከሀዲዎች በትእዛዙ መሰረት ለመገደላቸው በቂ ምክንያት እንዳለ ተገነዘቡ።

ያን አመት እንስሳቱ ከአምናው ይበልጥ ጠንክረው ሰሩ። ከመደበኛ ስራቸው ጋር ተጣምሮ ዊንድሚሉን ዳግም መገንባትና በታቀደለት የጊዜ ሰሌዳ መጨረስ ለዛውም ከቀድሞው ውፍረቱ ሶስት እጥፍ የሆነ ግርግዳ ያለው፤ ይህ ለእንስሳቱ እጅግ ከባድ የስራ ጫና ነበር። አንዳንዴ ከዘመነ ጆንስ ይበልጥ ረጅም ሰአታት እንደሚሰሩ፤ የምግብ ፍጆታቸውም ከዛን ዘመኑ ምንም ያልጨመረ መሆኑ ይሰማቸዋል።

ዘወትር እሁድ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ስኩለር ረጅም ሊስት ያለው ሪፖርት ይዞ ይቀርባል። በሪፖርቱ መሰረት *የእርሻው ጣቢያ የምግብ ዘር ምርት በሙሉ በሁለት መቶ ፐርሰንት፣ በሶስት መቶ ፐርሰንት፣ ወይም በአምስት መቶ ፐርሰንት (እንደ ሁኔታውና እንደ ጊዜው) መጨመሩን ያነብላቸዋል።*

**ከአመፁ** በፊት ስለነበረው የእድገት አሃዝ ዘገባ ምንም የሚያውቁት ነገር ባለመኖሩ የስኩለርን የምርት እድገት አሃዝ ዘገባ ላለማመን የሚያበቃ ምክንያት አልነበራቸውም። በበኩላቸው ግን የስኩለር የምርት እድገት አሃዝ ዝርዝር ቀንሶ ምግብ ቢበዛላቸው ፍላጎታቸው ነበር።

እነሆ በአሁኑ ዘመን ትእዛዛት ሁሉ የሚተላለፉት ወይ በስኩለር አልያም ከ አሳሞቹ በአንደኛው በኩል ሆኗል። ናፖሊዮን በአስራአምስት ቀን አንዴ እንኳን አደባባይ አይታይም።

አደባባይ ከወጣም በቅልብ ጠባቂ ውሾቹ ታጅቦ ብቻም አልነበረም። "ኩኩሉኡኡኡኡ" እያለ እንደ ጥሩንበኛ የሚያገለግል አውራ ዶሮ ከፊት ለፊት እየተራመደ የናፖሊዮንን መምጣት ያበስራል። ንግግር ከማድረጉም በፊት ይኸው አውራ ዶሮ "ኩኩሉኡኡኡኡ" በማለት ናፖሊዮን ንግግር ሊያደርግ መዘጋጀቱን ያስታውቃል።

በትልቁ መኖሪያ ህንፃ ውስጥ ናፖሊዮን የራሱ ብቻ የሆኑ ክፍሎች ይዟል ይባላል። ምግቡን የሚመገበው በሁለት ውሾች እየተጠበቀ ለብቻው እንደሆንና የሚመገበውም ከባለ መስታወቱ የእቃ መደርደሪያ ውስጥ ከሚገኙት መካከል "ክራውን ደርቢ" በሚባል ልዩ የሆነ ሳህን መሆኑም ይወራል። ከሁለቱ የተለያዩ በአላት በተጨማሪ በናፖሊዮን የልደት ቀን ጠመንጃ የሚተኮስ ለመሆኑ በአዋጅ ተነግሯል።

እንደ ቀድሞው ዘመን ናፖሊዮንን በስሙ ብቻ መጥራት አክትሟል። አሁን ዘመን ስነስርአት በያዘ የፕሮቶኮል አጠራር "መሪያችን ጓድ ናፖሊዮን" ተብሎ ይጠራል። መቼም አሳሞቹ የማይፈለስፉለት ስም አልነበረም። የእንስሳት ሁሉ አባት፣ የሰው ዘር አርበድባጅ፣ የበጎች ተከላካይ፣ የዳክዬዎች ወዳጅ፣ ሌላም፣ ሌላም ይሉታል።

ስኩለር ስለ ናፖሊዮን ሊቅነት፣ ስለ ሩህሩህና አዛኝ ልቡ፣ በአለም ዙሪያ ለሚገኙ እንስሳት - በተለይም ደግሞ በድንቁርና እና በባርነት በየእርሻዎቹ ለሚኖሩት ሁሉ - ስላለው ጥልቅ ፍቅር ንግግር ሲያደርግ ፊቱ በእንባ ጎርፍ እየታጠበ ነበር። ለተገኙት መልካም ውጤቶችና አጋጣሚዎች ሁሉ ምስጋናውን ለናፖሊዮን ማኸሮጎድጎድ የተለመደ ሆኗል።

"በመሪያችን በጓድ ናፖሊዮን አመራር በስድስት ቀን ውስጥ አምስት እንቁላሎች ለመጣል በቃሁ" በማለት አንዲት ዶሮ ለጓደኛዋ ስታወራ ወይም ደግሞ ሁለት ላሞች ከገንዳ ውሃ እየጠጡ "እድሜ ለጓድ ናፖሊዮን አመራር ይሁንና! ይህ ውሃ እንዴት ማር፣ ማር ይላል!" ሲባባሉ መስማት የተለመደ ሆኗል።

በእርሻው ጣቢያ ያለውን አጠቃላይ ስሜት አሳማው ሚኒመስ በገጠመውና ባቀረበው "ጓድ ናፖሊዮን" በተሰኘው ስነ ግጥም ተንፀባርቋል፣ እንደሚለተው

የአባት አልባዎች ጓደኛ!
የደስታ ምንጭ መገኛ!
የአሳሞች ምግብ ባልዲ ጌታ! ዋ፣ እንደምን መንፈሴ
አንተን በማየት ተነሳሳ
ከአይኖችህ ጨረር ርጋታና በራስ መተማመን የሚታይ፣
እንደ ሰማይቷ ፀሀይ፣
ጓድ ናፖሊዮን!
ቸርነትህ የትና የት
ፍጡራንህ የሚወዱትን ሁሉ ስትመፀውት፣
በቀን ሁለቴ በጥጋብ ተበልቶ፣ ንፁህ ድርቆሽ ለመኝታ ሰጥቶ፣

ደካማ ይሁን ብርቱ አውሬ ሁሉ
የሰላም እንቅልፍ በየማደሪያቸው ይተኛሉ፣
አቤቱ ጠባቂ ነህ አንተ የሁሉ
ጓድ ናፖሊዮን!

በጨቅላነቱ ጡት ሳቢ አሳማ
እነሆ አድጌ ሆኛለሁ ጡንቻማ
ቢያክልም ሚጢጢ፤ ወይም የስፒል ራስ
ሊማር የሚገባው፤
ላንተ ታማኝና ሀቀኛ መሆን ነው፤
አዎ፤ እንደበቱን መፍቻው፤ ቀዳማይ ቋንቋው
ስምህን መጥራት ነው፤
ጓድ ናፖሊዮን!

እነሆ ናፖሊዮን ግጥሙን አፀደቀ። ሰባቱ ትእዛዛት ከተፃፉበት ትልቁ መጋዘን ግርግዳ ላይ በሌላኛው ወገን ይፃፍም ዘንድ ፈቀደ። ስኩለር በነጭ ቀለም የናፖሊዮንን ከፊል ገፅታ የሚያሳይ ስእል ከሽኖ ከግጥሙ ጎን ተሰቀለ።

በዊምፐር ኤጀንሲ በኩል ናፖሊዮን ከፍሬደሪክ እና ፒልኪንግተን ጋር ውስብስብ የሆነ ድርድሩን ቀጥሏል። የተከመረው ጣውላ ገና አልተሸጠም። ከሁለቱ መካከል ጣውላዎቹን ለማግኘት ፍሬደሪክ ይበልጥ ፍላጎት ነበረው። ግን አመርቂ ዋጋ አልሰጠም። ከዚህ ሌላ ፍሬደሪክና ሰዎቹ *የእንስሳ እርሻን* ዳግም በማጥቃት፤ የቅናት በሽታ የለቀቀበትን የዊንድሚል ግንባታ ለመደምሰስ የማሴሩ ጭምጭምታ ይሰማል። ስኖውቦል በፒንችፊልድ እርሻ እንደመሸገ መሆኑም ይወራል።

በበጋው ወራት ላይ እንስሳቱን ሁሉ ያሸበረ ዜና ተሰማ። ስኖውቦል ባደረገላቸው ቅስቀሳ ተነሳስተው ሶስት ዶሮዎች ናፖሊዮንን ለመግደል አቅደው እንደነበር ራሳቸውን በማጋለጥ አመኑ። ወዲያው የሞት ቅጣት ተፈፀመባቸው። ናፖሊዮንን ከገዳዮች ለመከላከልም ተጨማሪ ጥንቃቄዎች ተወሰዱ። አራት ውሾች ናፖሊዮን ሲተኛ አልጋውን ከበው (እያንዳንዳቸው በየአንዳንዱ ያልጋው ጠርዝ) ይጠብቁታል። ፒንክአይ የተባለ አሳማ የናፖሊዮን ምግብ ያልተመረዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ናፖሊዮን ከመመገቡ በፊት ቀማሽ ሆኖ ተመደበ።

በዚህ መኻል ናፖሊዮን ለአቶ ፒልኪንግተን ጣውላዎቹን ለመሸጥ መስማማቱንና እንዲሁም *በእንስሳ እርሻ* እና በፎክስዉድ እርሻዎች መካከል የተወሰኑ የምርት ልውውጦች እንዲካሄዱ ቋሚ ውል ሊገባ መሆኑም እየተነገረ ነበር። በናፖሊዮንና በፒልኪንግተን መካከል ያለው ግንኙነት በዊምፐር ድልድይነት ቢሆንም መልካም ወዳጅነት የሰፈነበት ነበር። እንስሳቱ ፒልኪንግተንን ሰው እንደመሆኑ ባያምኑትም ከፍሬደሪክ ግን ይመርጡታል። እንስሳቱም ሆኑ ፒልኪንግተን ፍሬደሪክን አብዝተው ይፈሩታልም፤ ይጠሉታልም።

በጋው እያለቀ፤ የዊንድሚሉም ግንባታ እየተጠናቀቀ ሲመጣ የጦርነት ወሬ በሰፊው ይናኝ ጀመር። እንደወሬው ከሆነ ፍሬደሪክ ሃያ ሰዎችን ጠመንጃ አስታጥቆ *የእንስሳ እርሻን* ለመውረር አቅዷል። ለአቃቤ ህግ እና ለፖሊስ ጉቦ የሰጣቸው ሲሆን *የእንስሳ እርሻን* ወርሮ ከያዘ በኋላ በባለቤትነት ጉዳይ ጥያቄ እንዳይነሳበት ሁኔታዎችን አመቻችቷል ይባላል። ከዚህ ሁሉ በላይ ከፒንችፊልድ እርሻ እንደሚወጣው ዜና ከሆነ ፍሬደሪክ በሚያስተዳድራቸው እንስሳት ላይ ይህ ነው የማይባል አሰቃቂ በደል እያደረሰባቸው ይገኛል።

“ሽማግሌ ፈረስ ደብድቦ ገድሏል። ላሞችን በረሃብ ይቀጣል። እሳት ውስጥ ወርውሮ የውሻ ህይወት አጥፍቷል። አውራ ዶሮዎች ምላጭ አፋቸው ላይ ታስሮ እርስ በርሳቸው እንዲጣሉ በማድረግ ማታ ማታ ይዝናናባቸዋል” ይባላል። እንስሳቱ በጓዶቻቸው ላይ እየደረሰ ያለውን የግፍ ዜና ሲሰሙ ደማቸው ተንተከተከ። ፒንችፊልድን በማጥቃት የጓዶቻቸውን

በደል ለመበቀልና ነፃ ለማውጣት ፈቃድ እንዲሰጣቸው ጠየቁ። ስኩለር ግን እንዲረጋጉና ከግብታዊነት ይልቅ በጓድ ናፖሊዮን ስትራቴጂ እንዲያምኑ መከራቸው።

ይህም ሆኖ እንስሳቱ ለፍሬደሪክ ያላቸው ጥላቻ እየጦዘ ነበር። አንድ እሁድ ቀን ናፖሊዮን በመጋዘን ተገኝቶ ክምር ጣውላውን ለፍሬደሪክ ለመሸጥ አስቦ እንደማያውቅ ነገራቸው። ፍሬደሪክን ከመሰለ ወሮበላ ጋር ለመደራደር ክብሩ የማይፈቅድለት መሆኑንም ገለፀላቸው። የአመፅ እሳት በፎክስዉድ እርሻ እንዲለኮስ ለመቀስቀስ አሁን ድረስ ይላኩ የነበሩት ርግቦች ከእንግዲህ ወደ ፎክስዉድ እርሻ በረራ እንዳያደርጉ ታገዱ። “ሞት ለሰው ዘር” የሚለው የቀድሞው መፈክራቸው “ሞት ለፍሬደሪክ” በሚል እንዲተኩት ታዘዙ።

በበጋው መገባደጃ ሌላ የስኖውቦል አሻጥር ይፋ ሆነ። የስንዴው ማሳ በሙሉ በ አረም ተበክሏል። ስኖውቦል ከሚያደርጋቸው ምስጢራዊ ጉብኝቶች ባንዱ ያረም ዘር ከበቆሎ ዘር ጋር መቀላቀሉ ተደርሶበታል ተባለ። የሴራው ተሳታፊ የነበረ ተባእት ዳክዬ ሃጢያቱን ለስኩለር ተናዞ የመርዝ ፍሬ በመብላት ራሱን ገደለ።

ብዙዎቹ እንስሳት እስከአሁን ያምኑት እንደነበረው ሳይሆን ስኖውቦል ‘የእንስሳት ጀግና አንደኛ ደረጀ’ ሜዳሊያ በፍፁም እንዳልተሸለመ ተነገራቸው። “ከላምበረት ጦርነት በኋላ ስኖውቦል ሆን ብሎ ያሰራጨው ወሬ እንጂ ሜዳሊያ መሸለሙ እውነተኛ ታሪክ አይደለም” ተባለ። ከባለማእረግነትም ወርዶ እንደውም “በጦርነቱ ወቅት በፈሪነቱ ተግሳፅ ተሰጥቶታል” ተብሎ ተወራ። አንዳንድ እንስሳት የሰሙትን ለማመን ቢያዳግታቸውም ስኩለር ግን የማስታወስ ችሎታ ችግር እንዳለባቸው ገልፆላቸው የተወራው እውነት ለመሆኑ አሳመናቸው።

በልግ ውስጥ፣ እጅግ አድካሚና ፈታኝ ከሆነ ጥረት በኋላ (በዚህ ወቅት ምርት የሚሰበሰብበትም ጊዜ ነበርና) የዊንድሚሉ ግንባታ ተጠናቀቀ። ማሽኑ ግን ገና መተከል ነበረበት። ይህንን ለመግዛት በዊምፐር በኩል ድርድር እየተካሄደ ነበር፣ ሆኖም ዋናው ስራ አብቅቷል። መሰናክሎች ቢበዙም፣ የልምድ እጥረት ቢኖርም፣ ኋላ ቀር የሆነ አገነባብ ቢሆንም፣ መጥፎ አጋጣሚና የስኖውቦል አሻጥሮች የተባሉት
ቢደራረቡባቸውም - ስራው ግን በታቀደለት ጊዜ ተጠናቀቀ! አካላዊ ድካም ቢኖርባቸውም፣ በውጤታቸው ኩራት የተሰማቸው እንስሳት ስራቸውን ዙሪያውን እየዞሩት ያደንቁ ጀመር።

ለሁለተኛ ጊዜ የገነቡት ዊንድሚል ከፈረሰው ይልቅ እጅግ ውብ ሆኖ ታያቸው። ግርግዳውም ቢሆን ከበፊቱ ሁለት እጅ ውፍረት ነበረው። ከፈንጂ በስተቀር ይህንን ግንባታ ሊያፈርሰው የሚችል ሃይል አይኖርም! እንደምን አድርገው እንደደከሙ፣ ስንት ተስፋ አስቆራጭ መሰናክሎችን እንደተወጡ፣ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ሸራው ሲወጠርና ዳይናሞው መስራት ሲጀምር በህይወታቸው ላይ የሚያስከትለውን ግዙፍ ለውጥ ሲያስቡት፣ ድካማቸው ሁሉ ከላያቸው ብን ብሎ ጠፍቶ በዊንድሚሉ ዙሪያ እየተሽከረከሩ በደስታ ሲቃ ጨፈሩ።

ናፖሊዮን ራሱ በጠባቂ ውሾቹ ታጅቦ፣ አውራ ዶሮው ከፊት ለፊት የ’ኩኩሉኡኡኡኡ’ ጥሩንባውን እየነፋ የተጠናቀቀውን ግንባታ ሊጎበኝ መጣ። እንስሳቱን ሁሉ እሱ ራሱ ቀርቦ “እንኳን ደስ ያላችሁ” አላቸው፣ ግንባታውን በማጠናቀቃቸው። ዊንድሚሉም ‘ናፖሊዮን ሚል’ በሚል የተሰየመ መሆኑን አበሰራቸው።

ይህ በሆነ በሁለተኛው ቀን እንስሳቱ በትልቁ መጋዘን ውስጥ ለልዩ ስብሰባ ተጠሩ። ናፖሊዮን ክምር ጣውላውን ለፍሬደሪክ መሸጡን በነገራቸው ጊዜ መብረቅ የወረደባቸው ይመስል ደርቀው ቀሩ። “ከነገ ጀምሮ የፍሬደሪክ እቃ መጫኛዎች እየተመላለሱ ጣውላዎቹን

ያጓጉዛሉ” ተባሉ። ናፖሊዮን ይህን ያህል ጊዜ ከፒልኪንግተን ጋር ጓደኝነት የመሰረተ መስሎ ሲቆይ ለካስ ውስጥ ውስጡን ከፍሬደሪክ ጋር ሲደራደር ነበር።

እነሆ ከፎክስዉድ ጋር የነበሩ ግንኙነቶች ሁሉ ተቋረጡ። ለፒልኪንግተንም የዘለፋ መልእክቶች ተላኩለት። ርግቦቹ ከእንግዲህ ወደ ፒንችፊልድ በረራ እንዳያደርጉ፣ “ሞት ለፍሬደሪክ” የሚለውን መፈክር “ሞት ለፒልኪንግተን” በሚል እንዲቀይሩ መመሪያ ተሰጣቸው። *የእንስሳ እርሻ* ላይ በፍሬደሪክ በኩል የጦርነት አደጋ አንዣቧል ሲባል የነበረው የሀሰት ዜና ነበር ተባሉ። ፍሬደሪክ በሚያስተዳድራቸው እንስሳት ላይ ኢ-እንስሳዊ የሆነ ግፍ ይፈፅማል የተባለውም አለቅጥ ተጋኗል ተባለ። እኒህ ሁሉ ሀሜቶች የተፈጠሩት ምናልባትም በስኖውቦልና በሰላዮቹ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ በእንስሳቱ መኻል ተሰራጨ። እንደውም ስኖውቦል እስከዛሬ የተደበቀው በፒንችፊልድ እርሻ ውስጥ ነበር እንደተባለው ሳይሆን እውነቱ በተቃራኒው ነበር ተባለ። ስኖውቦል ፒንችፊልድን ረግጦ አያውቅም። በተንቀባረረ እንክብካቤ እየኖረ የሚገኘው በፎክስዉድ እርሻ ውስጥ ሲሆን ለዘመናት የፒልኪንግተን ምስጢራዊ አገልጋይ ነበር የሚል ወሬ ተነዛ።

አሳሞቹ በናፖሊዮን ረቂቅ ጥበብ በደስታ ብዛት ጣራ ነኩ። ከፒልኪንግተን ጋር ጓደኛ በመምሰል ፍሬደሪክን አስራ ሁለት ፓውንድ ጭማሪ  ከፍሎ እንዲገዛ አስገድዶታል። “የናፖሊዮን አስተሳሰብ ረቂቅነት” አለ ስኩለር “ማንኛቸውንም - ፍሬደሪክንም እንኳን ቢሆን - ባለማመኑ ሊታይ ይችላል። ፍሬደሪክ ቼክ በሚባል ነገር ከፍሎ ጣውላዎቹን ለመግዛት ፈልጎ ነበር። እንግዲህ ቼክ ማለት ቁራጭ ወረቀት ሲሆን በላዩ ላይ የገንዘብ መጠን ይፃፍበታል። ናፖሊዮን ግን ከፍሬደሪክ በላይ ብልህ በመሆኑ ክፍያው በጥሬ ገንዘብ ለዛውም በባለ አምስት ፓውንድ ኖቶች ሆኖ ጣውላዎቹ ከመጓጓዛቸው በፊት እንዲከፍል ጠየቀው። እና ከፈለ። ገንዘቡም ዊንድሚሉን ማንቀሳቀሻ የሚሆን መሳሪያ ይገዛበታል” አለ ስኩለር

ጣውላው በተቀላጠፈ ፍጥነት ይጓጓዝ ጀመር። ይህ እንደተጠናቀቀም ሌላ ልዩ ስብሰባ ተጠራ። እንስሳቱ በትልቁ መጋዘን ተገኝተው የባንክ ኖቶቹን እንዲጎበኙ ተደረገ። መድረኩ ላይ በተጎዘጎዘው ደረቅ ሳር ላይ ናፖሊዮን ሜዳሊያዎቹን ደርድሮና እንስሳዊ ፈገግታ ተላብሶ ተቀምጧል። ከትልቁ መኖሪያ ህንፃ በመጣ ሳህን ላይ የባንክ ኖቶቹ በስነ ስርአት ተከምረው ከጎኑ ሆነዋል። እንስሳቱ በዝግታ በገንዘቡ ፊት ለፊት ያልፋሉ፣ አይኖቻቸው እስኪጠግቡ ድረስ እየተመለከቱ። ቦክሰር ገንዘቡን ለማሽተት አፍንጫውን አስጠጋ። ልፍስፍሶቹ ነጫጭ ነገሮች በትንፋሹ ተረብሸው ተርገፈገፉ።

ይህ በሆነ በሶስተኛው ቀን በ*እንስሳ እርሻ* አስከፊ ሁካታ ተፈጠረ። ዊምፐር ፊቱ አመድ መስሎ፣ ብስክሌቱን እያከነፈ መጥቶ ሜዳው ላይ ወርውሮት ወደ ትልቁ ህንፃ እየሮጠ ገባ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም ከናፖሊዮን መኖሪያ ክፍል በንዴት የጦፈ የሲቃ ድምፅ ተሰማ። የሆነው ነገር በእርሻው ጣቢያ እንደ ሰደድ እሳት ተዛመተ። የባንክ ኖቶቹ ሀሰት /ፎርጅድ/ ነበሩ። ፍሬደሪክ ጣውላዎቹን የወሰደው በነፃ ነበር።

ናፖሊዮን እንስሳቱን በሙሉ በአስቸኳይ ሰበሰባቸው። በሚያስገመግም አስፈሪ ድምፅ በፍሬደሪክ ላይ የሞት ቅጣት በየነበት። “ፍሬደሪክ ከነነፍሱ ሲያዝ በህይወት እያለ የፈላ ውሃ ውስጥ ይጨመራል” አላቸው። እንዲህ ያለ ሸፍጥን አስከትሎ ሊመጣ የሚችል ነገር እንደሚኖርም አስጠነቀቃቸው። ፍሬደሪክና ሰዎቹ ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ የቆየውን ጥቃት ሊፈፅሙ ይችላሉ። ተጨማሪ የዘብ ማማዎች ወደ እርሻው መዳረሻዎች ላይ ሁሉ ተተከሉ። አራት ርግቦች ወደ ፎክስዉድ የእርቀ ሰላም መልእክት ይዘው ተላኩ። ይህም ከፒልኪንግተን ጋር መልካም ግንኙነትን ሊያመጣ ይችላል ተባለ።

ጥቃቱ በበነጋታው ተጀመረ። እንስሳቱ ቁርስ ላይ ነበሩ። ፍሬደሪክና ሰዎቹ የ እርሻውን ዋና መግቢያ በር አልፈው መዝለቃቸውን ለጥበቃ ተሰማርተው የነበሩት መጥተው ተናገሩ። እንስሳቱም ደረቶቻቸውን ገልብጠው ወራሪዎቹን ሊጋፈጡ ሄዱ። ሆኖም በላምበረቱ ጦርነት ላይ ተቀዳጅተውት እንደነበረው ቀላል ድል ማግኘት አልቻሉም። አስራ አምስት ሰዎች ነበሩ። ግማሽ ያህሉ ጠመንጃ ይዘዋል። ከሃምሳ ያርድ ርቀት ተኩስ ከፈቱ። ምንም እንኳን ናፖሊዮንና ቦክሰር ሊያበረታቷቸው ቢሞክሩም እንስሳቱ የተኩሱን እሩምታና የጥይቱን ጠዝጣዥነት መቋቋም ባለመቻላቸው አፈገፈጉ። ብዙዎች ቆሰሉ። በእርሻው ጣቢያ ካሉት ህንፃዎች ጀርባ ተከልለውም እያሾለቁ ይመለከቱ ጀመር።

የግጡሹ መሬት በሙሉና ዊንድሚሉ ጭምር በጠላት ቁጥጥር ስር ወድቋል። ለቅፅበት ናፖሊዮን ራሱ ምን ማድረግ እንዳለበት ግራ የተጋባ መሰለ። ወደ ላይና ወደ ታች ተንጎራደደ፣ ጭራው ቀጥ ብሎ እየተንቀጠቀጠ። ወደ ፎክስዉድ አቅጣጫ በተስፋ ስሜት ተመለከተ። ፒልኪንግተንና ሰዎቹ እርዳታ ቢያደርጉላቸው ከሽንፈት ሊድኑ ይችላሉ። በዚህ መኻል ወደ ፎክስዉድ ትላንትና ተልከው የነበሩት አራት ርግቦች ተመለሱ። ከመኻከላቸው አንዷ ከፒልኪንግተን የተላከ መልእክት ያዘለ ወረቀት ለናፖሊዮን አቀረበች። "የእጅህን አግኝተኻል" ይላል መልእክቱ።

ፍሬደሪክና ሰዎቹ ዊንድሚሉ አጠገብ ሲደርሱ ቆሙ። እንስሳቱ በጥንቃቄ ይመለከቷቸዋል፣ በስጋት ተወጥረው። ሁለት ሰዎች የብረት ዘንግና መዶሻ ይዘዋል፣ ዊንድሚሉን ሊያፈርሱት።

"ሊሆን አይችልም" ሲል ጮኸ ናፖሊዮን። "ግርግዳው እንዲህ በዋዛ የሚናድ አይደለም። አንድ ሳምንት ሙሉ ቢታገሉም አይፈርስም፣ አይዟችሁ ጓዶች!"

ቤንጃሚን የሰዎቹ ሁኔታ ስላላማረው በጥንቃቄ ነበር የሚያስተውላቸው። ሁለቱ በያዙት የብረት ዘንግና መዶሻ ዊንድሚሉ መሰረት አጠገብ ይቆፍሩ ጀመር። ይህንን የተመለከተው ቤንጃሚን በመደነቅ ስሜት በዝግታ አገጩን አወዛወዘ።

"እንደጠረጠርኩት ሊያደርጉ ነው" አለ። "ምን እየሰሩ እንደሆን ማየት አትችሉምን? በሚቀጥለው ደቂቃ በጉድጓዱ ውስጥ ፈንጂ ይቀብራሉ።"

እንስሳቱ በድንጋጤ የሚከተለውን ይጠባበቁ ጀመር። በአሁኑ ሰአት ከተሸሸጉበት ስፍራ መውጣት አይችሉም። ጥቂት ደቂቃዎች ቆይቶ ሰዎቹ በያቅጣጫው ሲሮጡ ታዩ። ቀጥሎም ሰማይና ምድሩን ያደባለቀ የሚመስል የፍንዳታ ድምፅ ተሰማ። ርግቦች ወደ አየር ተመነጠቁ። ከናፖሊዮን በስተቀር ሁሉም እንስሳት በሆዳቸው መሬት ይዘው ፊቶቻቸውን ቀበሩ። ካደፈጡበት ሲነሱ ጥቁር ደመና የመሰለ ጭስ በዊንድሚሉ ስፍራ ሲጥመለመል ተመለከቱ። ንፋሱ በዝግታ ጥቁሩን ደመና አስወገደው። ዊንድሚሉ በቦታው የለም።

ይህንን የተመለከቱት እንስሳት ወኔያቸው አንሰራራ። አደንዝዟቸው የነበረው ፍርሃትና ሽብር በተመለከቱት ርኩስ ተግባር ከላያቸው ጠፍቶ በውስጣቸው የሚንተከተክ የበቀል ቋያ ተቀጣጠለ። ሁሉም እንስሳት በሚያስገመግም የበቀል ጥሪ ድምፅ አንዳችም ትእዛዝ ሳይጠብቁ ወደ ጠላት ሰፈር ተምዘገዘጉ። በላያቸው እንደ ጉድ የሚዘንመው የጠላት ጥይት እንኳን አልበገራቸውም።

አሰቃቂና ጭካኔ የተሞላበት ጦርነት ተካሄደ። ሰዎቹ ደግመው ደጋግመው የተኩስ እሩምታ አወረዱ። እንስሳቱ በቀረቧቸው ጊዜም በዱላዎቻቸውና በጠንካራ ቧት ጫማዎቻቸው ጭምር ተከላከሏቸው። አንዲት ላም፣ ሶስት በጎችና አንዲት ዳክዬ ሞቱ። ከሞላ ጎደል

አብዛኛዎቹ ቆሰሉ። ጦርነቱን ከኋላ ሆኖ ይመራ የነበረው ናፖሊዮን እንኳን ሳይቀር የጭራው ጫፍ በጥይት ተቆርጧል። ሰዎቹም ቢሆኑ ጉዳት ደርሶባቸዋል። በቦክሰር ሾኾና የተመቱት ሶስቱ ጭንቅላታቸውን ተፈንክተዋል። ሌላው ሆድ እቃው በላም ቀንድ ተቦትርፏል። ብሉቤልና ጄሲ የሌላኛውን ሰው ሱሪ ቀዳደው ርቃኑን ሊሆን ምንም አልቀረው።

በቁጥቋጦ ውስጥ እንዲመሽጉ ታዝዘው የነበሩት ዘጠኙ የናፖሊዮን ጠባቂ ውሾች ከሰዎቹ ጀርባ ደም እንደጠማው አውሬ እየጮሁ እና እየተምዘገዘጉ በድንገት ሲመጡባቸው ሰዎቹ በፍርሃት ራዱ። ማምለጥ ከማይችሉበት ከበባ ውስጥ እየገቡ መሆናቸውንም አስተዋሉ። ቀዳዳው ሁሉ ሳይዘጋ በጊዜ እንዲያመልጡ ፍሬደሪክ ለሰዎቹ ትእዛዝ ሰጠ። በዚያው ቅፅበት ፈሪዎቹ ወራሪዎች ቀኝ ኋላ ዞረው ነፍስ አውጪኝ ፍርጠጣቸውን ተያያዙት። እንስሳቱ እስከ ሜዳው መጨረሻ ድረስ እየተከታተሉ አባረሯቸው። በቆንጥራማው ቁጥቋጦ በኩል ሾልከው ከማምለጣቸው በፊት አንዳንዶቹ የመሰናበቻ ርግጫና ንክሻ ቀመሱ።

እነሆ እንስሳቱ ጦርነቱን አሸነፉ። ግን እጅግ ደክሟቸዋል። በደም ተበክለዋል። እያነካከሱ፣ በዝግታ ወደ እርሻቸው አዘገሙ። በሜዳው ሳር ላይ በየቦታው የወዳደቁትን ጓዶቻቸውን ሲመለከቱ አንዳንዶቹን አስለቀሳቸው። የድካማቸው ፍሬ የነበረው ዊንድሚሉ ስፍራ ሲደርሱ በፀጥታና በሀዘን ተውጠው ለተወሰነ ጊዜ ቆሙ። አዎ! ደብዛው የለም። የዚያ ሁሉ ድካማቸው ደብዛው አይታይም! መሰረቱ ሳይቀር በከፊል ወድሟል። እንደገና ለመገንባት እንኳን ድንጋዩን እንዳለፈው ጊዜ ዳግም መጠቀም አይችሉም። ብትንትኑ ወጥቷል። የፍንዳታው ሃይል አያሌ ሜትሮች አሽቀንጥሮ በታትኗቸዋል። ዊንድሚሉ ከቶም በዛ ስፍራ ላይ ተገንብቶ የነበረ አይመስልም።

ወደ እርሻው እንደተዳረሱም፣ እስከ ጦርነቱ ማብቂያ የት እንደነበር ያልታወቀው ስኩለር እየነጠረ ወደ እነሱ መጣ፣ ፊቱ በደስታ ፈክቶና ጭራውን እያወዛወዘ። ከእርሻው ጣቢያ ህንፃዎች አቅጣጫ እንስሳቱ የተኩስ ድምፅ ሰሙ።

“የጠመንጃው ተኩስ ስለ ምንድን ነው?” ሲል ጠየቀ ቦክሰር።

“ድላችንን ለማብሰር!” ሲል ጮኸ ስኩለር።

“የምን ድል?” ጠየቀው ቦክሰር። ጉልበቱ ይደማል። ጫማውን ከማጣቱም በላይ ሾኾናው ተሰንጥቋል። በፊት እግሮቹ ደርዘን የሚሆኑ ጥይቶች ተሰንቅረው ቀርተዋል።

“የምን ድል? አልክ ጓድ? ጠላቶቻችንን ከመሬታችንና ከተቀደሰው *የእንስሳ እርሻ* አላባረርንምን?”

“ሁለት አመት የለፋንበትን ዊንድሚል ግን አውድመውታል።”

“ታዲያ ቢወድምስ? ሌላ እንገነባለን። አስፈላጊ መስሎ ከታየን ስድስት ዊንድሚሎች ልንገነባ እንችላለን። የሰራነውን ታላቅ ተግባር የምታደንቅ አይደለህም፣ ጓድ። ይህ የቆምንበት መሬት በጠላት እጅ ወድቆ የነበረ ነው። እድሜ
ለጓድ ናፖሊዮን አመራር ይሁንና እነሆ እያንዳንዷን ስንዝር መሬት ከጠላት እጅ አውጥተን መልሰን ይዘናል።”

“ቀድሞም የነበረንን እኮ ነው ያስመለስነው።” አለው ቦክሰር።

“እሱ'ኮ ነው ድላችን” በማለት መለሰለት ስኩለር።

እናም እያነካከሱ ወደ መሰባሰቢያቸው አዘገሙ። በቦክሰር እግር ውስጥ የተቀበሩት ጥይቶች ይጠዘጥዙታል። ከፊት ለፊቱ የሚጠብቀውን ዊንድሚሉን እንደ ገና የመገንባት ተግባር ሲያስብ ራሱን በሃሳቡ ማዘጋጀት ጀመረ። እነሆ ለመጀመሪያ ጊዜ አስራ አንድ አመት እንደ ሞላው ሲያስታውስና የእድሜው መግፋት ሲታሰበው ጠንካራ ጡንቻዎቹ እንደ ድሮው እንደማይሆኑለት ተሰማው።

እንስሳቱ አረንጓዴው ባንዲራቸው ሲውለበለብና የጠመንጃ ተኩስ እንደገና ሲሰሙ - በድምሩ ሰባት ጊዜ ተተኩሷል - እና ስለተወጡት ግዳጅ ናፖሊዮን  የምስጋና ንግግር ሲያደርግላቸው፣ እውነትም ታላቅ ድል እንደተቀዳጁ ተሰማቸው። በጦርነቱ ላይ የተሰዉት እንስሳት የቀብር ስነ ስርአት ተደረገላቸው። ቦክሰርና ክሎቨር የእንስሳቱ አስክሬኖች የተጫኑበትን ጋሪ ሲጎትቱ ናፖሊዮን ከሰልፈኛው ፊት ለፊት ይራመድ ነበር።

ለተገኘው ድል ፌሽታ ሁለት ቀን ተሰጠ። ብዙ መዝሙሮች ነበሩ። ብዙ ንግግሮችና ብዙ ተኩሶች ተካሄዱ። ለእያንዳንዱ እንስሳ የአንዳንድ አፕል ገፀ በረከት ተደረገላቸው። ሁለት ‘አውንስ’ በቆሎ ለወፎች፣ ሶስት፣ሶስት ብስኩቶች ለውሾች ታደላቸው። ጦርነቱም ‘የዊንድሚሉ ጦርነት’ በሚል የሚጠራ መሆኑ ታወጀ። ‘የአረንጓዴው ባንዲራ ማእረግ’ የሚል አዲስ የጀግና ሜዳሊያ ሽልማት ስም ወጣ። ተሸላሚውም ራሱ ናፖሊዮን ሆነ። በዚህ ፌሽታ መኻል ግን የባንክ ኖቶቹ ጉዳይ ተረሳሳ።

ይህ ከሆነ ከጥቂት ቀናት በኋላ አሳሞቹ ከትልቁ መኖሪያ ቤት ውስኪዎች አገኙ። እስከዛን እለት ድረስ ግን መኖራቸው አልታወቀም ነበር። እናም የዛን እለት ምሽት ከህንፃው ውስጥ በከፍተኛ ድምፅ መዝሙር ሲዘመር አመሸ። የዜማው ቅላፄ ሰሚዎቹን እስከሚያስደንቅ ድረስ፣ ‘የእንግሊዝ አራዊት’ን ዜማ ቅይጥ ነበር። ከምሽቱ ሶስት ሰአት ተኩል ገደማ ናፖሊዮን የአቶ ጆንስን አሮጌ ባርኔጣ ደፍቶ በጓሮ በር በመውጣት ሜዳው ላይ ጋልቦ ተመልሶ ሲገባ ታየ። ሲነጋ በህንፃዎቹ ፍፁም የሆነ ፀጥታ ሰፍኗል። አንድ የአሳማ ዘር እንኳን ዝር ሳይል ረፈደ።

ስኩለር በዝግታ እየተንገዳገደ፣ አይኑ ደፍርሶ፣ ጭራው የእሱ በማይመስል አይነት ተንጠልጥሎ፣ በጠና የታመመ በሚመስል ገፅታ ከጠዋቱ ሶስት ሰአት ሲሆን ብቅ አለ። እንስሳቱን ሰበሰቦ “አሳዛኝ ዜና ይዞ እንደመጣ” ነገራቸው። “ጓድ ናፖሊዮን በሞት ጣእር ላይ ይገኛል” አላቸው።

ዋይታ ሆነ። ከህንፃው መግቢያ ላይ ሳር ተጎዝጉዞ እንስሳቱ በላዩ ላይ በ እግሮቻቸው ጣቶች ጫፍ እየረገጡ አለፉ። አይኖቻቸው በእንባ ረጥበው፣ መሪያቸውን ሞት ቢነጥቃቸው ምን ማድረግ እንደሚችሉ እርስ በርሳቸው ይጠያየቃሉ። “ስኖውቦል በናፖሊዮን ምግብ ውስጥ በረቀቀ መንገድ መርዝ ጨምሯል” የሚል ወሬ ይናፈስ ጀመር። በዚህ መኻል ስኩለር ሌላ መግለጫ ሊሰጥ መጣ። “ጓድ ናፖሊዮን በዚህች ምድር የመጨረሻ ቆይታው ሰአት ላይ የሚከተለውን አዋጅ አስተላልፏል” አላቸው  “*አልኮል መጠጣት በሞት ያስቀጣል።”*

አመሻሽ ላይ ናፖሊዮን እየተሻለው መሆኑ ተሰማ። በበነጋታው ጠዋት ላይ ስኩለር መጥቶ እያገገመ መሆኑን ነገራቸው። በዛኑ ቀን ማታ ናፖሊዮን ስራ መጀመሩ ተነገረ። በሚቀጥለው ቀን ናፖሊዮን ዊምፐርን ከዊሊንግደን ስለ አልኮል ጥንስስ አሰራርና አጠማመቅ የሚያትት መፅሀፍ እንዲገዛለት ማዘዙ ታወቀ። ከአንድ ሳምንት በኋላ ናፖሊዮን በአስተላለፈው ትእዛዝ ከፍራፍሬው እርሻ ማዶ ለጡረተኞች ተከልሎ የነበረው የግጦሽ መሬት

እንዲታረስ ወሰነ። የሰጠውም ምክንያት “መሬቱ ስለነጠፈ ዘር ያስፈልገዋል” የሚል ነበር። ሆኖም ናፖሊዮን እንዲዘራ የፈለገው የዘር አይነት ገብስ መሆኑ ወዲያው ታወቀ።

በዚህ ወቅት ነበር እንግዳ የሆነ እና ምክንያቱ ሊገባ የማይችል ሁኔታ የተከሰተው። አንድ ምሽት አስራሁለት ሰአት ገዳማ ከጓሮ አንዳች ነገር በከፍተኛ ድምፅ ሲወድቅ ተሰማ። እንስሳቱ ከየማደሪያዎቻቸው ወጥተው ድምፁን ወደ ሰሙበት በፍጥነት ሄዱ። የጨረቃ ብርሃን ፏ ያለበት ምሽት ነበር። ሰባቱ ትእዛዛት ከተፃፉበት ከትልቁ መጋዘን ግርግዳ ስር ለሁለት የተከፈለ መሰላል ወድቋል። ስኩለር - በገፅታው ድንጋጤ ይታይበታል - ከጎኑ ተዘርሯል። ከአጠገቡም ፋኖስ፣ የቀለም ብሩሽና ባፍጢሙ የተደፋ የነጭ ቀለም ቆርቆሮ ይታያሉ። ጠባቂዎቹ ውሾች ወዲያው ዙሪያውን ከበቡት። ከወደቀበት ሲነሳም አጅበውት ወደ ትልቁ ህንፃ ሄዱ።

እንስሳቱ ሁሉ የስኩለር ድርጊት ምስጢሩ ሊከሰትላቸው አልቻለም፣ ከቤንጃሚን በስተቀር። እሱ ግን ነገሩ እንደ ገባው አገጩን ከማወዛወዝ ሌላ ለሌሎቹ ምንም አልነገራቸውም።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ሙሪል፣ ሰባቱን ትእዛዛት ለራሷ አንብባ ስትጨርስ እንስሳቱ የተሳሳተ ግንዛቤ ያላቸው ሌላ ህግ መኖሩን አስተዋለች። አምስተኛው ትእዛዝ *“ማንኛውም እንስሳ አልኮል መጠጣት የለበትም”* የሚል ህግ መስሏቸው ነበር። ነገር ግን የረሷቸው ሁለት ቃላት ነበሩበት። አምስተኛው ትእዛዝ በርግጥ የሚለው እንዲህ ነበር ***“ማንኛውም እንስሳ አልኮል መጠጣት የለበትም፣ ከመጠን በላይ”***

# ምእራፍ ዘጠኝ

## ሪፐብሊክ እና ፕሬዚዳንት

የተሰነጠቀው የቦክሰር ሸኾና ሳይድን ረጅም ጊዜ ቆየ። የድል በአል በተጠናቀቀ ማግስት ነበር የዊንድሚሉ ግንባታ የተጀመረው። ቦክሰር ለአንድ ቀን እንኳን ከስራ ለመቅረት አሻፈረኝ አለ። በህመሙ የሚሰቃይ መሆኑን ላለማሳወቅ ስቃዩን ውጦ ይሰራል። ሲመሽ ግን ለክሎቨር ሸኾናው ክፉኛ እንደሚጠዘጥዘው ሳይደብቅ ይነግራታል። እሷም ስራ ስር በማኘክና በመቀመም ቁስሉን ታክምለታለች። ቤንጃሚንና እሷ በስራ የሚያጠፋውን ሰአት እንዲቀንስ ደጋግመው ይወተውቱታል። "የፈረስ ሳንባ እድሜው ብዙ አይደለም" ትለዋለች ክሎቨር። ቦክሰር ግን ምክራቸውን አይሰማም። ጡረታ ከመውጣቱ በፊት ያለው ህልም አንድ ብቻ መሆኑን ይናገራል። ዊንድሚሉ ተገንብቶ ማየት።

የእንስሳ እርሻ ህግጋት መጀመሪያ የተደነገጉ ዘመን የጡረታ እድሜ ጣራ ተመድቦ ነበር። ፈረሶችና አሳሞች በአስራ ሁለት፣ ላሞች በአስራ አራት፣ ውሾች በዘጠኝ፣ በጎች በሰባት፣ ዶሮዎችና ዳክዬዎች በአምስት አመት እድሜያቸው በጡረታ እንዲገለሉ። እንደ አግባብነቱ እየታየም የጡረታ ክፍያ እንዲደረግ ተወስኖ ነበር። ይሁንና እስከዛሬ ጡረታ የወጣ እንስሳ ግን የለም። ሆኖም ጉዳዩ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደጋጋሚ ሲነሳ ተስተውሏል።

ከፍራፍሬው እርሻ ማዶ ተወስኖ የነበረው የጡረተኞች መሬት ገብስ እንደሚዘራበት ከተደነገገ ወዲህ ከትልቁ መስክ አንደኛ ወገን ያለው መሬት ታጥሮ ለተጧሪዎች ግጦሽ እንዲውል ይደረጋል የሚል ጭምጭምታ ይሰማል። እንደሚባለው ከሆነ ለፈረስ በቀን አምስት ፓውንድ በቆሎ፣ በክረምት ደግሞ አስራ አምስት ፓውንድ ድርቆሽ፣ ካሮት ወይም ምናልባት ከአፕል ጋር በበአላት ቀን ይሰጣል። የቦክሰር አስራ ሁለተኛ አመት ልደት በሚቀጥለው አመት በጋ ላይ ይውላል።

ህይወት ከብዷል። የዘንድሮው ክረምት እንደ አምናው ሁሉ ያኮማትራል። በዚህ ላይ የምግብ እጥረት አለ። ከአሳሞቹና ከጠባቂ ውሾቹ ራሽን በስተቀር የሁሉም እንስሳት ፍጆታ እንደገና ተቀንሷል። "አክራሪ የራሽን እኩልነትን መከተል የእንስሳዊነት መርሆን መፃረር ማለት ይሆናል" ይላቸዋል ስኩለር። ምንም እንኳን የምግብ እጥረት ያለ ቢመስልም በተጨባጭ ግን እንስሳቱ የምግብ ችግር የሌለባቸው መሆኑን ለማሳመን ስኩለር ማስረጃ የመደርደር ችግር የለበትም። እርግጥ ለጊዜው በቀን ፍጆታቸው ላይ ማስተካከያ ማድረግ

ተገቢ ሆኗል። (ስኩለር ሁልጊዜ 'ማስተካከያ' እንጂ 'ቅነሳ' አይልም ራሽንን በተመለከተ።) ነገር ግን ከጆንስ ዘመን ጋር ሲነፃጸር የመሻሻሉ መጠን ከፍተኛ ነበር።

ስኩለር በረጅም ወረቀት ላይ የተደረደሩ የእድገት መለኪያ ቁጥሮችን በቀጭን ፈጣን ድምፅ እያነበበ "ከጆንስ ዘመን ይልቅ ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ከጀመሩ ወዲህ ብዙ አጃ፣ ብዙ ድርቆሽ ሳርና ብዙ አገዳ እንዳላቸው፣ የስራ ሰአታቸው አጭር እንደሆን፣ ንፁህና ምርጥ የመጠጥ ውሃ እንዳገኙ፣ ረጅም እድሜ መኖር እንደጀመሩ፣ ከወሊድ ጋር በተዛመደ የህፃናት ሞት በአያሌው እንደ ቀነሰ፣ በየማደሪያቸው በቂ ጉዝጓዝ እንዳላቸውና ከቁንጫ እንደተገላገሉ" ይነግራቸዋል። እንስሳቱ ገለፃውን አምነውበታል። እውነቱን ለመናገር ግን ጆንስና የቆመለት አለማ ምን እንደነበሩ ከህሊናቸው ሙሉ ለሙሉ በመጥፋት ላይ ነበሩ።

ህይወታቸው በአሁኑ ወቅት አስከፊና ዝቅተኛው ደረጃ ላይ ያለ መሆኑ ይታወቃቸዋል። ምክንያቱም ዘወትር እንደራባቸውና እንደበረዳቸው፣ እንቅልፍ ካልተኙ በስተቀር ዘወትር በስራ እንደተጠመዱ መሆናቸው ይሰማቸዋልና። ነገር ግን ያለ ጥርጥር በድሮ ጊዜ ከዚህ የባሰ ነበር ብለው ያምናሉ። ይህንን በማመናቸው ደግሞ ደስተኞች ናቸው። በቀድሞ ዘመን ባሪያዎች ነበሩ። አሁን ነፃ ናቸው። ይህም ለነሱ መተኪያ የሌለው ነገር ነበር። ስኩለርም የነፃነታቸውን ጉዳይ ዘወትር በአፅንኦት ያስታውሳቸዋል።

አሁን ዘመን ብዙ የሚቀለቡ አፎች በዝተዋል። በልግ ውስጥ አራቱ አሳማቶች በተመሳሳይ ጊዜ በድምሩ ሰላሳ አንድ አሳሞችን ወለዱ። የተወለዱት አሳሞች ነጭና ጥቁር የሆነ ዥንጉርጉር ቆዳ ነበራቸው። ናፖሊዮን የእርሻው ጣቢያው ብቸኛው ያልተኮላሸ አሳማ በመሆኑ አባታቸው ማን እንደሆን መገመት አይከብድም። ወደፊት ጡቦችና ጣውላዎች ሲገዙ ከትልቁ መኖሪያ ቤት ግቢ የአትክልት ስፍራ ላይ ለታዳጊ አሳሞቹ ትምህርት ቤት እንደሚገነባ ታወጀ። እስከዛው ድረስ በህንፃው ውስጥ በሚገኘው የምግብ ማብሰያ ክፍል ናፖሊዮን ራሱ መመሪያ እንደሚሰጣቸው ተገለፀ። በአትክልቱ ስፍራ ላይ ስፖርት ይሰራሉ። ከሌሎቹ እንስሳት ህፃናት ጋር ግን እንዳይቀላቀሉ ታግደዋል።

እነሆ በዚህ ወቅት ነበር *"አሳማና ሌላ እንስሳ ጎዳና ላይ ሲገናኙ ሌላው እንስሳ ለአሳማ መንገድ መልቀቅ አለበት"* የሚል ህግ የወጣው። በተጨማሪም በየትኛውም ደረጃ ላይ የሚገኝ ማንኛውም አሳማ ዘወትር እሁድ አረንጓዴ ሪቫን ጭራው ላይ የማሰር ልዩ መብት እንዳለው ተደነገገ።

በዛን አመት እርሻው በአንፃራዊ መልኩ ማለፊያ የሆነ ውጤት አግኝቷል። የገንዘብ እጥረት ግን ነበር። ትምህርት ቤቱን ለመገንባት ጡቦች፣ አሸዋና የሲሚንቶ መቀላቀያ መግዛት አለባቸው። ለዊንድሚሉ የሚሆን መሳሪያ ለመግዛት ገንዘብ ማጠራቀም አስፈላጊ ነበር። ለቤቶች የሚሆን ዘይትና ሻማ መግዛት አለባቸው። ለናፖሊዮን ደግሞ ስኳር። (ናፖሊዮን ሌሎች አሳሞች ስኳር እንዳይመገቡ አግዷል። የሰጣቸውም ምክንያት አለቅጥ ያወፍራችኋል የሚል ነበር።) በተጨማሪም የእጅ መሳሪያዎች፣ ምስማሮች፣ ሲባጎ፣ ከሰል፣ ሽቦ፣ ብረታ ብረት እና የውሻ ብስኩቶች መግዛት ይኖርባቸዋል።

ክምር ጭድና ከድንቹ ምርት ደግሞ ከፊሉ ተሸጠ። ከዶሮዎቹ የሚወሰዱትም እንቁላሎች ኮንትራት በሳምንት ቁጥሩ ወደ ስድስት መቶ ከፍ አለ። ያን አመት ዶሮዎቹ በቂ ጫጩቶች መፈልፈል ባለመቻላቸው የተወሰነባቸውን ኮታ ለማሟላት ተቸግረው ነበር። በታህሳስ ወር ከተደረገው የራሽን ቅነሳ በተጨማሪ በየካቲት ወርም ሌላ ቅነሳ ተካሄደ። በየማደሪያዎቹ ይበሩ የነበሩት ፋኖሶች ዘይት ለመቆጠብ በሚል አስባብ ታገዱ። ***አሳሞቹ ሁሉ ግን ምቾት በምቾት ነበሩ። ውፍረት ጨምረው ከማነጥነጥ በቀር ያጡት ነገር አልነበረም።***

በየካቲት ወር ውስጥ አንዱን ቀን ከሰአት በኋላ ከትልቁ መኖሪያ ህንፃ ጓሮ ከሚገኘውና በዘመነ ጆንስ ከግልጋሎት ውጪ ከነበረው መጥመቂያ ክፍል ከዚህ ቀደም እንስሳቱ የማያውቁት፣ የምግብ ፍላጎትን ቀስቅሶ አንጀት የሚያንሰፈስፍ ሽታ ሜዳውን አቋርጦ ሸተታቸው። ከመኻከላቸው አንዱ 'የገብስ ቆሎ ሽታ' መሆኑን ተናገረ። እንስሳቱ አየሩን በተራበ አንጀታቸው እያሸተቱ ለእራታቸው የሚሆን ለብ ያለ ገንፎ እየተዘጋጀላቸው ሊሆን ይችላል ብለው አሰቡ። ሆኖም የቀረበላቸው ያሰቡት አልነበረም።

ይህ በሆነ ሳምንት እሁድ እለት "ከእንግዲህ ገብስ በሙሉ ለአሳሞች ፍጆታ ብቻ ይውላል" የሚል ደንብ ወጣ። ከመለስተኛው የአትክልት እርሻ ማዶ ለጡረተኞች ተብሎ የተከለለው መሬት ገብስ ከተዘራበት ሰንብቷል። ብዙም ሳይቆይ እያንዳንዱ አሳማ ከምግቡ ጋር ግማሽ ሊትር ቢራ እንደሚሰጠው እንስሳቱ አወቁ። ናፖሊዮን ለራሱ  በቀን ሁለት ሊትር ተኩል ቢራ የሚወስድ ሲሆን ይህም ሁልጊዜ 'ክራውን ደርቢ' በተባለ የሾርባ መጠጫ ይቀርብለታል።

የኑሮ መከራ የበዛ ቢሆንም ቅሉ በዚህ ዘመን ያለውን ህይወት የሚያካክሰው፣ ከበፊቱ ዘመን ይበልጥ ክብር ያገኘ መሆኑ ነበር። ምክንያቱም ብዙ መዝሙሮች ይዘመራሉ። ብዙ ንግግሮች ይካሄዳሉ። ብዙ ሰልፎች ይደረጋሉ። ናፖሊዮን ባስተላለፈው ትእዛዝ መሰረት በሳምንት አንድ ቀን ሰላማዊ ሰልፍ ይደረጋል። ሰልፉንም 'ግብታዊ' ሰላማዊ ሰልፍ ሲል ሰይሞታል። አላማውም *የእንስሳ እርሻን ትግልና ድል መዘከር*።

እንስሳቱ በተወሰነላቸው ሰአት ስራቸውን አቋርጠው በወታደራዊ አደረጃጀት በእርሻው ጣቢያ ውስጥ ሰልፍ ይወጣሉ። አሳሞች ሰልፉን ይመራሉ። ፈረሶች ይከተላሉ። ቀጥሎ ላሞች። ከላሞች ኋላ በጎች። ከዚያ ዶርዎችና ዳክዬዎች። ወሾቹ በሰልፉ ግራና ቀኝ እየሄዱ ያስተናብራሉ። ከሰልፈኛው ሁሉ ፊት የሚሆነው የናፖሊዮን ጥቁር አውራ ዶሮ ነበር። ሾኾና እና ቀንድ ተስሎበት ከስሩ "ረጅም እድሜ ለጓድ ናፖሊዮን!" የሚል የተፃፈበትን አረንጓዴ አርማ የሚይዙት ቦክሰርና ክሎቨር ነበሩ። ከሰልፉ ቀጥሎ ስለ ናፖሊዮን ዝና የሚያወሳ ግጥም ይነበባል። የስኩለር መግለጫ ይከተላል። *በተለይ የምግብ ምርት በምን ያህል ፐርሰንት እንደጨመረ የሚያተኩር ገለፃ ነበር የሚያደርገው ስኩለር።* አልፎ፣ አልፎ ጠመንጃ ይተኮሳል።

የግብታዊ ሰላማዊ ሰልፉ ታላቅ ደጋፊዎች በጎች ነበሩ። አንዳንዶች (አሳሞቹና ጠባቂ ውሾች በሌሉበት ጥቂት እንስሳትም እንደሚሉት) ሰላማዊ ሰልፉ ጊዜ ያባክናል፣ በብርድ ላይ ለብዙ ሰአታት ያስቆማል፣ በማለት ማጉረምረም ሲያሰሙ በጎቹ በከፍተኛ ድምፅ "አራት እግሮች ጥሩ፣ ሁለት እግሮች መጥፎ" በማለት ፀጥ እንዲሉ ያደርጋሉ። በአብዛኛው ግን እንስሳቱ ይህንን አከባበር ይወዱታል። ራሳቸው የራሳቸው ጌቶች ስለመሆናቸውና የሚሰሩትና የሚደክሙትም ለራሳቸው መሆኑን የሚያስታውሳቸው በመሆኑ ይመቻቸዋል።

*የስኩለር የኢኮኖሚ እድገት ሊስቶች፣* ነጎድጓዳማው የጠመንጃ ተኩስ፣ የአውራዶሮው 'ኩኩሉሉኩኩኩኩታ' እና የባንዲራው መውለብለብ ተጣምረው ባዶ ሆዳቸውን መሆናቸውን ያስረሷቸዋል፣ ቢያንስ ግማሹን ጊዜ።

እነሆ በሚያዚያ ወር *የእንስሳ እርሻ* ሪፐብሊክ መሆኑ ታወጀ። እናም የሪፑብሊኩን ፕሬዚዳንት መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ። ለውድድር የቀረበው አንድ ተወዳዳሪ ብቻ ነበር፣ ናፖሊዮን። እሱም በሙሉ ድምፅ የሪፑብሊኩ ፕሬዚዳንት ሆኖ ተመረጠ። በዛኑ እለት ስኖውቦል ከጆንስ ጋር ስለነበረው የቆየ መመሳጠር የሚዘረዝር አዲስ ሰነድ መገኘቱ ተገለፀ።

እንስሳቱ እስከዛን ጊዜ እንደሚገምቱት፤ ስኖውቦል በላምበረቱ ጦርነት ስትራቴጂካዊው ግቡ እንዲሸነፉ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፤ ጦርነቱን ይዋጋ የነበረው ከጆንስ ጎን ሆኖ ነበር ተባለ። እንደውም ወራሪውን የሰው ዘር ይመራ የነበረው እሱ ከመሆኑም ሌላ "ሰብአዊነት ለዘላለም ይኑር" የሚለውን የሰው ዘርን የጦርነት መሪ መፈክር ከአንደበቱ አውጥቶ ውጊያውን ያስጀመረው ራሱ ነበር ተባለ። በስኖውቦል ጀርባ ላይ የደረሰው ቁስል (ጥቂቶች እስከ አሁን ያስታውሱታል) በናፖሊዮን ጥርስ የተዘነጠለ እንደ ነበርም ተነገራቸው።

በበጋው አጋማሽ ላይ ሙሴ፤ ጥቁሩ አሞራ፤ ከብዙ አመታት በኋላ በእርሻው ጣቢያ ተገኘ። ምንም አልተለወጠም። አሁንም ስራ አይሰራም። አሁንም በተወጠረ ድምፅ ስለ ሽንኮራአገዳ ተራራ ይሰብካል። በወደቀ ቅርንጫፍ ላይ ሆኖ፤ ጥቋቁር ክንፎቹን እያማታ፤ የሚሰማው ካገኘ ለሰአታት ያለማቋረጥ ይሰብካል።

"እዚያ ላይ ጓዶች" ይላቸዋል ሙሴ በተምስጦ፤ በረጅሙ ሹል አፉ እያመለከታቸው፤ "እዚያ፤ ከምታዩት ጥቁር ዳመና ወዲያ ማዶ፤ እኛ ድሃ እንስሳት ከምድራዊው ድካማችን ለዘላለሙ እረፍት የምናደርግበት የሸንኮራአገዳ ተራራ የሚባል የሀሴት ሀገር ይገኛል።" ሙሴ በዚህ ብቻ አያበቃም። እንደውም በከፍተኛ ምጥቀት ካካሄዳቸው በረራዎች በአንደኛው፤ የሸንኮራአገዳ ተራራን ማየቱንም ይናገራል። "በአደይ አበባ የተዋበ፤ በተልባ ዘር ኬክ የተሞላ፤ ለሽ ያለ ሜዳ እና አንኳር ስኳር የሚበቅሉባቸው ቁጥቋጦዎችን አይቻለሁ" ይላቸዋል።

ብዙሃኑ እንስሳት ሙሴን ያምኑታል። ምክንያቱም ህይወታቸው በአሁኑ ወቅት በረሃብና በአድካሚ ስራ የተሞላ ሆኗል። *መቼም ከዚህ የተሻለ ህይወት ያለበት ስፍራ መኖሩ ተገቢ አይደለምን?*

አሳሞቹ ስለ ሙሴ ያላቸውን አመለካከት መገመት ይከብዳል። ሁሉም በአንድ ድምፅ የሸንኮራአገዳ ተራራ ታሪክ ውዳሴ ከንቱ መሆኑን ተናግረዋል። ነገር ግን በእርሻው ጣቢያ ስራ ሳይሰራ እየሰበከ እንዲኖር ፈቅደውለታል። በቀን አንድ ሽክና ቢራ ቀለብም ተወስኖለታል።

ቦክሰር ሸኾናው ከዳነ ወዲህ ከበፊቱ ይበልጥ ይሰራል። እንደ እውነቱ ከሆነ ሁሉም እንስሳት ያን አመት እንደ ባሪያ ነበር የለፉት። ከመደበኛው እርሻ እና ዊንድሚል ግንባታ በተጨማሪ በመጋቢት ወር የተጀመረውን የወጣቶቹን አሳሞች ትምህርት ቤት ማነፅ ነበረባቸው። አንዳንድ ጊዜ ያለ በቂ ምግብ ለረጅም ሰአታት መስራት ከአቅም በላይ ይሆንባቸዋል። ቦክሰር ግን ፍንክች አይልም። በሚናገረውም ሆነ በሚያደርገው ድርጊት የቀድሞው ጉልበቱ እንዳለ ላለመሆኑ የሚያሳይ ምንም ፍንጭ አልነበረም። ሰውነቱ ብቻ መጠነኛ ለውጥ ይታይበታል። ቆዳው እንደ ቀድሞ አያብረቀርቅም። ታላላቆቹ ሻኛዎቹ የከሱ ይመስላሉ። "በፀደይ ሳር የቦክሰር ሰውነት ይመለሳል" ይላሉ አንዳንዶች ሲያወሩ።

ፀደይ መጣ። የቦክሰር ሰውነት ግን ወደ ቀድሞው ደንዳናነት አልተመለሰም። አንዳንድ ጊዜ ከድንጋይ ማውጫው ጭነት ወደ ላይ ሲጎትትና ጡንቻዎቹ ሲላሉበት፤ ከአካላዊ ብቃቱ ይልቅ መስፈሳዊ ጥንካሬው ነበር የሚስተዋለው። በእንዲህ ያለው ወቅት ከንፈሮቹ "ጠንክሬ እሰራለሁ" በማለት ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ። ድምፅ ለማውጣት ግን አቅሙ እያጠረው ነበር። ቤንጃሚንና ክሎቨር ጤንነቱን እንዲንከባከብ ከመምከር አልቦዘኑም። ሆኖም አይሰማቸውም። አስራ ሁለተኛው የልደት በአሉ እየተቃረበ ሲሆን ለዊንድሚሉ ግንባታ የሚሆን በቂ ድንጋይ ከጡረታው በፊት ማከማቸት እስከቻለ ድረስ ለሌላው ጉዳይ ደንታ አልነበረውም።

በበጋው ወራት አንድ ቀን ምሽት በቦክሰር ላይ ችግር ደርሷል የሚል ድንገተኛ ወሬ በእርሻው ውስጥ ተናፈሰ። ለዊንድሚሉ የሚሆን ድንጋይ ሊጎትት ብቻውን ሄዶ ነበር።

እንደተባለውም ወሬው እውነት ነበር። ብዙም ሳይቆይ ሁለት ርግቦች ዜና ይዘው መጡ፣ “ቦክሰር ወድቋል! በአንድ ጎኑ ተንጋሎ መነሳት አልቻለም!”

የእርሻው ጣቢያ ግማሽ ያህሉ እንስሳት ዊንድሚሉ ወደሚገኝበት ኮረብታ በፍጥነት ሄዱ። አዎ፤ ቦክሰር ወድቋል። በሚጎትተው ጋሪ አጠናዎች መሃል፤ አንገቱ ተመዞ እና ጭንቅላቱን እንኳን ቀና ማድረግ አቅቶት። አይኖቹ ቡዝዝ ብለዋል። ጎኑ በላብ ተጠምቋል። ከአፉ በቀጭኑ ደም ይወርዳል። ክሎቨር ከጎኑ በጉልበቷ ተንበረከከች።

“እንዴት ነህ ቦክሰር?” ስትል ጮኸች።

“ሳንባዬ ነው” አላት ቦክሰር በደከመ ድምፅ። “ምንም አይደል። የዊንድሚሉን ግንባታ እኔም ባልኖር አንቺ ልትጨርሺው ትችያለሽ። በቂ የሆነ ድንጋይ ተከማችቷል። በዛም ሆነ በዚህ ምናልባት የሚቀረኝ እድሜ የአንድ ወር ጊዜ ይሆናል። እውነቱን ልንገርሽና ጡረታ የምወጣበትን ወቅት እየናፈቅሁ ነበር። ቤንጃሚንም እድሜው እየገፋ በመሆኑ ምናልባት ለእሱም የጡረታ መብቱን ቢፈቅዱለት አብረን ጊዜያችንን ማሳለፍ እንችላለን።”

“በአስቸኳይ እርዳታ ማግኘት አለብን” አለች ክሎቨር “አንዳችሁ ፍጠኑና ለስኩለር የሆነውን ንገሩት።”

ሁሉም እንስሳት ለስኩለር ሊናገሩ ወደ ትልቁ ህንፃ ሽመጠጡ። ክሎቨርና ቤንጃሚን ብቻ ቀሩ። ቤንጃሚን ከቦክሰር ጎን ተጋድሞ ምንም ሳይናገር፤ በረጅም ጭራው ዝንቦቹን ይከላከልለታል። ሩብ ሰአት ቆይቶ ስኩለር መጣ። ገፅታው ለቦክሰር የተጨነቀለትና ያሰበለት ይመስላል። “ጓድ ናፖሊዮን እጅግ በጣም ታማኝ ከሆኑት ሰራተኞቹ አንዱ በሆነው በቦክሰር ላይ የደረሰውን ሁኔታ በጠለቀ ሀዘን የተመለከተው ከመሆኑም በላይ ዊሊንግደን በሚገኘው ሆስፒታል ይታከም ዘንዳ አስፈላጊውን ዝግጅት አጠናቋል” አላቸው።

እንስሳቱ የሰሙት ነገር ጎረበጣቸው። ከሞሊና ከስኖውቦል በስተቀር የእርሻ ጣቢያውን እስከ ዛሬ ለቅቆ የሄደ አልነበረም። የታመመው ጓዳቸው በሰው ልጆች እጅ እንዲወድቅባቸው አልፈለጉም። ሆኖም እንደተለመደው ስኩለር ከስጋታቸው አረጋጋቸው። “እዚህ ከሚታከም ይልቅ ዊሊንግደን የሚገኘው የከብት ህክምና ጣቢያ ውስጥ የሚሰራው ቀዶ ጠጋኝ ቦክሰርን በቀላሉ አክሞ ሊያድነው ይችላል” አላቸው።

ከግማሽ ሰአት በኋላ ቦክሰር ተሻለው። ከወደቀበትም እንደምንም ብሎ ተነስቶ እየተንገዳገደ ወደ ማደሪያው ሄደ። ክሎቨርና ቤንጃሚን ለመኝታ የሚሆን ዳጎስ ያለ ሳር ጎዝጉዙለት።

ለሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ቦክሰር ያልጋ ቁራኛ ሆነ። አሳሞቹ ከትልቁ መኖሪያ ቤት መታጠቢያ ክፍል የመድሃኒት መደርደሪያ ላይ ያገኙትን አንድ ትልቅ ሮዝ መልክ ያለውን መድሃኒት ሰደዱለት። ይህንንም በቀን ሁለቴ ከምግብ በኋላ ክሎቨር ትሰጠዋለች። ምሽት ላይ ከጎኑ ተኝታ ታጫውተዋለች። ቤንጃሚንም ዝንቦቹን ይከላከልለታል። ቦክሰር በሆነው ሁሉ እንደማይፀፀት ነገራቸው። ከህመሙ ካገገመ ወደፊት ሶስት አመት ሊኖር እንደሚችል፤ ከግጦሹ መሬት ጥግ በሚገኘው የጡረተኞች ሰፈርም ቀሪ ጊዜውን በሰላም የማሳለፍ ምኞት እንዳለው አጫወታቸው። ይህም ለመጀመሪያ ጊዜ ራሱን የሚያዝናናበት፤ አእምሮውንም የሚያዳብርበት እንደሚሆን እና ቀሪውን ህይወቱን ሃያ ሁለቱን ሆሄያት ለማወቅ እንደሚያውለው ነገራቸው።

ቤንጃሚንና ክሎቨር ከቦክሰር ጋር መሆን የሚችሉት ከስራ መልስ ብቻ ነበር። እንስሳቱ ወደ ስራ እንደተሰማሩ ቀትር ላይ ነበር ቦክሰርን ለመውሰድ የጭነት ጋሪ የመጣው። እንስሳቱ ሁሉ በአሳሞቹ ካቦነት አረም በመንቀል ላይ እያሉ ነበር ቤንጃሚን በከፍተኛ ድምፅ እያናፋና እየጋለበ ከትልቁ ህንፃ በኩል የመጣው። ቤንጃሚንን በስሜት ተወጥሮም ሆነ ሲጋልብ ያዩት ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር።

“ፍጠኑ! ፍጠኑ!” ሲል ጮኸ። “በአስቸኳይ እንሂድ! ቦክሰርን እየወሰዱት ነው!” እንስሳቱ የአሳሞቹን ፈቃድ ሳይጠብቁ ስራቸውን ጣጥለው ወደ ትልቁ ህንፃ ተፈተለኩ። እውነትም ሜዳው ላይ በሁለት ፈረሶች የሚጎተት የጭነት ጋሪ ቆሟል። ጎኑ ላይ ጽሁፍ አለው። መሰሪ ፊት ያለው ሾፌር ባርኔጣ ደፍቶ ተቀምጧል። የቦክሰር ማደሪያ ባዶ ነበር።

እንስሳቱ የጭነት ጋሪውን ከበው “ደህና ሁን ቦክሰር፤ ደህና ሁን!” እያሉ ጮሁ።

“ሞኞች! ሞኞች!” በማለት ጮኸ ቤንጃሚን፤ በትናንሽ ሸኾናዎቹ መሬቱን እየተመተመ። “ሞኞች ሁላ! ከመኪናው ጎን የተፃፈውን ማየት አትችሉምን?”

እዚህ ላይ እንስሳቱ አደብ ገዙ። ፀጥታም ሰፈነ። ሙሬል ሆሄያቱን መቁጠር ጀመረች። ቤንጃሚን ወደ ጎን ገፍቷት፤ እንደ መቃብር በከበደው ፀጥታ መኻል ፅሁፉን አነበበ።

“አልፍረድ ሲመንድ፤ ፈረስ አራጅና ግሉ ቀቃይ፤ ዊሊንግደን፤ የቆዳና የ አጥንት ምግብ ደላላ፤ የውሾች ቤት አምራች” ይህ ምን ማለት እንደሆን አይገባችሁምን? ቦክሰርን ወደ ፈረስ አራጆች ሊወሰዱት ነው።

የሰቆቃ ጩኸት አስተጋባ። በዚህ ሰአት ሾፌሩ ፈረሶቹን በአለንጋ መዥርጦ በሶምሶማ ከግቢው መልቀቅ ጀመሩ። ሁሉም እንስሳት በከፍተኛ ድምፅ እያለቀሱ እቃ መጫኛውን ተከተሉ። ክሎቨር ከፊት ለፊት መሮጥ ጀመረች። እቃ መጫኛው ፍጥነቱን ጨመረ። ክሎቨርም በግልቢያ ልትደርስበት ሞከረች። ከጎን ጎኑ እየጋለበችም “ቦክሰር! ቦክሰር! ቦክሰር!” እያለች ተጣራች። ቦክሰር ውጪ በመካሄድ ላይ ያለውን ትርምስ የሰማ ይመስል ከግንባሩ እስከ አፍንጫው የሚወርደውን ነጭ መስመር የያዘ ፊቱን ከመጫኛው ጋሪ ጀርባ ባለው መስኮት በኩል ብቅ አደረገ።

“ቦክሰር” ስትል በሚያስፈራ ድምፅ ጮኸች ክሎቨር “ቦክሰር በአስቸኳይ ውጣ፤ ሊገድሉህ እየወሰዱህ ነው!”

ሁሉም እንስሳት “ቦክሰር ውጣ! ቦክሰር ውጣ!” እያሉ በአንድ ድምፅ ያስተጋቡ ጀመር። ነገር ግን እቃ መጫኛው እየፈጠነና እየራቃቸው ነበር። ቦክሰር ክሎቨር የተናገረቻችውን ስለመረዳቱ ምንም ፍንጭ አልነበረም። ሆኖም ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፊቱ ከትንሹ መስኮት ጠፍቶ በምትኩ የርግጫ ድምፅ ከውስጥ ይሰማ ጀመር። ራሱን ነፃ ለማውጣት እየሞከረ ነበር። የቦክሰር ሸኾና ጥቂት ምቶች እንዲህ ያለውን መጫኛ ብትንትኑን የሚያወጡበት ጊዜ ነበር። ግና አበቃ! ጉልበቱ ክዶታል። እናም ጥቂት ኳኳታ ተሰምቶ የቦክሰር ሸኾና ድምፅ ፀጥ አለ።

እንስሳቱ መላው ቢጠፋቸው እቃ መጫኛውን የሚጎትቱትን ፈረሶች ይማፀኑ ገቡ። “ጓዶች፤ ጓዶች” በማለት ጮኹ። “የገዛ ወንድማችሁን ወደ ሞቱ አትውሰዱት”። ነገር ግን ደደቦቹ ጨካኞች እየተካሄደ ያለውን ነገር መገንዘብ ተስኗቸው፤ ጆሮዎቻቸውን ወደ ጋማቸው ቀልብሰው ፍጥነታቸውን ጨመሩ።

የቦክሰር ፊት ዳግም ወደ መስኮቱ አልተመለሰም። ከመኻከላቸው አንዱ የግቢውን አጥር ትልቁን በር ፊጥኖ በመሄድ ለመዝጋት አስቦ ነበር። ዘገየ። እቃ መጫኛው በዛው ደቂቃ ውስጥ የግቢውን አጥር በር አልፎ የመንገዱን ቁልቁለት ይዞ ከነፈ። እነሆ ቦክሰር ዳግም አልታየም።

አንድ ፈረስ ሊያገኝ የሚችለው የህክምና ርዳታ ቢደረግለትም፣ ከሶስት ቀን በኋላ ቦክሰር ዊሊንግደን ሆስፒታል ውስጥ ማረፉ ተነገረ። ዜና ረፍቱን ለእንስሳቱ ሊያረዳ የመጣው ስኩለር ነበር። "በቦክሰር የመጨረሻዎቹ የህይወት ሰአታት ውስጥ አብሬው ነበርኩ" አላቸው።

"በህይወቴ ሙሉ አጋጥሞኝ የማያውቅ ስሜታዊ ምሽት ነበር" አለ ስኩለር የፊት እግሩን አንስቶ ዘለላ እንባ ከአይኑ እየጠረገ። "እስከ መጨረሻው ደቂቃ ከራስጌው አልተለየሁም። በመጨረሻም፣ እጅግ በደከመ ለሆሳስ ድምፅ፣ በህይወቱ የሚያዝነው ዊንድሚሉ ሳይጠናቀቅ በመሞቱ እንደሚሆን በጆሮዬ ነገረኝ። 'ወደፊት ጓዶች' ሲል አንሾካሾከልኝ '**በእመፁ** ስም ወደ ፊት! *የእንስሳ እርሻ* ለዘላለም ይኑር! ናፖሊዮን ሁሌም ትክክል ነው!' ነፍሱ ከስጋው ከመለየቷ በፊት የተናገራቸው ቃላት እኒህ ነበሩ፣ ጓዶች"

ይህንን ተናግሮ ሲያበቃ የስኩለር ገፅታ ተቀይሮ ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ተዋጠ። እነዛ ትናንሽ አይኖቹ ከግራ ወደ ቀኝ እየተራወጡ እንስሳቱን በጥርጣሬ ተመለከታቸው። ዘግየት ብሎም ንግግሩን ቀጠለ።

"ቦክሰር በተወሰደበት ወቅት ደካማና ርባና የሌለው ሀሜት እንደተናፈሰ ተረድቻለሁ" ሲል ጀመረ ስኩለር። "አንዳንድ እንስሳት ቦክሰርን የወሰደው መጫኛ 'ፈረስ አራጅ' የሚል ፅሁፍ እንደ ነበረው አስተውለዋል። ከዚህ ተነስተው ቦክሰር ለፈረስ አራጆች ተሰጥቷል በማለት ችኩል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል። እንዴት ያለ ደደብ እንስሳ እንዲህ ያለ ከንቱ ማጠቃለያ ላይ ሊደርስ እንደ ቻለ ይገርማል። እንደ እውነቱ ከሆነ ተወዳጁ መሪያችንን፣ ጓድ ናፖሊዮንን፣ ከዚህ በተሻለ አያውቁትምን?" ሲል ጮኸ ስኩለር፣ ጭራውን ሽው ሽው እያደረገና ከጎን ወደ ጎን እየነጠረ። ማብራሪያው እጅግ ቀላል ነበር። እቃ መጫኛው ቀድሞ የፈረስ አራጅ ንብረት የነበረ ሲሆን ኋላ የእንስሳት ሀኪሙ ገዛው። ነገር ግን ሀኪሙ የቀድሞውን ስም ገና አልለወጠውም ነበርና ስህተቱ የመነጨው ከዚህ የተነሳ ነበር።

እንስሳቱ ይህንን በመስማታቸው እንዳች ጭነት ከትከሻቸው ላይ የወረደላቸው ይመስል ተነፈሱ። ስኩለር ስእላዊ ገለጣውን በመቀጠል፣ ስለ ቦክሰር ህልፈተ - ህይወት የመጨረሻ ሰአት፣ እጅግ የሚያስመሰግን የህክምና እርዳታ ስለማግኘቱ፣ ናፖሊዮን ለአንዲትም ደቂቃ ስለ ወጪው ሳይጨነቅ ውድ የሆኑ መድሃኒቶች ተገዝተው እንዲታከም ስለማድረጉ በነገራቸው ጊዜ ጥርጣሬያቸው ሁሉ ተወግዶላቸው፣ በጓዳቸው ሞት ተሰምቷቸው የነበረው ጥልቅ ሀዘን ቢያንስ በህልፈቱ
ወቅት በደስታ ከዚህች አለም መለየቱን ማወቅ በመቻላቸው የሀዘናቸውን መጠን አቀለለላቸው።

በቀጣዩ እሁድ ጠዋት እራሱ ናፖሊዮን ስብሰባ ላይ በመገኘት ስለ ቦክሰር ክብር አጭር የሀዘን መግለጫ ንግግር አደረገ። በሀዘን የተኮማተሩለትን ጓዳቸውን ሬሳ ለቀብር ማምጣት እንዳልተቻለና በምትኩ ከትልቁ ቤት የአትክልት ስፍራ የተዘጋጀው ጉንጉን አበባ በመቃብሩ ላይ እንዲቀመጥ ማስደረጉን ነገራቸው። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ አሳሞቹ ለቦክሰር መታሰቢያ የእራት ግብዣ የሚያደርጉ መሆናቸውንም ገለፀላቸው። ናፖሊዮን ንግግሩን የደመደመው በሁለቱ የቦክሰር እምነት መመሪያዎች ነበር። "የበለጠ ጠንክሬ እሰራለሁ" እና "ጓድ

ናፖሊዮን ሁሌም ትክክል ነው" በሚሉት። "እኒህን የቦክሰር እምነት መመሪያዎች" አለ ናፖሊዮን "ሁሉም እንስሳት የራሳቸው መመሪያዎች አድርገው ሊወስዷቸው ይገባል።"

የመታሰቢያ ግብዣ ይደረጋል በተባለበት ቀን ከዊሊንግደን የመጣ የእቃ መጫኛ አሳሞቹ መኖሪያ ግቢ ውስጥ በእንጨት ሳጥን የታሸገ ትልቅ እቃ አስረከበ። የዛን እለት ምሽት ድብልቅልቅ ያለ ዘፈን ከአሳሞቹ መኖሪያ ተሰማ። ዘግይቶም የዘፈኑ ድምፅ ሀይለኛ በሆነ አምባጓሮ ተተካ። አስራ አንድ ሰአት ገደማ ሲሆን እንደ ፈንጂ በጮኸ የብርጭቆ መሰበር ድምፅ ብጥብጡ ፀጥ እረጭ አለ። በማግስቱ እስከ እኩለ ቀን ድረስ በህንፃው ውስጥ ከሚኖሩት አሳሞች የተንቀሳቀሰ ነፍስ አልታየም። በእርሻው ጣቢያ እንደሚወራው ከሆነ አሳሞቹ በሆነ ምክንያት ወይም ከሆነ ቦታ ባገኙት ገንዘብ ሌላ የውስኪ ሳጥን ለራሳቸው ገዝተው አስመጥተው ነበር።

# ምእራፍ አስር

## ሁሉም እንስሳት እኩል ናቸው፤ ነገር ግን . . .

እነሆ አመታት አለፉ። ወቅቶች ይመጣሉ፣ ይሄዳሉ። የእንስሳቱ አጭር የህይወት ዘመንም ይነጉዳል። ከክሎቨር፣ ከቤንጃሚን፣ ከጥቁሩ አሞራ ሙሴ፣ እና ከ አሳሞቹ በስተቀር **ከአመፁ** በፊት ስለነበረው ዘመን የሚያስታውስ የለም።

ሙሬል ሞታለች። ብሉቤል፣ ጄሲ እና ፒንችር ሞተዋል። ጆንስ ሞቷል። ሌላ ክፍለ ሀገር ጡረተኞች መንደር ውስጥ ነበር የሞተው። ስኖውቦል ተረስቷል። ቦክሰር ተረስቷል - በቅርብ ከሚያውቁት ጥቂቶች በስተቀር። ክሎቨር አርጅታለች። ሰውነቷ ይንቋቋል። አይኖቿን ይጋርዳት ጀምሯል። በጡረታ መገለል ከነበረባት ዘመን ሁለት አመት አልፏታል። እንደውም እስከ ዛሬ ጡረታ የወጣ እንስሳ የለም። ለተጧሪዎች የሚያገለግል የግጦሽ መሬት ይከለላል ተብሎ የነበረው ሀሳብ ውድቅ ከተደረገ ቆይቷል።

ናፖሊዮን በጎልማሳ እድሜ ላይ የሚገኝ አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ኪሎ ግራም የሚመዝን አሳማ ሆኗል። ስኩለር ከመወፈሩ የተነሳ አይኖቹ የጠፉ ይመስላሉ። ቤንጃሚን ብቻ ነበር ብዙም ያልተለወጠው - አፉ አካባቢ ያለው ጢም ከመሸበቱ በስተቀር። ከቦክሰር ሞት ወዲህ ይበልጥ ሀዘንተኛና ይበልጥ ዝምተኛ ሆኗል።

በአሁኑ ዘመን ብዙ ፍጥረታት በእርሻው ጣቢያ ይኖራሉ። የቁጥራቸው ብዛት ግን ድሮ ተገምቶ እንደነበረው አይደለም። **ከአመፁ** ወዲህ ለተወለዱት በርካታዎቹ **አመፁ** በወሬ ወሬ የሚሰሙት የደበዘዘ የድሮ ዘመን ታሪክ ሆኗል። ተገዝተው ወደ እርሻው ጣቢያ ለመጡት ለሌሎቹ ደግሞ እንዲህ ያለ ነገር (**አመፅ**) መደረጉንም የሰሙት እዚህ ከመጡ በኋላ ነበር። ከክሎቨር ሌላ እርሻው ሶስት ፈረሶች አሉት። ጠንካሮች፣ የስራ ፍላጎት ያላቸውና መልካም ጓዶች የሆኑ ፈረሶች ነበሩ፤ ግን ደደቦች። የትኛቸውም ከ'ቢ' በላይ ያሉትን ሆሄያት መማር አልቻሉም። ስለ **አመፁ**ና ስለ እንስሳዊነት መርሆ በተለይ የማያወላውል ከበሬታ ካላቸው ከክሎቨር የሰሙትን በሙሉ አምነው ተቀብለዋል። ይሁንና የተነገራቸውን ጠንቅቀው ስለ መገንዘባቸው በእጅጉ ያጠራጥራል።

እርሻው አሁን ይበልጥ ሀብታም ሆኗል። የተሻለ አደረጃጀትም አለው። ከአቶ ፒልኪንግተን በተገዙ ሁለት ሰፋፊ መሬቶች ሳቢያ ከበፊቱ ይበልጥ አድጓል። ዊንድሚሉ በአርኪ ሁኔታ ተገንብቶ አልቋል። አሁን እርሻው የመውቂያ መሳሪያ እና የደረቀ እስር ሳር

ማንሻ ባለቤት ሆኗል። በርካታ አዳዲስ ህንፃዎችም ተገንብተዋል። ዊምፐር ለራሱ ጋሪ ገዝቷል።

ዊንድሚሉ ጥቅም ላይ የዋለው ግን የኤሌክትሪክ ሃይል ለማመንጨት አልነበረም። ለበቆሎ ወፍጮነት እያገለገለ ሲሆን፣ ይህም ዳጎስ ያለ የገንዘብ ማግኛ ምንጭ ሆኗል። እንስሳቱ ሌላ ዊንድሚል ግንባታ ላይ ደፋ ቀና ማለት ጀምረዋል። እንደሚወራው ከሆነ የተጀመረው ዊንድሚል ሲጠናቀቅ ዳይናሞ ይገባለታል።

ከብዙ ዘመን በፊት ስኖውቦል እንስሳቱ ተድላና ፍሰሀ የሞላበት ብሩህ ህይወት እንዲያልሙ አስተምሯቸው ነበር። "ዊንድሚሉ ሲጠናቀቅ በረቶች ሁሉ መብራት ይገባላቸዋል፣ ቀዝቃዛና ሙቅ ውሃ ይኖራችኋል፣ በሳምንት የምትሰሩት ሶስት ቀናት ብቻ ይሆናል" ብሏቸው ነበር። ዛሬ ይህንን ጉዳይ የሚያነሳው ከቶም የለም። ናፖሊዮን "እንዲህ ያሉ ሀሳቦች ከእንስሳዊነት መንፈስ ጋር ተፃራሪዎች ናቸው" በማለት አውግዟል። "እውነተኛ ደስታ የሚገኘው" አላቸው ናፖሊዮን "ጠንክሮ በመስራትና በቁጠባ በመኖር ነው።"

*ከአሳሞቹና ከጠባቂ ውሾቹ በስተቀር እንስሳቱ እየደኸዩ እርሻው ግን በሀብት ላይ ሀብት እየጨመረ በማደግ ላይ ነበር።* ምናልባት ለዚህ ምክንያት አያሌ አ ሳሞችና ጠባቂ ውሾች በመኖራቸው ሊሆን ይችላል። እኒህ ፍጡራን ስራ አይሰሩም ማለት አልነበረም፣ እንደየምድባቸው መስራታቸው አልቀረም።

ስኩለር ያለ መታከት እንደሚገልፅላቸው ከሆነ እርሻውን በመቆጣጠርና በማደራጀት ረገድ ማለቂያ የሌለው ስራ አለ። የዚህን የስራ ዘርፍ አብዛኛውን ክፍል እንስሳቱ ለመገንዘብ ከእውቀታቸው በላይ ነበር። ለምሳሌ ስኩለር እንደነገራቸው ከሆነ አሳሞቹ በየቀኑ 'ፋይል'፣ 'ሪፖርት'፣ 'ቃለ ጉባኤ' እና 'ማስታወሻ' በተባሉ ለእነሱ ግልፅ ባልሆኑ ምስጢራዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ጉልበት ያጠፋሉ። እነዚህ ማለት እንግዲህ በላያቸው ላይ ፅሁፍ ያላቸው ረጃጅም ወረቀቶች ነበሩ። ወረቀቶቹ ከተፃፉባቸው በኋላ ይቃጠላሉ። ይህ ስራ ለእርሻው ጣቢያ እድገት ከፍተኛ የሆነ አስፈላጊነት ያለው ተግባር ስለመሆኑ ስኩለር ገልፆላቸዋል።

ይሁንና አሳሞቹም ሆኑ ጠባቂ ውሾቹ በላባቸው ያመረቱት አንዳችም ምግብ ኖሮ አያውቅም። *ቁጥራቸው ብዙ ሲሆን፣ የመብላት አቅማቸው ደግሞ እጅግ ከፍተኛ ነበር።*

ሌሎቹን እንስሳት በተመለከተ፣ ህይወታቸውን እስከሚያውቁት ድረስ ከቀድሞው ህይወት የተቀየረ ነገር አልነበረም። አብዛኛውን ጊዜ ይራባሉ። ደረቅ ሳር ላይ ይተኛሉ። ውሃ ከገንዳ ይጠጣሉ። በእርሻው ላይ ሲማስኑ ይውላሉ። የክረምት ቁር ያኮማትራቸዋል። በበጋው ደግሞ ዝንቦች ይወሯቸዋል። ከመካከላቸው አዛውንቶቹ አንዳንዴ ወደ ኋላ መለስ ብለው **አመፁ** እንደፈነዳ፣ ጆንስ በተባረረ ማግስት ስለነበረው ህይወት እያሰላሰሉ፣ አሁን ከሚኖሩት ህይወት የተሻለ ወይስ የከፋ እንደነበር ለማስታወስ ይጥራሉ። ግን ማስታወስ አይችሉም።

*ከጊዜ ወደ ጊዜ እድገትና መሻሻል መምጣቱን ከሚዘረዝሩት የስኩለር አሃዛዊ ሊስቶች በስተቀር አሁን የሚኖሩትን ህይወት ሊያነፃፅሩ የሚችሉበት ምንም ነገር አልነበራቸውም።*

ሽማግሌው ቤንጃሚን ብቻ የረዥም እድሜውን ህይወት እያንዳንዱን ጉዳይ እንደሚያስታውስ ተናግሯል። "ህይወት እንደሆን ከዚህ ተሽላም ሆነ ጎምዝዛ እንደማታውቅ ጠንቅቄ አውቃለሁ" ይላል። "ረሀብ፣ እንግልትና ተስፋ ማጣት የማይለወጡ የህይወት ህግጋት ናቸው" በማለትም ተናግሯል።

ይህም ሆኖ እንስሳቱ ከቶም ተስፋ አልቆረጡም። *የእንስሳ እርሻ* አካል በመሆናቸው የሚሰማቸው ክብር እና ልዩ ስሜት ለቅፅበት እንኳን አልጠፋም። በድፍን ሀገር - በመላው እንግሊዝ! - በእንስሳት የተያዘና በእንስሳት የሚተዳደር እርሻ የእነሱ ብቻ ነበርና። ከመካከላቸው የትኛውም፣ ወጣቶቹም እንኳን ቢሆኑ ወይም ከአስርና ከሃያ ማይልስ ርቀት ላይ ተገዝተው የመጡት አዳዲሶቹም እንኳን ሳይቀሩ፣ *የእንስሳ እርሻን* ከማድነቅ ተቆጥበው አያውቁም።

ጠመንጃቸው ሲተኮስ ሲሰሙና አረንጓዴ ባንዲራቸው ሲውለበለብ ሲመለከቱ ልባቸው መቼም በማይሞት ኩራት ይሞላል። ወሬውም ተቀይሮ ስለ ጥንቱ የአርበኝነት ጊዜ፣ ስለ ጆንስ መባረር፣ ስለ ሰባቱ ትእዛዛት ድንጋጌ እና ወራሪዎቹ የሰው ልጆች ድል ስለሆኑበት ስለ ታላቁ ጦርነት - ይሆናል።

የጥንቱን ህልማቸውን ዘንድሮም አልረሱም። አዛውንቱ ሜዠር ተንብዮላቸው የነበሩት - የእንስሳት ሪፑብሊክ የመመስረቱና አረንጓዴዎቹ የእንግሊዝ ሜዳዎች ሁሉ ከሰው ልጆች ቁጥጥር ነፃ የመሆናቸው ጉዳይ ዛሬም ይታመንባቸዋል። አንድ ቀን እውን ይሆናል። በቅርቡ ላይሆን ግን ይችላል። ምናልባትም ዛሬ በህይወት በሚገኙት እንስሳት እድሜ ውስጥም ላይሆን ይችል ይሆናል። ነገር ግን እውን መሆኑ አይቀሬ ነው። ምናልባት 'የእንግሊዝ አራዊት' መዝሙር ሳይቀር እዚህና እዚያ በድብቅ ሳይዜም አይቀርም። ምንም እንኳን የትኛቸውም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለመዘመር ባይደፍሩም፣ በእርሻው ጣቢያ የሚኖሩት እንስሳት ሁሉ መዝሙሩን ስለማወቃቸው ግን የሚያጠራጥር ነገር አልነበረም።

ህይወታቸው ከባድና ህልማቸውም ሁሉ እውን አልሆነ ይሆናል። ነገር ግን እነሱ ከሌሎች እንስሳት የተለዩ መሆናቸውን ያውቃሉ። ቢራቡ፣ ጨቋኝ የሰው ልጆችን በመቀለባቸው አልነበረም። ቢለፉ፣ ቢያንስ የሚደክሙት ለራሳቸው ነበር። ከመካከላቸው የትኛውም ፍጡር በሁለት እግሩ ቆሞ አልሄደም። የትኛውም እንስሳ ሌላውን 'ጌታዬ' ብሎ አይጠራም። *ሁሉም እንስሳት እኩል ነበሩ!*

በበጋው ወቅት አንድ ቀን ስኩለር በጎቹ እንዲከተሉት አዟቸው ከእርሻው ጣቢያ አንደኛው ወገን ወደ ሚገኘው የማይጠቀሙበት መሬት ይዟቸው ሄደ። ቦታው በሰንሰል የተሞላ ነበር። በስኩለር ካቦነት በጎቹ የሰንሰሉን ቅጠል ሲቀረድዱና ሲግጡ ዋሉ። ሲመሽ እሱ ወደ ትልቁ ህንፃ ሲመለስ እነሱን ግን ባሉበት እንዲያድሩ ነገራቸው፣ ምሽቱ ሞቃት ነበርና። እነሆ በጎቹ ለአንድ ሳምንት እዛው ቆዩ፣ ሌሎቹ እንስሳት የት እንዳሉ ሳያውቁ። አብዛኛውን ሰአትም ስኩለር አብሯቸው ነበር። እንደ ስኩለር ገለፃ ለበጎቹ ፀጥታ በሚያስፈልግበት ቦታ አዲስ መዝሙር እያስተማራቸው ነበር።

በጎቹ በተመለሱ ሰሞን በአንድ የደስ ደስ ባለው ምሽት ወቅት፣ እንስሳቱ የቀን ስራቸውን ጨርሰው ወደ ህንፃዎቹ በመጓዝ ላይ እንዳሉ፣ የሚያስፈራ የፈረስ ጩኸት ሜዳውን አቋርጦ ተሰማ። እንስሳቱ በድንጋጤ በያሉበት ቆሙ። የክሎቨር ድምፅ ነበር። እንደገና ጮኸች። ይሄኔ ሁሉም እንስሳት ወደ ሜዳው ሸመጠጡ። እናም ክሎቨር ያየችውን እነሱም ተመለከቱ።

*አሳማ ቆሞ እየተራመደ ነበር።*

አዎ ስኩለር። ያንን የሚያህል ሰውነቱን በአቋቋሙ መደገፍ ያልቻለ በሚመስል መልኩ፣ ሆኖም አንዳች ሳይንገዳገድ ሚዛኑን በመጠበቅ ሜዳውን እየተራመደ አቋረጠ። ጥቂት ደቂቃዎች ቆይቶ ከትልቁ ህንፃ ውስጥ አያሌ አሳሞች በሰልፍ ወጡ። ሁሉም በሁለት የኋላ እግሮቻቸው ቆመው ነበር የሚራመዱት። አንዳንዶቹ ከሌሎቹ በበለጠ አረማመዱን

ተክነውታል። አንድ፣ ሁለቱ እንደ መንገዳገድ ቢያደርጋቸውምና የድጋፍ ከዘራ የሚያስፈልጋቸው ቢመስሉም ቅሉ፣ ሁሉም ሜዳውን በአመርቂ ሁኔታ ዞሩ።

በመጨረሻ በሚያስገመግም የውሾች ጩኸትና የጥቁሩ አውራ ዶሮ 'ኩኩሉኡኡኡኡኡ'ታ ታጅቦ፣ ግርማ ሞገስን በተላበሰ ቀጥ ያለ አቋቋም በሁለት የኋላ እግሮቹ ቆሞ፣ ግራና ቀኙን በቀብራራ አመለካከት እየቃኘና ጠባቂዎቹ ውሾች ዙሪያውን እያደገደጉ ናፖሊዮን ብቅ አለ።

*በፊት እግሩ ጣቶች መኻል አለንጋ ይዟል።*

አስፈሪ ፀጥታ ሰፈነ። እንስሳቱ በመደነቅና በመረበሽ አንድነት ተጠጋግተው ሜዳውን በዝግታ በመዞር ላይ የነበሩትን የአሳሞቹን ረጅም ሰልፍ ሲመለከቱ ሰማይና ምድር የተደባለቁ መሰላቸው። የመጀመሪያው የድንጋጤ ማእበል እንዳለፈላቸው - ውሾቹን ቢፈሯቸውምና በአመታት ሂደት ባካበቱት ልምድ የልብን አለመናገርና ፍፁም ያለመገሰፅ ቢጠናወቷቸውም - የፈለገው ነገር ቢከተል እንኳን - ሳይታወቃቸው የተቃውሞ ቃል መሰንዘራቸው አይቀርም ነበር። ታዲያ ልክ በዚህ ጊዜ ልዩ ምልክት እንደተላለፈላቸው ሁሉ፣ ሁሉም በጎች በአንድነትና በከፍተኛ ድምፅ እንደሚከተለው ያስተጋቡ ጀመር።

"አራት እግሮች ጥሩ፣ ሁለት እግሮች *የተሻሉ! አራት* እግሮች ጥሩ፣ ሁለት እግሮች *የተሻሉ!* አራት እግሮች ጥሩ፣ ሁለት እግሮች *የተሻሉ!"*

ያለ ማቋረጥ አዲሱን መፈክር ለአምስት ደቂቃ አወረዱት። በጎቹ ባቆሙበት ሰአት ተቃውሞ የማሰሚያው እድል አክትሞለት ነበር፣ ምክንያቱም አሳሞቹ በሰልፍ ወደ መኖሪያ ህንፃቸው ተመልሰው ገብተዋልና።

ቤንጃሚን ትከሻው ሲጎነተል ተሰማው። ፊቱን አዞረ። ክሎቨር ነበረች። ያረጁት አይኖቿ ይበልጥ የደበዘዙ መሰሉ። ምንም ሳትናገር ምልክት አሳይታው ሰባቱ ትእዛዛት ወደ ተፃፉበት ትልቁ መጋዘን ወሰደችው።

"የማየት አቅሜን እያጣሁ ነው" አለች በመጨረሻ። "ወጣት እያለሁ እንኳን እዛ ላይ የተፃፉትን ማንበብ አልችልም ነበር። ግን ግርግዳውን ስመለከተው አሁን የተለየ መስሎ ይታየኛል። ሰባቱ ትእዛዛት ቀድሞ እንደነበሩ ናቸው እንዴ ቤንጃሚን?"

ቤንጃሚን ለመጀመሪያ ጊዜ የራሱን የዝምታ ህግ ለመስበር ወሰነ። እናም ግርግዳው ላይ የተፃፈውን አነበበላት። በዚያ ግርግዳ ላይ ከአንድ ትእዛዝ በስተቀር ሌላ ትእዛዝ አልነበረም። እንዲህ ይላል -

***ሁሉም እንስሳት እኩል ናቸው***
***ነገር ግን ጥቂት እንስሳት ከሌሎች ይበልጥ እኩል ናቸው።***

እነሆ ከዚህ በኋላ በማግስቱ አሳሞቹ በሙሉ አለንጋ ይዘው በካቦነት የሚያሰሩዋቸውን እንስሳት መቆጣጠር መጀመራቸው አስገራሚ አልሆነም። ሬዲዮ ለራሳቸው መግዛታቸው፣ ቴሌፎን ለማስገባት መዋዋላቸው፣ 'ጆን ቡል'፣ 'ቲት ቢትስ' እና 'ዴይሊ ሚረር' የተባሉ መፅሄቶችንና ጋዜጦችን ማዘዛቸው ሲታወቅ አዲስ ነገር አልሆነም። ናፖሊዮን በትልቁ ህንፃ የአትክልት ስፍራ ፒፖ ይዞ እያጨሰ ሲንጎራደድ መታየቱ የሚያስገርም አልሆነም። አሳሞቹ የጆንስን ልብሶች ከቁምሳጥን አውጥተው ሲለብሱ፣ ናፖሊዮን ራሱ ጥቁር ኮትና ከጉልበቱ በታች የቆዳ የሆነ ሱሪ ለብሶ፣ ከሌሎቹ አሳሚቶች ይበልጥ የሚያቀርባት አሳሚት ደግሞ ወ/ሮ

ጆንስ ዘወትር እሁድ ትለብስ የነበረውን የሀር ቀሚስ አጥልቃ መታየታቸው አስደናቂ ክስተት አልሆነም። በፍፁም።

ይህ በሆነ በሳምንቱ አንድ ቀን ቀትር ላይ በርካታ ጋሪዎች ወደ እርሻው ጣቢያ መጡ። ለጉብኝት የተጋበዙት የጎረቤት ገበሬዎች ልኡካን ነበሩ። አሳሞቹ እርሻውን እያዘዋወሩ አስጎበኟቸው። ጎብኚዎቹም በተመለከቱት ሁሉ መደነቃቸውን ገለፁ። በተለይ ደግሞ በዊንድሚሉ። እንስሳቱ አረም ላይ ነበሩ። ካቀረቀሩበት ገፅታዎቻቸውን ቀና ሳያደርጉ በጥንቃቄ ነበር የሚሰሩት። ጎብኚዎቹን የሰው ዘር ይሁን ወይም አሳሞቹን፣ ከሁለቱ የትኛቸውን ይበልጥ እንደፈሩ ግን አያውቁም።

ያን ምሽት ከፍተኛ ሳቅና ቅልጥ ያለ ዘፈን አሳሞቹ ከሚኖሩበት ህንፃ ተሰማ። እንስሳቱ የተቀየጡ ድምፆችን ሲሰሙ ምንነቱን የማወቅ ስሜት አደረባቸው። እዚያ ህንፃ ውስጥ ምን በመካሄድ ላይ ይሆን? እንስሳትና የሰው ዘር ለመጀመሪያ ጊዜ በእኩልነት ስብሰባ ተቀምጠዋልን? ሁሉም እንስሳት ኮሽታ ሳያሰሙ ወደ ትልቁ ግቢ የአትክልት ስፍራ ሄዱ።

ከአጥሩ በር ሲደርሱ በጥርጣሬ ቆሙ። ግማሽ ልባቸው ፈራ። ክሎቨር ግን አበረታታቻቸው። ወደ ትልቁ ቤትም ድምፃቸውን አጥፍተው ቀረቡ። ረጃጅሞቹ እንስሳት በምግብ ቤቱ መስኮት በኩል አሾልቀው ተመለከቱ።

አዎ፣ እዚያ ክብ የምግብ ጠረጴዛ ዙሪያ ግማሽ ደርዘን ሰዎች እና ብዙ የአሳማ ባለስልጣናት ተቀምጠዋል። ናፖሊዮን የተቀመጠው የክብር ወንበር ላይ ሲሆን አሳሞቹ በሙሉ አቀማመጣቸው በተዝናና መንፈስ ነበር። ተሰብሳቢዎቹ በካርታ ጨዋታ እየተዝናኑ ነበር። ጨዋታቸውን አቋርጠው የደስ ደስ መጠጥ ሊጠጡ ተነሱ። ትልቅ ማንቆርቆሪያ እየተዘዋወረ ብርጭቆዎቻቸውን በቢራ ይሞላሉ። በመስኮቱ በኩል በመደነቅ የሚመለከቷቸውን እንስሳት ግን ያስተዋለ አልነበረም።

አቶ ፒልኪንግተን፣ የፎክስዉድ ባለቤት፣ ብርጭቆውን እንደጨበጠ ተነሳ። ዘግየት ብሎ ተሰብሳቢዎቹን ለደስ ደስ ብርጭቆዎቻቸውን እንዲያጋጩ እንደሚጋብዛቸው ተናገረ። ይህ ከመሆኑ በፊት ግን መናገር ያለበት ጥቂት ነገሮች እንዳሉት ገለፀላቸው።

“ታላቅ የመንፈስ እርካታ አግኝቻለሁ፣ እርግጠኛ ነኝ እኔ ብቻ ሳልሆን እዚህ የተገኙት ሁሉ” ሲል ጀመረ። “ለረጅም ዘመን በመካከላችን የቆየው ያለ መተማመንና ያለመግባባት በመጨረሻ አብቅቷል። እኔም ሆንኩ ሌሎች እዚህ የተገኙት ልኡካን ሙሉ ለሙሉ የምንጋራው አመለካከት ነበር ለማለት ቢያዳግትም፣ ከዚህ በፊት በነበረው ዘመን የተከበረው *የእንስሳ እርሻ* አስተዳዳሪ ይታይ የነበረው በጠላትነት ነበር ማለት ባልችልም፣ ነገር ግን በተወሰነ ደረጃ በሰው ልጆች ጎረቤቶቹ በጥርጣሬ አይን ይታይ ነበር። አላስፈላጊ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። የተሳሳቱ ሀሳቦች ተንሸራሽረዋል። የአሳሞች ንብረት የሆነና በአሳሞች የሚተዳደር እርሻ መኖሩ ታይቶ የማይታወቅ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በጎረቤቶቹ ላይ ያለመረጋጋትንም ያስከትላል የሚል ፍራቻም አሳድሮ ነበር። ብዙዎቹ ገበሬዎች እንደገመቱት፣ በአግባቡ ምርምር ሳያደርጉ፣ በእንዲህ ያለ እርሻ ውስጥ ስርአተ አልበኝነትና ለህግ ተገዢ አለመሆን ይሰፍናል ብለው ነበር። የዚህ እርሻ ህልውና እነሱ በሚያስተዳድሯቸው እንስሳት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ቀጥረው በሚያሰሯቸው የሰው ልጆች ላይም ተፅእኖ ያስከትላል በማለት ሰግተው ነበር። እነሆ ያ ሁሉ ጥርጣሬ ዋጋ ቢስ ሆኖ ተገኘ።” አለ ፒልኪንግተን።

በአቶ ፒልኪንግተን እምነት፣- ዛሬ እሱና ጓደኞቹ *የእንስሳ እርሻን* እያንዳንዱን ስንዝር ተዘዋውረው በአይናቸው በብሌኑ መርምረዋል። እና ምን አገኙ? እጅግ ዘመናዊ የሆነ

የአስተዳደር ዘዴ ያለው ብቻ ሳይሆን ዲሲፕሊኑና ተዋረዳዊ አሰራሩ በየትኛውም ስፍራ ለሚገኙ ገበሬዎች ምሳሌ ሊሆን የሚገባው እርሻ መሆኑንም መረዳት ችለዋል።

በበኩሉ ከጉብኝቱ እንደ ተገነዘበው፣- *በእንስሳ እርሻ* የሚገኙት ዝቅተኞቹ እንስሳት በመላ ሀገሪቱ ከሚገኙት አቻዎቻቸው ይበልጥ የሚሰሩና አነስተኛ ምግብ የሚያገኙ ናቸው ብሎ ያምናል። እሱና ሌሎቹ ልኡካን ዛሬ የተመለከቷቸውን አያሌ ጠቃሚ የአሰተዳደ መንገዶችን ሳይውሉ ሳያድሩ በየእርሻዎቻቸው ተግባራዊ ያደርጋሉ።

*"ንግግሬን የማጠቃልለው"* አለ ፒልኪንግተን "*በእንስሳ እርሻ* አና በጎረቤቶቹ መካከል ያለው መልካም የግንኙነት ስሜት የበለጠ ቋሚ መሆን እንዳለበት አፅንኦት በመስጠት ይሆናል። በአሳሞችና በሰው ልጆች መካከል የፍላጎት ግጭት ቀድሞ ያልነበረ ሲሆን ወደፊትም መኖር የለበትም። ትግሎቻቸውና መሰናክሎቻቸው አንድ ናቸውና። የሰራተኛ ችግር ሁላችንም ዘንድ አልነበረምን?"

እዚህ ላይ አቶ ፒልኪንግተን ለተሰብሳቢዎቹ አንደ በሚገባ የተቀመረ ምፀት ሊያስተላልፍ የፈለገ መሰለ። ሆኖም ሊናገር በፈለገው ምፀት ውስጡ እጅግ እየተገረመ ስለነበር ቃላቱን አውጥቶ ለመናገር ጥቂት ተቸገረ። ደጋግሞ ምራቁን ከዋጠና የተደራረቡት ኩልኩልቶቹ በዚሁ ሳቢያ ሳንባ ከመሰሉ በኋላ መናገር ያሰበውን ከጉሮሮው አወጣ።

*"እናንተ ዝቅተኛ እንስሳት ኖረዋችሁ ደስተኞች ከሆናችሁ"* አለ ፒልኪንግተን *"እኛም ዝቅተኛ መደቦች አሉን!"*

ይህ ምፀት በጠረጴዛው ዙሪያ የነበሩትን በሳቅ አንፈራፈራቸው። አቶ ፒልኪንግተን *በእንስሳ እርሻ* ስለተገነዘበው ዝቅተኛ የራሽን እደላ፣ የረጅም የስራ ሰአት እና በአጠቃላይ የቅንጦት አልባ አስተዳደር ዘዴ አሳሞቹን በድጋሚ "እንኳን ደስ ያላችሁ" አላቸው።

"እንግዲህ አሁን" አለ ፒልኪንግተን "ከመቀመጫዎቻችሁ እንድትነሱና ብርጭቆዎቻችሁም ሙሉ መሆናቸውን እንድታረጋግጡ እጠይቃለሁ። ክቡራን" ሲል ቀጠለ ፒልኪንግተን "ብርጭቆዎቻችሁን *ለእንስሳ እርሻ* ብልፅግና አንሱ!"

በእግር ኳኳታ የታጀበ ታላቅ ደስታ ሆነ። ናፖሊዮን ከተቀመጠበት ተነስቶ ፒልኪንግተን አጠገብ በመሄድ ብርጭቆውን አጋጭቶ ቢራውን በአንደ ትንፋሽ ጨለጠ። ብርጭቆዎች የማጋጨቱ ስነ ስርአት ጋብ እንዳለ (ናፖሊዮን እስከ አሁን በሁለት እግሮቹ እንደቆመ ነበር) እሱም የሚናገረው ጥቂት ቃላት እንዳሉት አስታወቀ።

እንደ ሌሎቹ የናፖሊዮን ንግግሮች ሁሉ ይህኛውም አጭርና መልእክቱን ብቻ የያዘ ነበር። በፒልኪንግተንና *በእንስሳ እርሻ* መካከል የነበረው አለመግባባት በማክተሙ እሱም ደስተኛ መሆኑን ተናገረ። *የእንስሳ እርሻ* ቀንደኛ ጠላት በሆነ አካል ለረጅም ጊዜ ሲናፈሱ የቆዩ አሉባልታዎች መኖራቸውን፣ እነዚህም አሉባልታዎች - እሱ ራሱ ናፖሊዮንና ጓደኞቹ ህጋዊ በነበረው የሰውልጅ አስተዳደር ላይ **አመፅ** ማካሄዳቸው ብቻ ሳይሆን አብዮታዊ የሆነ አመለካከት እንደነበራቸው፣ በጎረቤት እርሻዎች በሚኖሩ እንስሳት ውስጥም **አመፅ** ለማነሳሳት እንደሞከሩ ተደርገው የተወሩ አሉባልታዎች ነበሩ። ከነዚህ መሰረተ ቢስ አሉባልታዎች በላይ ከእውነት ያፈነገጠ ነገር አልነበረም።

ዛሬም ሆነ ቀድሞ እሱም ሆነ ጓደኞቹ የነበራቸው ምኞት፣- ከጎረቤቶቻቸው ጋር በሰላምና በተረጋጋ የንግድ ግንኙነት መኖር ነበር። ይህ *የእንስሳ እርሻ* ጣቢያ እሱ የሚያስተዳድረው

በመሆኑ ክብር የሚሰማው ሲሆን ይዞታውም በአሳሞች የጋራ ተራድኦ ድርጅት የተያዘና የባለቤትነት ማረጋገጫው ሰነድም በእጁ እንደሚገኝ ተናገረ።

በአሳሞች አስተዳደር በሚካሄደው *የእንስሳ እርሻ* ይዞታና በሰው ልጆች መካከል የነበሩት የቀድሞ ጥርጣሬዎች ዛሬም ያንዣብባሉ ብሎ እንደማያምንና መተማመንን ግን ይበልጥ ማጠናከር እንዲቻል በእርሻው ውስጥ ይዘወተሩ በነበሩ ልምዶች ላይ በቅርቡ ለውጥ መደረጉን አበሰራቸው።

ናፖሊዮን የተደረጉትን ለውጦች ሲያብራራ "እስከ አሁን ድረስ እንስሳቱ እርስ በርሳቸው የሚጠራሩበት የጅል ባህል ነበራቸው፤ 'ጓድ' መባባል። ከእንግዲህ 'ጓድ' ተባብሎ መጠራራት ታግዷል" አለ። "ምንጩ ያልታወቀ ሌላም አስገራሚ ባህል ነበር" ሲል ቀጠለ ናፖሊዮን "በአትክልቱ ስፍራ በሚገኝ ምሰሶ ላይ በተቸነከረ የአሳማ የራስ ቅል ፊት ለፊት ዘወትር እሁድ ጠዋት እንስሳቱ በሰልፍ የማለፍ ልምድ ነበራቸው። ይህም ተግባር ከእንግዲህ ታግዷል። የአሳማው ራስ ቅልም ተቀብሯል። ሰንደቅ አላማ መስቀያው ላይ የሚውለበለበውን አረንጓዴ ባንዲራ አይታችሁ በላዩ ላይ የተሳለውን ነጩን ሸኾና እና ቀንድ መቼም ልብ ሳትሉ አልቀራችሁም። የተመለከታችሁት ባንዲራ ከነምስሉ ታግዷል። ከእንግዲህ አረንጓዴ ቀለም ብቻ ያለው ባንዲራ ይውለበለባል" በማለት ናፖሊዮን የወሰናቸውን ለውጦች አስታወቀ።

አቶ ፒልኪንግተን ባደረገው ድንቅ ጎረቤታዊ ንግግር ላይ አንድ ነገር ብቻ ቅር እንዳሰኘውና ይህም ይዞታቸው የሆነውን የእርሻ ጣቢያ *የእንስሳ እርሻ* በማለት መጥራቱ እንደሆነ ገለፀላቸው።

እርግጥ ፒልኪንግተን *የእንስሳ እርሻ* የሚለውን ስያሜ ለውጥ በተመለከተ የሚያውቀው ነገር ባለመኖሩ መሆኑን ጠቅሶ እንደውም እሱ እራሱ ናፖሊዮን የ እርሻውን ጣቢያ ስያሜ ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ ሊያደርግ መዘጋጀቱንም ተናገረ።

"*የእንስሳ እርሻ (Animal Farm)* የሚለው ስም" አለ ናፖሊዮን "ከእንግዲህ ተሰርዟል። በምትኩ ከዛሬ ጀምሮ ይህ የእርሻ ጣቢያ በይፋ የሚታወቀው ***"የማኖር እርሻ"*** *(The Manor Farm)* ተብሎ ይሆናል።" በማለት አወጀ። በእሱ በናፖሊዮን እምነት ትክክለኛውና ኦሪጅናል መጠሪያው ድሮም ቢሆን ይህ ነበር ብሎ እንደሚያምንም ገለፀላቸው።

"ክቡራን" አለ ናፖሊዮን "በአቶ ፒልኪንግተን የተጀመረውን የደስ ደስ እንደግማለን፤ ግን በተለየ ስሜት ይሆናል። ብርጭቆዎቻችሁን እስከ አፍጢማቸው ሙሏቸው። ክቡራን፤ እነሆ ***ለማኖር እርሻ*** ብልፅግና!"

ልባዊ የሆነ ፌሽታ ቀለጠ። የየብርጭቆዎቹ ቢራም እንጥፍጣፌያቸው ሳይቀር ተጨለጠ።

ከውጪ ያሉት እንስሳት ትእይንቱን እየተመለከቱ ቢሆንም አንድ እንግዳ የሆነባቸው ሁኔታ ይታያቸዋል። በአሳሞቹ ፊት ላይ የተቀየረው ነገር ምንድን ነበር? የክሎቨር ደካማ አይኖች ከአንዱ ገፅታ ወደ ሌላው ተመላለሱ። አንዳንዶቹ አመስት
እጥፍጥፍ ኩልኩልት አላቸው፤ አንዳንዶቹ አራት፤ አንዳንዶቹ ሶስት። ከሰውነታቸው እየቀለጠ የሚቀየር የሚመስለው ነገር ደግሞ ምንድን ነው?

የደስታ ጭብጨባው አብቅቶ ታዳሚዎቹ አቋርጠውት የነበረውን የካርታ ጨዋታ ቀጠሉ። እንስሳቱም በመጡበት አኳኋን በፍጥነት መመለስ ጀመሩ።

እንስሳቱ ሃያ ሜትር እንኳን ሳይሄዱ ቆሙ። ከህንፃው ውስጥ ከፍተኛ ጫጫታ ይሰማቸዋል። ወደ ኋላ ተመልሰው በመስኮቱ በኩል አሻግረው ተመለከቱ። አዎ፤ አደገኛ የሆነ ብጥብጥ እየተካሄደ ነበር። አሳሞቹና ሰዎቹ ይጪጪሃሉ። ጠረጴዛውን ይደበድባሉ። እርስ በርሳቸው በጥርጣሬ ይተያያሉ። በከረሩ ቃላት ይካካዳሉ። የግጭቱ መነሾ ናፖሊዮንና ፒልኪንግተን ሁለቱም በአንድ ጊዜ እኩል አሸናፊነታቸውን የሚያሳዩ ካርታዎችን ማውረዳቸው ነበር።

አስራ ሁለት ድምፆች በንዴት ይጨቃጨቃሉ። ሁሉም ተመሳሳይ ነበሩ። እነሆ በአሳሞቹ ፊት ላይ የታየው ለውጥ ምን እንደ ነበር የሚያጠያይቅ አልሆነም። ከውጪ የነበሩት ፍጥረታት ከአሳማ ወደ ሰው ተመለከቱ። እንደገናም ከሰው ወደ አሳማ ተመለከቱ። መልሰው ከአሳማ ወደ ሰው ተመለከቱ። ***ነገር ግን የትኛው ሰው የትኛው አሳማ እንደሆን መለየት የሚቻል አልነበረም።***

ኖቬምበር 1943 - ፌብሩዋሪ 1944

***ተ ፈ ፀ መ***

**አንባቢ ሆይ!**

*እነሆ "የእንስሳት አብዮት"ን ጨረሱ። የዚህ መፅሀፍ ፅንሰ ሀሳብ መልእክት ጠቃሚ ሆኖ ካገኙት፤ መፅሀፉን ያላነበቡ በዙሪያዎ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ይህንን መፅሀፍ አግኝተው ያነቡት ዘንዳ የበኩልዎን ትብብር እንዲያደርጉ በትህትና እጠይቃለሁ። በትርጉም ስራው ላይ ያልዎትን አስተያየት ለተርጓሚው ማካፈል ቢፈልጉ የኢሜል አድራሻው ይኸውሎ፤-* mmtessema@gmail.com